*ምዕራፍ 14*

# መደራጀት፣ አመራርና አገልግሎት

አስከአሁን (በክፍል 2) ለቤተ ክርስቲያን እድገትና መታነጽ መሠረታዊ የሆኑ ስድስት መንገዶችን ማለትም ጸሎት፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ ፍቅርና አንድነት፣ ቅድስና፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ እና የሌላውን ሽክም መሸከም የሚሉትን ተመልክተናል። እነዚህ የእድገትና የመታነጽ መንገዶች መልክ ባለው ሁኔታ የሚገለጹት ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ቅርጽ ሲኖራትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አመራርና አገልግሎት ስታገኝ ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን የምታድገውና የምትታነጸው፡- የሕያው እግዚአብሔርን መሪነት በማወቅ በኃይለኛው በእግዚአብሔር ሥር ራሱን ዝቅ አድርጎ የሚያገለግል አመራር፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት ሲኖራት ነው።

ይህ ምዕራፍ በአራት ንዑሳን ክፍሎች ላይ ያተኮረ ነው። እነዚህም የመጀመሪያው አደረጃጀት፣ ሁለተኛው አመራር ሦስተኛው አገልጋይነትና አራተኛው የአገልጋይ መጠለፊያዎች (ፈተናዎች) ናቸው።

## *14.1 መደራጀት*

### 14.1.1 አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት

በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት የተገለጸው በተለያየ ሁኔታና መንገድ ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን ሲጓዙ በወገን በወገናቸው የሚሰፍሩበት አቅጣጫ ተመድቦላቸው ነበር (ዘኁ 2:2)። እቃዎቹን እንዴት አድርገው እንደሚይዟቸው ለአሠራሩ ሥርዓት ወጥቶለት እናገኛለን (ዘኁ 3)፣ አለቃም ነበራቸው (ዘኁ 3:32)። ይህም አደረጃጀት ነው።

በማደሪያው ድንኳን አገልግሎት እንዲያገለግሉ በእግዚአብሔር የተመረጡት ሌዋውያን/ ካህናት (ዘኁ 1-5) በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ያለውን አገልግሎት ያከናውኑ ነበር፣ ሊቀ ካህኑ ደግሞ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ያለውን አገልግሎት በዓመት አንድ ጊዜ ይፈጽም ነበር (ዘኁ 3:10)። ቤተ መቅደሱ በተሠራ ጊዜ «የእግዚአብሔርንም ቤት በሚሠሩት ላይ ለተሾመት ሰጠ፣ እነርሱም ይጠግኑና ያድሱ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቤት ለሚሠሩ ሠራተኞች ሰጠ» (2ዜና 34:10) እንደሚል በዚህ የአሠራር አደረጃጀትን እንመለከታለን።

በቤተ መቅደስ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለሚፈጽሙ አገልጋዮች የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ፣ አገልግሎቱ እንዴት መከናወን እንዳለበት ተገልጾና ለአገልጋዮች የአገልግሎት ሰሞን ወይም የክፍል ተራ ወጥቶላቸው ያገለግሉ ነበር። ይህ ይበልጥ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ታይቷል። «ዳዊትም ከአልዓዛር

ልጆች ከሳዶቅ ጋር፣ ከኢታምርም ልጆች ከአቢሜሌክ ጋር ሆኖ እንደ አገልግሎታቸው ሥርዓት ከፍሎ መደባቸው» (1ዜና 24:3 እንዲሁም 2ዜና 8:14)።

በእግዚአብሔር ስም ለሰሎሞን የወጣለት ዝና የእግዚአብሔርን ቤት ብቻ ሳይሆን የራሱንም ቤት ሳይቀር በሚገባ በማደራጀቱ ነበር። የሳባ ንግሥት «... የማዕዱንም መብል፣ የብላቴኖቹንም አቋቋም፣ የሎሌዎቹንም አሠራር፣ አለባበሳቸውንም፣ ... ባየች ጊዜ ነፍስ አልቀረላትም» (1ነገ 10:4-5)። ይህ እጅግ ደስ የሚያሰኝ አደረጃጀት እግዚአብሔር ለሰሎሞን ከሰጠው ጥበብ የተነሣ ነበር። የጥበብ ራስ የሆነው እግዚአብሔር ለቤቱ ሥራ የሚያስፈልገውን ጥበብ ሁሉ ይሰጣልና (ዘጸ 31:1-6)።

በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ሥራ በተደራጀና ሥርዓት ባለው ሁኔታ ይከናወን ነበር። ሐዋርያት የእግዚአብሔር ሥራ እየሰፋ ሲሔድ ማዕድን የሚያገለግሉ (ዲያቆናትን)[83] መረጡ (ሐዋ 6)። እንዲሁም ወንጌልን እየሰበኩ በዞሩባቸው ቦታዎችና ያመኑት ቁጥር እየጨመረ ሄዶ ቤተ ክርስቲያን ተብለው ለመደራጀት በደረሱ ጎብረቶች ሽማግሌዎችን ይሾሙላቸው፣ ራሳቸውንም ችለው ኃላፊነትን ይወስዱ ዘንድ በጸሎት ለጌታ አደራ ይሰጧቸው ነበር። «በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡዋቸው» (ሐዋ 14:23) እንደሚል።

ይህ ወንጌል በተዘራባቸው (በተሰበከባቸው) ቦታዎች ቤተ ክርስቲያንን «መትከልና» ማደራጀት ሐዋርያው ጳውሎስ ይከተለው የነበረ የአሠራር ሥርዓት ነው። ቲቶንም «የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማው እኔ አንተን እንዳዘዝሁ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቆርጤስ ተውሁህ» (ቲቶ 1:5)፣ እንደሚለው ማደራጀት በእግዚአብሔር ሥራ አስፈላጊና ትልቅ መንፈሳዊ ሥራ መሆኑን እንገነዘባለን።

## 14.1.2 ማደራጀት ምንድን ነው?

**ማደራጀት፡-** *ለሥራው የአሠራር ሥርዓት ማስያዝ፣ ሥራውን የሚመጥኑ ሠራተኞች መመደብ፣* ከእድገት ጋር የሚጣጣም ተስማሚ አሠራር (መዋቅር) *መቅረጽ ነው*። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ሥርዓት ባለው መንገድ ለመፈጸም የሚቻለው ራሷ ቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ (ድርጅታዊ) መልክ ኖሯት ተግባሯን «በሰላም» ማከናወን ስትችል ነው። የአሠራር ሥርዓት ማበጀት ሁከትን ለማጥፋት ይረዳል። «እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና» (1ቆሮ 14:33)።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያለውን የሥራ ዝርዝር ማወቅ፣ አገልጋዮችን መምረጥና ያለ አድልዎ በየሥራውና በየአገልግሎት ክፍሉ መመደብ በእግዚአብሔር ጥበብ የሚሠራ ከፍ ያለ የአመራር ደረጃ ነው። *መደራጀት ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ለሚሰጠው ገንዘብና ዕቃ የአሰባሰብ ስልት መቀየስን፣ በጥንቃቄ ገንዘብ መቀበልንና ለሚያስፈልገው ተግባር በጥንቃቄ ክፍያ ማከናወንን*

[83] Gk: diakoneo- from diakonos (dia and konis, to serve as deacon (1Ti 3:10, 1Ti 3:13).

ይጨምራል (2ነገ 12:5-16፣ 22:3-6፣ 1ዜና 9:22-34፣ 2ዜና 34:9-11)። ይህም ጥሩ አደረጃጀትን ይጠይቃል።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሰላም የሰፈነባት እንድትሆንና በአግባቡ ተልእኮዋን ትወጣ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የሥራ መጠን ማወቅ፣ የሥራ ዝርዝር ማዘጋጀት፣ ለሥራው ተስማሚና የእግዚአብሔር መንፈስ የሞላባቸው ሰዎች መመደብ፣ አሠራሩንም በተቀናጀና ሥርዓት በያዘ ሁኔታ እንዲሆን ማድረግ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሥራ ነው። «ሰዎች ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለው ይኖሩ ዘንድ የሚወድ» (1ጢሞ 2:1) እግዚአብሔር የቤቱም ሥራ እንደሚገባ የተደራጀና ሥርዓት የያዘ እንዲሆን ፈቃዱ ነው።

ስለሆነም ሥራዋን ለማከናወን ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ ቅርጽ ያስፈልጋታል። የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ስለሆነች (ማቴ 21:13) አወቃቀሯ ይህን እግዚአብሔር የሰጣትን ተግባርና ኃላፊነት (የጸሎት ቤት መሆንን) ለመፈጸም የሚያግዝ መሆን አለበት። ይህች ሕያው አካል ድርጅታዊ ቅርጽ ይዛ ዓላማዋን እንድታሟላ ራሷን ማስቻል፣ መዋቅር ማዘጋጀትና አገልጋዮችን መምረጥ ይገባል።

አያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ናት። ከአንድ በላይ የሆኑ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ ላይ ጎበረት ሲያደርጉ የሚመሠረተው ያ ጎበረት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች «ራስ» አይደለም። የአካሉ ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። የዚያ ጎበረት (ወይም ቤተ እምነት) ጥቅም ተመሳሳይ እምነትን ለማስጠበቅ፣ ለማስተማር፣ በአንድ ጎበረት ሥር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ተመሳሳይ የሆነ አሠራር እንዲኖር መንገድ ለማሳየትና ለመደገፍ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቤተ ክርስቲያኖችን ለመወከል ነው።

አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች ግንኙነቷ ቀጥታ ከጌታ ከክርስቶስ ጋር ነው። የምታመልከው እርሱን ነው። እያንዳንዱ አባል ሕያው የሆነ ግንኙነት የሚያደርገውም ከዚሁ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው። በመሆኑም ከአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «በላይ» የሆነ ጎበረት ወይም የአደረጃጀት ሥርዓት ይህንን ሊጋፋ ወይ ሊተካ አይገባውም።

በምድር ላይ ያለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእምነት አንድ ልትሆን (ልትመሳሰል) በተገባት ነበር። አንድ ጌታ አለና አንድ እምነት። ግን በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ቤተ ክርስቲያን ተከፋፍላና የተለያየ ስም ተሰጥቷት ትገኛለች። በምድር ላይ ብዙ ማኅበሮች (ቤተ እምነቶች) አሉ። ይህ በሰው ምክንያት የመጣው መከፋፈል ሁሉ ይቀርና በሰማይ አንዲት ቤተ ክርስቲያን (የክርስቶስ ሙሽራ) ብቻ ትሆናለች።

በአንድ አገር ወይም አካባቢ ተመሳሳይ እምነት ወይም ልምምድ ያላቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች የሚመሠርቱት ጎበረት (ወይም ቤተ እምነት) የቤተ ክርስቲያኖች ጎበረት ስለሆነ በአጠራሩ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ቢታወቅ ትክክል ይሆናል። ምክንያቱም ከተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች የሚመጡትንና በአንድ ላይ ጉባኤ የሚቀመጡትን ምዕመናን ወይም መሪዎች የሚያገናኛቸው ምክንያት የክርስቶስ አካል ክፍል መሆናቸውና የጎበረቱም ዋና ዓላማ የክርስቶስ ወንጌል ጉዳይ ስለሆነ ነው።

ይህ በምድር ከሚገኙ በልዩ ልዩ ስም ከሚጠሩ ጎብረቶች የተለየ ነው። ስለሆነም ጎብረቱ የቤተ ክርስቲያኖች ጎብረት መሆኑን በማመልከትና የአካባቢውን ወይም የአገርን ስም በማስቀደም ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ቢጠራ ትክክል ይሆናል።

አንዲት ቤተ ክርስቲያን ባለችበት አካበቢ ከጌታ የተሰጣትን ሥራና ኃላፊነት በተቻለ መጠን ሁሉ በራሷ ምእመናንና ከምዕመኗ በምታገኘው ገቢ ልታከናውን ያስፈልጋል። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመነሻ የመደራጀትዋ ጊዜ (በመትከያ ወቅት) ወይም ስደትና ችግር በደረሰባት ጊዜ እንዲሁም ለየት ያለ የሥራ እንቅስቃሴ ስታደርግ ከሌሎች ወገኖች ስጦታ ልትቀበል ብትችልም (ሐዋ 24:17፣ ሮሜ 15:26) በአጠቃላይ ግን ቤተ ክርስቲያን በራሷ አባሎች ወንጌልን የምታስፋፋ፣ በራሷ አባሎች የምትተዳደርና የምትመራ፣ ከምዕመኗ በሚገኘው ኢሥራት፣ መባና ስጦታ ወጪዋን የምትሸፍን ልትሆን ይገባል። ራእይንና ሥራን የሚሰጥ እግዚአብሔር ለሥራው ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን ሁሉ አብሮ ይሰጣል።

**የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት እግዚአብሔርን ማክበር ዓላማው ያደረገ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ያለው፣ «አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ»[84] እንደሚቀመጥ (ማቴ 9:17) ለሥራው ተስማሚ የሆነ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን በጊዜው የደረሰችበትን እድገቷንና የሥራዋን መጠን ያገናዘበ፣ ምዕመናን ሁሉ እንደየጸጋቸውና በጎብረት እንዲያገለግሉ ለሥራ የሚጋብዝ፣ ቀልጣፋ የሥራ አሠራር ሥርዓት ያለው፣ ግልጽ የሆነ የሥራ ክፍፍል የሚታይበት (ሐዋ 6:3) እና እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል የሚችል ድርጅታዊ መዋቅር ሊኖራት ይገባል።**

## አገልጋዮችን መምረጥና መሾም

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መዋቅር ከተዘጋጀ በኋላ ለመንጋው የሚጠነቀቁ (ሐዋ 20:28)፣ ታማኝና ልባም የሆኑ (ነህ 13:13፣ ማቴ 20:15፣ 1ቆሮ 4:2)፣ በመልካም የተመሰከረላቸውና መንፈስ ቅዱስ ጥበብም የሞላባቸው (ሐዋ 6:3)፣ ለወገኔ ይጠቅማል የማይሉ (ፊሊ 2:3)፣ ከሌሎች ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈሩ (ነህ 7:2)፣ ያለ አድልዎ የሚያገለግሉ (1ጢሞ 5:21)፣ በኑሮአቸው ምሳሌ የሚሆኑ (1ጢሞ 4:12፣ 1ጴጥ 5:2-3)፣ **አገልጋዮችን መምረጥና መሾም ያስፈልጋል።**

እነዚህ አገልጋዮች ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው የሚያውቁና ያለ ጌታ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ የተረዱ (ዮሐ 15:5፣ 1ቆሮ 4:7)፣ በአገልግሎታቸው ችግር ሲገጥማቸው ችግራቸውን ወደ እግዚአብሔር አቅርበው መልስ መቀበል የተለማመዱ (ዘጸ 17:4፣ ዘኁ 16)፣ በተመሠረተው እውነተኛ መሠረት ላይ በጥንቃቄ የሚያንጹ (1ቆሮ 3:10)፣ በግድ ሳይሆን በውድ መንጋውን የሚጠብቁና የሚያገለግሉ (1ጴጥ 5:2-3)፣ «እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ሊልቅ እኔ

[84] በዚህ ክፍል «አቁማዳ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው- ተስማሚ የአሠራር ዘዴን፣ አደረጃጀትንና አወቃቀርን ነው። a propriety or fitness of things." (Mt 9:17 Barnes).

ግን ላንስ ይገባኛል» (ዮሐ 3:30) በማለት በትሕትና የሚያገለግሉ እና የእግዚአብሔርን ክብር የማይሻሙ ሊሆኑ ያስፈልጋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው ሰዎች በመሪነት ቦታ በቀጥታ በእግዚአብሔር የተሾሙበት፣ በሰው በኩል በእግዚአብሔር የተሾመበት፣ ራሳቸውን የሾሙበትና በሰው በኩል የተሾሙበት እንደ ነበረ እንመለከታለን።

1 ቆሬ ራሱን የሾመና ሌሎች ብዙዎችን ከእርሱ በኋላ ያሰለፈ ሰው ነበር (ዘኁ 16)። እስራኤላውያን ኑ አለቃ ሾመን ወደ ግብፅ እንመለስ ብለው እርስ በርሳቸው ሊነጋገሩና አለቃ ለመሾም ሲመካከሩ በዘኁ 14:4 እንመለከታለን። ይህም አካሄዳቸው ከእግዚአብሔር ሀሳብ የሚቃረን የሰው ምክር ብቻ እንደ ነበረ እናስተውላለን። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ዲዮጥራጢስ ራሱን ከፍ አድርጎ የተመለከተና የሾመ ሰው ነበር።

2 ኢዮርብዓም ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ በእስራኤል ማነበር መካከል «... ከሌዊ ልጆች ካይደሉ ከሕዝቡ ሁሉ ካህናትን አደረገ» (1ነገ 12:31) ይላል። እነዚህ ካህናት የራሱን ሀሳብ (ምኞት) ለማስፈጸም የመረጣቸውና የሾማቸው ነበሩ። በሰው ብቻ የተመረጡ አገልጋዮች ምሳሌ ናቸው።

3 እግዚአብሔር በቤቱ የሚያገለግሉትንና በሕዝቡ ፊት የሚቆሙ አለቆችን (መሪዎችን) በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ራሱ ይመርጣል። እግዚአብሔር የሚሾማቸውን ሰዎች በስም እየጠራ በቀጥታ ራሱ ሲሾማቸው ብዙ ቦታ እንመለከታለን። ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያው ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ «ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና» (ሐዋ 26:16) ብሎት ነበር ለአገልግሎቱ የሾመው። ስለዚህም ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ «ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ የቆጠረኝን እግዚአብሔርን ...» (1ጢሞ 1:12) በማለት ነበር ስለመሾሙ የመሰከረው።

4 እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በሰዎች በኩልም ሲሾም እናያለን። ሐዋርያት መመዘኛዎችን አዘጋጅው አገልጋዮችን እንደ መረጡ በሐዋ 6:1-6 እናነባለን። እንዲሁም በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን እንደ ሾሙ እናያለን። በኤፌሶን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተሹመው ነበር (ሐዋ 20:17)፣ በፊሊጵስዩስ ኤጲስ ቆጶሳትና ዲያቆናት ነበሩ (ፊሊ 1:1)። ጳውሎስ ስለ ጢሞቴዎስ የወንድሞችን ምስክርነት ተቀብሎ ለአገልግሎት ይዞት እንደ ሄደ በሐዋ 16:1-4 እንመለከታለን። በኋላም የታመኑ መሪዎቹን እንዲሾም ጢሞቴዎስን ሲያዘው እናያለን (2ጢሞ 2:1-2)። ይህ በሰዎች በኩል የሚፈጸም የእግዚአብሔር አሠራር ነው። ስለሆነም በእግዚአብሔር ቃል መመዘኛነት ሽማግሌዎችን ዲያቆናትንና ሌሎች አገልጋዮችን በመምረጥ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ማካሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

እንግዲህ በመሠረቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን የሚሰጥ/የሚሾም እግዚአብሔር ነው። ለቤቱ አገልጋዮችን የሚሾም እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ግን በቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ከሚሾሙት ሰዎች መካከል ለአገልግሎቱ በእግዚአብሔር ያልተመረጡ ወይም የሚሾሙበትን ቀን የሚናፍቁ (2ሳሙ 15:4) ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት የሚሾም ሰው

በእግዚአብሔር የተመረጠ ስለ መሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ ሊኖር ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን የሚመርጡና የሚሾሙ ሰዎች ትልቅ ኃላፊነት የተሸከሙ ስለሆኑ በእግዚአብሔር የተመረጠውን ያውቁ ዘንድ በብዙ ጸሎት እግዚአብሔርን የሚያደምጡ መሆን ይኖርባቸዋል። የራሳቸውን ወይም የብዙኃኑን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያስፈጽሙ ስለሆኑ እርሱ የሚወደውን ለማድረግ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው ማለት ነው።

## 14.1.3 በራእይና በእቅድ መሥራት

እግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ አለው። ይህ እቅድ በእርሱ ሁሉን አዋቂነት፣ ሁሉን ቻይነትና ባለመለወጡ ላይ የተመሠረተ ነው።

እቅድ ወደ ፊት ተከናውኖ እንዲታይ የሚፈለገውን ሥራ አስቀድሞ ማየት፣ ወደዚያ ግብ የሚደረስበትን ስልት መምረጥና ሥራውን በተግባር መተርጎም ነው። በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ እቅድ መንደፍ ወደ ፊት ሊሆን የሚፈለገውን ከወዲሁ በማየት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመፈጸም ይረዳል/ያስችላል። ይህን እግዚአብሔር የሚያየውን ለማየት በፊቱ መቅረብን ተስፋ ማድረግንና እምነትን ይጠይቃል።

ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ የዕቅድ ሥራ ሂደት ከመነሻው ከጽንሰ ሀሳቡ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ቢያንስ አራት ዋና ደረጃዎች አሉት። እነርሱም፦

- ማቀድ
- ማከናወን/ መተግበር
- መከታተልና
- መገምገም ናቸው።

ማቀድ ያለፈውን በመገምገምና የአሁኑን ሁኔታ በሚገባ በማጤን ለወደፊቱ ዓላማ፣ ግብ፣ ስልትና የአፈጻጸም መርሃ ግብር ማዘጋጀት ነው። እቅዱን ማከናወን፦ በሥራ መተርጎም ሲሆን መከታተል ደግሞ አፈጻጸሙን በቅርብ መመልከትንና ከእቅዱ አንጻር በየደረጃው መመዘንን ያጠቃልላል። በአራተኛው ደረጃ ያለው መገምገም ደግሞ የተዘጋጀው እቅድ ከተፈጸመ (ከተሠራ) በኋላ በእቅዱ የታየው ዓላማና ግብ በምን ያህል መፈጸሙን፣ አፈጻጸሙ በታቀደው ስልት መሠረት መሆኑን በዝርዝር ማየት ነው። ይህም ለሚቀጥለው እቅድ ጠቃሚ ትምህርትና መረጃ ይሰጣል።

የእግዚአብሔር ሰዎች በየዘመናቸው በተገለጠላቸው መጠን በእቅድ ሲሠሩ ኖረዋል። ኖኅ ወደ ፊት የሚሆነውን ከእግዚአብሔር አስቀድሞ በመረዳቱ ለመቶ ሃያ ዓመታት ያህል መርከብ በመሥራት ለሚመጣው የጥፋት ውኃ ሲዘጋጅ ቆይቷል (ዘፍ 6:13-22)። ዮሴፍ በግብፅ ላይ ሊመጣ ስላለው ረሃብ ከእግዚአብሔር በመረዳቱ ረሃቡ ከመምጣቱ በፊት ለሰባት ዓመታት ስንዴ በማከማቸት ለረሃቡ ዘመን ዝግጅት አድርጓል (ዘፍ 41:46-49)። ነህምያ ስለ

ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ከሰዎች ከተረዳና ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ የቅጥሩንም ሁኔታ እራሱ ተዘዋውሮ ከተመለከተ በኋላ ቅጥሩን የማደስ እቅድና ዝግጅት አድርጎና ሥራውንም አጥብቆ በመያዝ (ነህ 5) እግዚአብሔር የሰጠውን እቅድ በተግባር ላይ አውሎታል።

ራእይ[85] ስለ ወደፊቱ ያለውን ማየት መቻል የሚል አጠቃላይ ትርጉም አለው። የቃሉ የሥነ መለኮት መዝገበ ቃላት ትርጉሙ፡- ሰው ሳይተኛ (እንቅልፍ ሳይወስደው) ስለ አንድ ሁኔታ ወይም ነገር ከእግዚአብሔር የሚሰጠው መገለጥ ወይም መረዳት ነው። በዚህ መጽሐፍ ራእይ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ምሪትን ነው። ይህ ምሪት ምንጩ ብቻ እግዚአብሔር ይሁን እንጂ «በራእይ»፣ በሕልም፣ በመንፈስ፣ በቃሉ መገለጥ ወይም ሌላ እግዚአብሔር ሊጠቀምበት በወደደው መንገድ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል።

በእቅድ የሚሠራ ሰው ከሁሉ አስቀድሞ ስለ ሥራው ከእግዚአብሔር ራእይ ለመቀበል ይጸልያል። የተቀበለውን ራእይ በተግባር ለመተርጎም እቅድ ለማዘጋጀትና ስልትም ለመንደፍ ይጸልያል። ሥራውን ለመጀመር፣ በሥራው ላይ ለሚነሣ ችግር ምሪትንና መፍትሔን ለማግኘት በየጊዜው ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል (ነህ 1:4፣6፣ 2:4፣12፣ 4:9፣ ዕዝ 8:21)። ስለዚህ ራእይና እቅድ የጸሎት «ልጆች» ማለትም ውጤቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በጸሎት ነው። ስለ ሥራው የእግዚአብሔርን ፊት አጥብቆ የሚፈልግ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሥራ እቅድን ይቀበላል።

**መለኮታዊ ራእይ** እግዚአብሔር የሚያየውን እርሱ በሚገልጠው መጠን አርቆ ማየት፣ የእርሱን ዓላማ መረዳትና ከእርሱ ጋር በመሥራት የእርሱን ፈቃድ መፈጸም ነው። ራእይ እግዚአብሔርን በማወቅና ሀሳቡን በመረዳት ይጀምራል። ራእይ **በጸሎት** ይወለዳል። ራእይ አሁን ከሚታዩት ሁኔታዎች በላይ የሆኑና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ነገሮችን አልሞ መነሣት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ከመነሣት አስቀድሞ እግዚአብሔርን መጠየቅና እርሱ የሚሰጠውን ራእይ ማየት፣ እንደ ይሳኮር ልጆች ዘመኑን ማወቅ (1ዜና 12:32) ያስፈልጋል። ይህንንም እግዚአብሔር በቅንነት ለሚጠይቁት ይሰጣል። ራእይ በሌለበት መጥፋት አለና (ምሳ 29:18፣ ሰቆ 2:9)።

«ባለ ራእይ» የሆነ ሰው ራእዩ እስኪፈጸም ተግቶ የሚሠራ፣ በዓላማው የሚጸና፣ ሰው ነው። ራእይ የተቀበለ ሰው በሥራው ላይ በሚነሣው ችግርና ተቃውሞ ተስፋ ሳይቆርጥ ራእይ የሰጠውን እግዚአብሔርን በተስፋ የሚጠብቅ፣ በእግዚአብሔር የኃይል ችሎት ላይ የማተማመን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት በማጥበቅ ኃይሉን በየጊዜው የሚያድስ ሰው ነው።

ቤተ ክርስቲያን ዓላማዋንና ተግባሯን በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን ትችል ዘንድ ከአመት ወደ አመት ባለፈች ቁጥር እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባታል። ይህንም ስታደርግ ሳለ እስካለችበት ጊዜ ድረስ በተሠራው መጠንና የአሠራር ልምድ በመነሣት፣ አሁን ያለችበትን ዘመንና ሁኔታ በማጤን፣ ወደ ፊት ምንና እንዴት ሊሠራ እንደሚገባ የሥራ ንድፍ ማውጣት አሠራሩን የተያያዘና ቀጣይነት ያለው

---

[85] vision - (Heb: haza, Gk: harao- to perceive, to see). በመጽሐፍ ቅዱስ - ራእይ vision - a supernatural presentation of certain circumstances to the mind of a person while awake.

ያደርገዋል። የሥራ እቅዱ በሥራ መተርጎም ሲጀምር ሥራውን ማቀናጀት፣ የሥራውን እፈጻጸምና አሠራር በቅርብ ሆኖ መከታተልና በየደረጃው መገምገም ያስፈልጋታል።

ይሁን እንጂ ስው ምንም ያህል ድንቅ የሚባል የተቀናጀ የሥራ እቅድና የአሠራር ስልት ቢያዘጋጅ፣ እግዚአብሔር ለዚያ ዘመንና ሁኔታ ያለው ሀሳቡ ምን እንደሆነ በመረዳት እንደ ሀሳቡ የሆነ እቅድ ካልተዘጋጀና ሥራውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካልተሠራ በስተቀር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው። ስለሆነም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አስተዋይ አገልጋይ የእግዚአብሔርን መሪነት የሚያውቅና እርሱን በቅርበት ሆኖ የሚከተል ነው። ይህ ካልሆነ ግን እቅዱ ለእግዚአብሔር ክብር የማይሆን፣ «ዘላለማዊ ዋጋ» የሌለውና ውጤት የማይገኝበት ከንቱ ልፋት ብቻ ይሆናል።

## 14.1.4 መረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር

የእቅድ ሥራ አሠራሩም ሆነ ውጤቱ በአንዛዊ አገላለጽ ካልተገለጸ በስተቀር እቅድ መሆኑ ይቀራል። እቅዱን የማይቆጠር፣ የማይለካ፣ የማይመዘን ያደርገዋል። ስለሆነም ለእቅድ ሥራ መረጃ በመሰብሰብ አጠናቅሮ መያዝ ሥራውንም በአንዛዊ አገላለጽ መግለጽ አስፈላጊ ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ማስረጃ እንደምናየው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሌላው ለመለየት ሕዝቡን መቁጠርና ማወቅ አስፈላጊ ነበር (ዕዝ 2:62-63፣ ነህ 7:5-8)። በሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች እንደተጨመሩና (ሐዋ 2:41) አምስት ሺህ እንደ ደረሱ (ሐዋ 4:4) ሉቃስ መዝግቧል። መበለቶችም ይመዘገቡ ነበር (1ጢሞ 5:9-10)። ኖኅ የሠራት መርከብ ርዝመት ወርድና ከፍታ የተለካ ነው (ዘፍ 6:15)። በነነዌ የነበሩ ሰዎች ቁጥር ይታወቃል (ዮና 4:11)።

የእግዚአብሔር ቤት ንብረትና ለስጦታ የሚሰጠው ሁሉ ይመዘንና የተመዘነውም በየዓይነቱ ይጻፍ ነበር። የአገልጋዮች ልብስ ዓይነትና ቁጥር፣ ገንዘቡ፣ ንብረቱ ሁሉ ተመዝግቧል (ዕዝ 8:1፣34፣ ነህ 7:69-72)። እንዲሁም ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ የደብዳቤ ልውውጦች፣ ሥራው መቼ ተጀምሮ መቼ እንዳለቀ ተመዝግቧል። በሥርዓት የተቀመጠ መዛግብት በሚፈለጉበት ወቅት ታላቅ አገልግሎት ይሰጣሉ (ዕዝ 4፣ 6:1-2፣ 10:16-17፣ አስ 6:1-9)፣ ለእግዚአብሔርም ክብር ይሆናሉ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ምዕመኗን ለይታ ልታውቅ፣ የገንዘቧንና የንብረቷን ልክ በጥንቃቄ ልትመዘግብ፣ መዛግብቶቿን ሁሉ በሚገባ ልትይዝ ይገባታል። ለቤተ ክርስቲያን እድገት የሚሆን እቅድ ማዘጋጀትና አሠራሮችንም ገምግሞ የተሻለ አሠራር መንደፍ የሚቻለው አኃዞችና መረጃዎች በትክክል ተመዝግበው ሲያዙ ነው። ስለዚህ መረጃን መሰብሰብና ማጠናቀር የጥሩ አደረጃጀትና አሠራር አንድ መልክ ነው።

## 14.1.5 ሂሳብ አያያዝና አዲት - «ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን»

ቤተ ክርስቲያንን የማደራጀትና ሥርዓት ያለው አሠራር የመቅረጽ አንዱ ተግባር የአግዚአብሔር ቤት ንብረትና ገንዘብ በጥንቃቄ የሚያዝበትን መንገድ ማበጀት ነው::

ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ስለመሆኑና ከአግዚአብሔር ያልሆነ በረከት የማግኛ መንገድ ሁሉ በአግዚአብሔር ፊት የተጠላ መሆኑን በዚህ መጽሐፍ በቀደሙት ምዕራፎች ተመልክተናል:: በዚህ ቦታ በአጭሩ የምናየው ከገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ቤተ ክርስቲያን ልታደርገው የሚገባትን ጥንቃቄ ነው::

ወንጌልን የሚያገለግል ሰው መኖሪያውን ከወንጌል ይቀበል ዘንድ የጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ ነው:: «ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል» (1ቆሮ 9:14):: «ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል» (ሉቃ 10:7):: እንዲሁም «ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል» (ገላ 6:6)::

ከገንዘብ ጋር ግንኙነት ያለው አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች «ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን» ማለት ይችሉ ዘንድ ንጹሕና ግልጽ የአሠራር ሥርዓት ማበጀት አለባቸው:: ጥንቃቄው ደግሞ «በጌታ ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ» ነው (2ቆሮ 8:20-21):: የገንዘብ ኮረጆ የሚይዝና ዕቃም የሚገዛ ወይም ለበጎ ሥራ ወጪ የሚያደርግ ሰው (ዮሐ 13:29) በእጁ ከሚያልፈው ገንዘብ ውስጥ እንደ አስቆሮቱ ይሁዳ ሰራሱ እንዳያስቀርና (ዮሐ 12:6) ወጥመድ እንዳይሆንበት እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ ይገባዋል::

ሥልጣን በገንዘብ ላይ ማዘዝና ከገንዘብም ተጠቃሚ የመሆን መብትን እስካላስገኘ ድረስ ይህ ሥልጣን ሳይሆን እንዲሁ በነጻ አገልግሎት መስጠት ብቻ የሚመስላቸው ጥቂት አይደሉም:: ብዙ ጊዜ ሥልጣንን የሚመኝ ሰው ሥልጣኑን የሚፈልገው በትረ-ሥልጣኑ በገንዘብ ላይ የወደደውን ለማድረግ እስካስቻለው ድረስ ይሆናል:: «ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ» (ሉቃ 3:13) እንዲሁም «ደመወዛችሁ ይብቃችሁ» (3:14) የሚለው የጌታ ቃል በቤተ ክርስቲያን ለሚያገለግሉ ሽማግሌዎችና እረኞችም ጭምር ነው:: እግዚአብሔር በአደራነት እንዲያስተዳድሩት በሰጣቸው ገንዘብ የወደዱትን ለመጥቀም፣ «ወዳጅም» ለማፍራት የሚደረግ ሙከራ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው:: ወዳጅ የሚያፈራ በግል ገንዘቡ ያድርገው:: የአግዚአብሔርን ገንዘብ ግን በአደራ የተቀበለው በመሆኑ እግዚአብሔርን በመፍራት ያስተዳድረው::

እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች በገንዘብ ነገር ታማኞች ሆነው ቢገኙ እምብዛም የሚያስደንቅ መሆን የለበትም:: ይህ እግዚአብሔርን ከሚያውቁ ሰዎች ሁሉ የሚጠበቅ አነስተኛ የታማኝነት ደረጃ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ኃላፊነት የነበራቸው ሰዎች «ነገር ግን እነርሱ የታመኑ ነበሩና በእጃቸው ስለ ተሰጠ አይቆጣጠሩአቸውም ነበር» (2ነገ 22:7) የተባለላቸው ታማኝ አገልጋዮች ነበሩ::

በሌላ በኩል ደግሞ በከፍተኛ የአገልግሎትና የኃላፊነት ደረጃ ላይ ሆነው ያልታመኑ አገልጋዮች እንደነበሩም እንረዳለን። የጌታ ደቀ መዝሙር የነበረው የአስቆርቱ ይሁዳ በአንደበቱ ለድሆች አዛኝ የሚመስል ሰው ነበር። «ማርያምም እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፣ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች» በዚህ ጊዜ «የአስቄርቱ ይሁዳ፡- ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው» ባለ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ «ይህን የተናገረ ... ሌባ ስለ ነበር ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፣ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው» (ዮሐ 12:6) ይላል። ይሁዳ ምላሱና እጁ፣ አንደበቱና ልቡ የተለያዩበት ሰው ነበር። በትንሹ መስረቅ የለመደ ሰው ደግሞ ደቀ መዝሙርም እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔርን ቤት ገንዘብ ከመስረቅና እንደ ይሁዳ ጌታውን በገንዘብ ከመሸጥ አይመለስም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ወንጌል ስብከቱ እንደሚጠነቀቅ ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ገንዘብ አያያዝም ብርቱ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር። የእግዚአብሔርን (የቤተ ክርስቲያንን) ገንዘብ አያያዝ በተመለከተ ጥንቃቄ የሚያደርገው በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያለ ነቀፋ ሆኖ ለመገኘት ነው። ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደጻፈላቸው «ስለምናገለግለው ስለዚህ ለጋስ ስጦታ ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን? በጌታ ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለንና» (2ቆሮ 8:20-21) ይላል።

አንድ መሪ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ያህል ጥንቃቄ አድርጎ ሳለ ሰው ሁሉ ጥንቃቄውን ላያደንቅለት ይችላል (2ቆሮ 12:17-18)። ይሁን እንጂ ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በታማኝነት ለመያዝ በሰው ሁሉ ዘንድ ያለ ነቀፋና በግልጽነት ለመጠበቅ የቆረጠ ሰው ነበር። እንግዲህ ገንዘብን በሚመለከት እንደ ሌላው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሁሉ ተጠያቂነቱ ድርብ ነው። ወደ ላይ ለእግዚአብሔር ወደ ጎን ደግሞ ለሰው ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገንዘብ ያዥ የሚመደበው የሂሳብ አያያዝ እውቀት ወይም ችሎታ ስላለው ብቻ መሆን የለበትም። በገንዘብ ጉዳይ ኃላፊነት የሚሰጠው ሰው የሂሳብ እውቀት ያለውና እንዲሁም በወንጌል አገልግሎቱም የተመሰከረለት መሆን አለበት። ገንዘብን መያዝና ማስተዳደር «የሂሳብ ችሎታ» ጉዳይ ቢመስልም እንኳን ገንዘቡ ግን የወንጌል ገንዘብ ነው። ከመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተዋጣውን ገንዘብ በኢየሩሳሌም ለነበሩ ወገኖች እንዲያደርስ ከቲቶ ጋር ስለተመረጠው ሰው «ስለ ወንጌል ስብከት በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወንድም እንልካለን» ተብሎ ተመስክሮለታል (2ቆሮ 8:18)። «ብዙ ጊዜም በብዙ ነገር መርምረን ትጉ እንደ ሆነ ያገኘነውን» እንደሚል ይህን ኃላፊነት የሰጡት በብዙ ምርመራ ወይም አዲት ተፈትኖ ታማኝነቱን ላሳየ ሰው ነበር (8:22)። ይህ ሰው በአብያተ ክርስቲያናትም የታወቀና የተመረጠ ሰው ነበር (8:19)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሁሉ ጥረት የደረገው በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያለ ነቀፋ ሆኖ ለመገኘት ነው። ሐዋርያት የማዕድ አገልጋዮችን ለመምረጥ «በመልካም የተመሰከረላቸውን፣ መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ምረጡ» (ሐዋ 6:3) ነው ያሉት። ሰዎች በመልካም የሚመሰክሩላቸው ብዙ ጊዜ መልካም ሲሠሩ ላዩአቸው ሰዎች ነው። ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ደግሞ በመልካም

የሚመሰከርላቸው በታማኝነታቸው የታወቁ ሲሆኑ ነው። ታማኝነታቸውም ገንዘብን ለመያዝ ብቻ ሳይሆን ለወንጌል ታማኝ የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ ነው።

**በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ገንዘብ አያያዝ ግልጽነት ሲጎድል የአመራር ድክመት ለመኖሩ አንድ አመልካች ነው።** በገንዘብ አያያዝ ግልጽነት አለመኖር ራስን ለነቀፋ ማጋለጥ ነው። ጠንቃቃ መሪዎች ስለ ገንዘብ ጉዳይ በእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን በሰዎችም እንዳይነቀፉ ይጠነቀቃሉ። አንዱ የጥንቃቄ መንገድ ደግሞ አሠራሩን ሰው ሊያየው በሚችለው መንገድ በመሥራት ግልጽ ማድረግና ሂሳቡን ማስመርመር (ኦዲት ማስደረግ) ነው።

## 14.2 አመራር

### 14.2.1 የአመራር ሀ ሁ፦ የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ ነው

ሕያው እግዚአብሔር ሕያው ቃሉን እየገለጸ፣ በሕያው መንፈሱ እየተናገረ፣ እርሱ ራሱ በሕያውነት በቤቱ እየተመላለሰ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራ እርሱ ነው። ቤተ ክርስቲያን በውክልና[86] አትመራም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዋ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በሕያውነት አለ። በራእ 3:20 እንደምናነበው ጌታ ወደ ውጪ እንዲወጣ ካልተደረገ በስተቀር የክርስቶስ ኢየሱስ ቦታ ሁልጊዜ አብሮ በቤቱ ከሕዝቡ ጋር መሆን ነው።

**በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለ ዙፋን አንድ ብቻ ነው፣ የእግዚአብሔር ዙፋን።** እግዚአብሔር የሕዝቡ ንጉሥና መሪ ነው። መጽሐፍ «በቸርነትህ የተቤዠሃቸውን ሕዝብህን መራህ» (ዘጸ 15:13) እንደሚል እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ፣ ያዳነውን፣ የታደገውን ሕዝብ ለሌላ መሪ፣ ለሌላ አለቃ አሳልፎ እይሰጥም። ያዳነውን ሕዝብ እራሱ ይመራል። ሙሴም እግዚአብሔርን የጠየቀው «አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ፣ ከዚህ አታውጣን። በምድር ፊት ካለው ሕዝብ ሁሉ እኔና ሕዝብህ የተለየን እንሆን ዘንድ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ እኔና ሕዝብህ በአንተ ዘንድ ሞገስ ማግኘታችን በምን ይታወቃል (ዘዳ 33:14-15) ብሎ ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኘ ሕዝብ እግዚአብሔር የሚመራው፣

---

[86] የውክልና ሥልጣን (delegated authority) አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ መገኘት ስለማይችል፣ ሁሉን ሥራ ለማከናወን ጊዜውም እውቀቱም ስለማይኖረው እንደ እርሱ ሆነው የሚሠሩለትን ሰዎች በመምረጥ ሥራውን ያከፋፍላል፣ ኃላፊነቱንም ከተገቢው ሥልጣን ጋር ይሰጣል። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፣ በሁሉ ቦታ የሚገኝ፣ ሕያው አምላክ ከጊዜ እጥረት ወይም ከሥራ ብዛት የተነሣ የእርሱን ሥራ እንዲሠሩለት የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለሌሎች አይወክልም። የተወከለ (delegated) የሚለው ቃል የሚጠቁመው የሚያደርገው ባለቤቱ በሌለበት «in the absence of» የሚለውን ነው። እግዚአብሔር ግን የሌለበት ጊዜ የለም። «ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ያለው ጌታችን ለዚህ ነው። የቤተ ክርስቲያን አመራር ከእግዚአብሔር የተወረሰ ሥልጣን አይደለም። አልጋ ወራሽ በእግዚአብሔር መንግሥት የለምና። ስለማይም አማኞች የርስቱ ወራሾች የምንሆነው የሚያወርሰን እግዚአብሔር ራሱ በሕያውነት በሚገኝበት ከእርሱ ጋር አብረን ነው የምንወርሰው።

እግዚአብሔር አብሮት የሚሄድ ሕዝብ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሴላው «ተጓዥ» የሚሰየው የራሱን ሕዝብ የሚመራ እግዚአብሔር አብሮት መጓዙ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። **በጎቹ የክርስቶስ** ናቸው፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚመግባት ክርስቶስ ነው።

እግዚአብሔር **የሕዝቡ ዳኛና ፈራጅ** ነው። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚነሣውን ክርክር በጽድቅ ይዳኛል። ማርያምና አሮን በሙሴ ላይ በተነሡበት ጊዜ ትሑት የሆነው ሙሴ አልተበቀላቸውም፣ ክፉን በክፉ አልመለሰም። ነገር ግን ሙሴ ተቃውሞውን በእግዚአብሔር ፊት አቀረበዉ። ጌታም ከሳሾቹንና ተከሳሹን ወደ መገናኛው ድንኳን ጠርቶ ዳኝነትን ሰጠ (ዘኁ 12)። እንዲሁ ቆሬና አቤሮን በሙሴ ላይ በቅንዓት በተነሡበት ጊዜ እግዚአብሔር በጽድቅ ፍርድን አድርጓል (ዘኁ 16)። እግዚአብሔር በእሳት የሚመልሰው ከጣዖታት የተሰየ ሕያው አምላክ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ላይሆን (1ነገ 18) በሕዝቡም መካከል በጽድቅ ለመገኘትና ሕዝቡን ለመዳኘት ነው (ዘኁ 16)። እግዚአብሔር አይወግንም። የእግዚአብሔር የሆኑትን ግን ወደ እርሱ ይጠራቸዋል (ዘጸ 32:26)።

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ያላቸውን ድርሻ በትክክል ማወቅ ይገባቸዋል። የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር ስለሆነ እረኞችና ሽማግሌዎች ራሳቸውም ቢሆኑ በእግዚአብሔር መሪነት ሥር መሆናቸዉን መዘንጋት የሰባቸውም። የእስራኤል ልጆች ዮርዳኖስን ተሻግረው ከነዓንን ለመውረስ በተዘጋጁ ጊዜ ኢያሱ ሰይፍ በእጁ የያዘውን ሰው አየ። እርሱንም ከማን ወገን እንደሆነ ሲጠይቀው የሰውየው መልስ ከማንም ወገን እንዳልሆነ ነገር ግን «እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ መጥቻለሁ» (ኢያ 5:14) የሚል ነበር። ለዚህ «የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ» ስለሆነው «ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና፦ ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው?» (5:14) ብሎ ጠይቆታል።

የእግዚአብሔርን ሠራዊት በአለቅነት የሚመራዉ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ኢያሱ ሙሴን ተክቶ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ በእግዚአብሔር የተሾመ ሆኖ ሳለ ኢያሱ ኢያሪኮን ድል ለማድረግ፣ ከነዓንን ለመውረስ ከአለቃው ከእግዚአብሔር ፊት ወድቆ መስገድና «ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው?» ብሎ ምሪትን መጠየቅ ነበረበት። ሁል ጊዜም የእግዚአብሔር ሕዝብ ዋና አለቃና መሪ እግዚአብሔር ስለሆነ በምድር መሪ ሆኖ የተሾመ ሰው በሰማይ ካለው መሪ ምሪትን መጠየቅ አለበት።

እግዚአብሔር የሠራዊት አለቃ ነው። የመላእክት ሠራዊት አለቃ ነው (መዝ 148:2)፣ የምድራዊ ሠራዊቱ (እስራኤላውያን) (ዘጸ 12:41) አለቃ ነው (1ሳሙ 17:26)። ሠራዊቱ በእርሱ ትእዛዝ ሥር ያሉ የእርሱን ፈቃድ የሚያደርጉ እርሱን የሚታዘዙ ናቸው። በሰማይ ያሉ ከዋክብት (መሳ 5:20) ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ በረዶ (ኢያ 10:11-14) ሁሉም ፍጥረታት በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር የሚተዳደሩ የእርሱ ሠራዊት ናቸው። ስለዚህ ኢያሱ ፈጥኖ ያስተዋለው ነገር የእስራኤል አለቃ እርሱ ራሱ ሳይሆን አለቃው እግዚአብሔር መሆኑንና እርሱ ደግሞ የአለቃው ባሪያ ማለትም የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን ነው።

በኢያሱ 6-11 እንደምንመለከተው እግዚአብሔር የሕዝቡ አለቃ ስለሆነ በእያንዳንዱ ጦርነት ኢያሱ ምን ማድረግ እንዳለበት፣ ኢያሪኮን፡- ስንት ጊዜ መዞር፣ መቼ መጮህ እንዳለባቸው፣ ጋይን ድል ለማድረግም ምን ማድረግ እንደሚገባቸውና ከዚያ በኋላ ለተደረጉት ጦርነቶች ሁሉ ዝርዝር መመሪያና ትእዛዝ ይሰጠዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ከሕዝቡ ጋር ያለው በመገኘት ብቻ ሳይሆን በአለቃነትም ነው።

**እግዚአብሔር የትኛውን የቤቱን ሥራ ማን ሊሠራለት እንደሚገባ እራሱ ይወስናል። እንደ ዳዊት ለቤቱ ሥራ ምሳሌውን (ራእይ) ከእግዚአብሔር የተቀበለ መሪ ቢሆንም እንኳ ቤቱን የሚሠራለት ደግሞ ዳዊት ሳይሆን ሰሎሞን ሊሆን ይችላል** (2ሳሙ 7:13)። መሪው በእግዚአብሔር ምንም ያህል የሚወደድ አገልጋይ ቢሆንና እንደ ዳዊት «የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚያገለግል» ቢሆንም እንኳ ገና ሥራው ሳያልቅ ወይም በተወሰነ የሥራ ደረጃ ላይ እያለ በእግዚአብሔር አንተ በቃህ ሊባልና ሊከለከል ይችላል። **የሥራው መሪ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሁሉ በሙሉ እውቀትና በጽድቅ ያደርጋልና**። ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ በምን መንገድ እንዳገለገለ ከሚከተለው ክፍል መገንዘብ ይቻላል፡-

> ንጉሡም ዳዊት በእግሩ ቆሞ እንዲህ አለ፡- ወንድሞቼና ሕዝቤ ሆይ፣ ስሙኝ፡- ለእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታቦትና ለአምላካችን እግር ማረፊያ ለዕረፍት ቤት ለመሥራት እኔ በልቤ አስቤአለሁ፣ ለሥራም የሚያስፈልገውን አዘጋጅቻለሁ፣ እግዚአብሔር ግን፡- የሰይፍ ሰው ነህና፣ ደምም አፍስሰሃልና ለስሜ ቤት አትሠራም ብሎኛል (1ዜና 28:2-3)

በማለት ለእግዚአብሔር ሊሠራው ያሰበው ነገር እጅግ መልካም ነገር ቢሆንም እንኳን እንዳልተፈቀደለት በልብ ቅንነት ይገልጻል። ልጁን ሰሎሞንን ደግሞ «እነሆ፣ እግዚአብሔር ለመቅደስ ለሚሆን ቤትን ትሠራ ዘንድ መርጦሃልና፣ ጠንክረህ ፈጽመው» (28:10) በማለት ሥራውን እግዚአብሔር ለመረጠው ያስረክባል፣ ያስተላልፋል። በእርግጥም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል እንዲህ ነው።

እግዚአብሔር በኢዩ አገልግሎት ደስ የተሰኘውና ለልጆቹም ተስፋ የሰጠው የልቡን ሀሳብ ስለ ፈጸመለት ነበር። «እግዚአብሔርም ኢዩን በፊቴ ቅን ነገር አድርገሃልና በልቤም ያለውን ሁሉ በአክዓብ ቤት ላይ አድርገሃልና ልጆችህ እስከ አራት ትውልድ ድረስ በእስራኤል ዙፋን ላይ ይቀመጣሉ አለው» (2ነገ 10:30)። እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ብድራቱን ይቀበላል።

ጌታ ኢየሱስ በምድር የሚያደርገው በአባቱ ዘንድ ሲደረግ ያየውን፣ የአባቱ ፈቃድ የሆነውን ነው። በአብና ወልድ መካከል ላለው ፍጹም የሆነ ግንኙነት አንዱ መገለጫ ወልድ የሚሠራውን ሁሉ ከአብ እያየ መሥራቱ ነው። አብ ደግሞ ወልድን ስለሚወደው ሁሉን ያሳየዋል። ጌታ ሲናገር «አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፣ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል» (ዮሐ 5:19-20) አለ። እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ «እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ፣ ፍርዴም ቅን ነው የላከኝን ፈቃድ

እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» ብሏል (ዮሐ 5:30)። በሌላም ስፍራ «አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ እንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ» (ዮሐ 8:28) ካለ በኋላ «እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና» (8:29) ብሏል። ስለዚህም እግዚአብሔር አብ በልጁ ደስ ብሎታል።

**እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፣ እረኛ ወይም መሪ የቤተ ክርስቲያንን እመራርና አገልግሎት በሚመለከት የራሱ የሆነ ሀሳብና የራሱ የሆነ ፈቃድ የሌለው ሰው ነው ማለት ይቻላል።** ጌታ ኢየሱስ «ፈቃዴን ለማድረግ እይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና» (ዮሐ 6:38) እንዳለ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የራሱ ፈቃድ ያደረገ ሰው ነው። ይህም የታዛዥነት ሕይወት ነው። ይህን ዓይነት የአገልግሎት ሕይወት እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚመጣ ነው። «... አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ አብም እንዳዘዘኝ እንዲሁ እደርጋለሁ ...» (ዮሐ 14:31) በማለት ጌታ ኢየሱስ በታዛዥነት እንደኖረና ይህም አብን የመውደዱ መግለጫ እንደሆነ ሁሉ አገልጋዩም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የተሰጠ መሆን አለበት።

አገልጋይ በሕይወቱ እግዚአብሔርን የሚያከብርበት አንዱ ትልቅ መንገድ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሥራ ምን እንደሆነ ለይቶ አውቆ ያችን ለመፈጸም ሲተጋና የራሱን ሀሳብ ሳይቀላቅልበት በንጹሕ ሲያገለግል ነው። ይህንም ከጌታ ሕይወት የምንማረው ዋና ነጥብ ነው። ጌታ ኢየሱስም «እኔ ላደርገው የሰጠኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» አለ (ዮሐ 17:4)።

መጽሐፍ ቅዱስ አማኞችን፡- «የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፣ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፣ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» (1ቆሮ 3:9) ይላል። የእርሻው ባለቤት እግዚአብሔር ነው። አጵሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ (3:5-7) እንደ ድካማቸው መጠን ደመወዝ የሚቀበሉ አገልጋዮች፣ ባርያዎች ናቸው (3:8)። የሕንፃው ባለቤት እግዚአብሔር ነው፣ የሕንፃውም መሠረት ክርስቶስ ነው (3:11)። አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ጋር አብረው የሚሠሩ ሠራተኞች ናቸው። «በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» (ዘካ 4:6) የሚለው የእግዚአብሔር ድምጽ ዛሬም ለቤተ ክርስቲያን ሕያው ነው። **ሰው ምንም ያህል ችሎታና ቅንነት ቢኖረው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ብቃት የለውም። የእግዚአብሔርን ቤት የሚሠራው ራሱ እግዚአብሔር ነው። አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ መጠመድ ነው፣ ከእርሱ ጋር በትሕትና መተባበር ነው።**

እግዚአብሔር የሠራው ሁሉ «መልካም» (ዘፍ 1) እንደነበረ ሁሉ **በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ የሚችልና ውጤቱ መልካም የሆነ ሥራ ራሱ እግዚአብሔር ሲሠራው ብቻ ነው።** እርሱ የሚሠራው ብቻ ነው «መልካም» የሚሆነው። ስለዚህ ከእርሱ ጋር ተባብሮ በሚሠራና እርሱን አድምጦ እንደተነገረው በሚፈጽም አገልጋይ መልካም ሥራ ይሠራል፣ መካሪውና መሪው እግዚአብሔር ሆኗልና።

በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ሽማግሌዎችን በመሾም (ሐዋ 20:17-18)፣ አገልጋዮችን ለእርሱ በመለየት (ሐዋ 13:2)፣ በአስቸጋሪ ጉዳዮች ውሳኔ በመስጠት (ሐዋ 15:28)፣ የአገልጋዮችን እቅድ በመፍቀድና በመከልከል (ሐዋ 16:6-10) ቤተ ክርስቲያንን መርቷል። እንዲሁም ጌታ ለቤተ ክርስቲያን

ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ የወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች (ኤፌ 4:11) ሰጥቷል። የእነዚህ አገልጋዮች ድርሻ የእግዚአብሔርን ሕያው መሪነት አውቀው በእርሱ ሥር በመሆን ፈቃዱን ማገልገል ነው።

በእርግጥ እግዚአብሔር ሕያው መሪ ነው። «የምናደርገውንም እናወቅም ነገር ግን ዓይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው» (2ዜና 20:12) ለሚሉት «ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና ... አትፍሩ (20:15) ይላቸዋል። «ልውጣን?» (2ሳሙ 5:19) ብሎ ለጠየቀው «ውጣ» (5:19)፣ «በኋላቸው ዞረህ ... ግጠማቸው» (5:23) ይላል። ሌሊቱን ሁሉ ለፍተው ምንም ዓሣ መያዝ ላልቻሉና ከንቱ ድካም ብቻ ለሆነባቸው፦ «ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ» (ሉቃ 5:4) ይላል።

እግዚአብሔርን ሳያማክሩ ከእርሱም ምሪትና ምክር ሳይጠይቁ መወሰን (ኢሳ 30:1-2) በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ አሠራር ነው። እንዲሁም «ልከኛውን ነፋስ» አይቶ መመራት (መምራት) «የመርከብ መሪዎች» ሥራ ነው (ሐዋ 27)። የእግዚአብሔር ሰው ግን ምንም ያህል ጉዞ ለመጀመር ነፋሱ ተስማሚ፣ ወቅቱ ለመንገድ አመቺ ቢሆንና ይህም በልምድ የታወቀ፣ እንዲሁም አሁን ካለበት ቦታና ሁኔታ ይልቅ የሚሄድበት ቢሻልም እንኳ በሚያየው ብቻ ያልተማመነ፣ እስቀድሞ እግዚአብሔርን የጠየቀ የአውራቂስን መኖር ወይም አለመኖር ማየት የሚችል ሰው ነው። ከብዙዎች «ባለ ሙያዎችና ባለ ሥልጣኖች» ምክር ይልቅ የእግዚአብሔርን ሀሳብ የተረዳ አንድ ጳውሎስ ይሻላል (ሐዋ 27:9-14)።

ስለዚህ በእግዚአብሔር መንፈስ በውዴታ ያልተነዳ ሰው በዓውሎ ነፋስ ፈቃድ ነፋስ ወደ ነፈሰበት ሁሉ ይነዳል (ሐዋ 27:15)። ነፋስ አይቶ መንገዱን የጀመረ (13) ከዚያ በሚበልጥ ታላቅ ነፋስ (20) ተስፋ ወደ መቁረጥ ይደርሳል። ሁኔታዎችን አይቶ የሚመራ ሰው ሁኔታው በተቀየረ ጊዜ የሚሄድበት ይጠፋበታል፣ ያከማቸውን ሁሉ ይጥላል። እግዚአብሔርን የሚያማክር ግን እንኳንስ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ከጀመረም በኋላ በባሕር መካከል ሆኖ በታላቅ ነፋስ ሊቸገር የእግዚአብሔር «አትፍራ» (27:24) የሚል ድምጽ ሊመጣለት ይችላል። እግዚአብሔር ያስጀመረውን መንገድ ያስጨርሳል፣ በመንገድም ያበረታል።

እንግዲህ በመንፈሳዊ አመራር የመጀመሪያው ነገር እግዚአብሔር ያሕዝቡ ሕያው መሪ መሆኑን ማውቅና ይህንን ሕያው መሪ በትጋት መከተል ነው።

### 14.2.2 «በተራራው እንደተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ»

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የማደሪያውን ድንኳን ምሳሌ (ዲዛይን) ለሙሴ ሲያሳየው «ማደሪያውንም በተራራ እንዳሳየሁህ ምሳሌ አቁም» (ዘጸ 26:30) እንዳለውና እንዳስጠነቀቀው (ዘጸ 25:40) እናነባለን። በአዲስ ኪዳን እስጢፋኖስ ስለ ማደሪያው ድንኳን ሲናገር «እንዳየው ምስል አድርጎ ይሠራት ዘንድ ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው የምስክር ድንኳን ከአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች» (ሐዋ 7:44) ብሎ ተናግሯል።

ሙሴ ለእግዚአብሔር ማደሪያ የሚሆን ድንኳን የሠራው የቀደሙት አባቶቹ እነ አብርሃም የነበራቸውን የድንኳን ዓይነት ወይም በሲና ምድር ያየውን ድንኳን አስመስሎ አልነበረም። ለእግዚአብሔር ማደሪያ ለሚሆን ድንኳን ምሳሌውን እግዚአብሔር ሰጠው እንጂ። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤት ለሚሆኑ እቃዎች ሁሉ ዝርዝር ምሳሌ ነበራቸው (ዘጸ 25:9፣ ዘኁ 8:4፣ ዕብ 8:5)። ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሥራ «ዳዊትም የሥራውን ሁሉ ምሳሌ አውቅ ዘንድ ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ተጽፎ መጣልኝ» እንዳለ (1ዜና 28:19) ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዴት ሊሠራ እንደሚገባው ዕቅዱን የሰጠው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ስለ ቤቱ ሥራ ይገድደዋል። ሙሴ የማደሪያውን ድንኳን ሥራ ከፈጸመ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር በድንኳኑ ውስጥ ስለሚፈጸመው የአምልኮ (የመሥዋዕት) ሥርዓት ዝርዝር ትዕዛዝ ሰጥቷል (ዘሌ 1-7)።

**በመንፈሳዊ አገልግሎት በምድር የሚከናወነው አገልግሎት አስቀድሞ በሰማይ በአብ ዘንድ የተደረገ ነው።** እግዚአብሔር በምድር የተፈጸመውን እይቶ እይደነቅም ወይም እይማርም፣ ምድር ከሰማይ ይማራል እንጂ፣ ምድር ከሰማይ መመሪያ ይጠይቃል እንጂ። የእግዚአብሔር ሥርዓት «ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» (ማቴ 6:10) የሚል ነው።

እግዚአብሔር ለእርሱ ለሚቀርብ አገልግሎት ሁሉ ምሳሌ አለው። ቤተ ክርስቲያን በምድር ለምትሠራው ሥራ ዲዛይኑ አስቀድሞ በሰማይ ይዘጋጃል (ተዘጋጅቷል)። በሰማይ ካለው እግዚአብሔር በሚቀበለው ምሳሌ መሠረት አስመስሎ በጥንቃቄ የሚሠራ አገልጋይ የጌታን ሀሳብ የሚያገለግል ሰው ነው። እግዚአብሔርን የሚያውቅና ከእርሱም ጋር የቀረበ ጎብረት ያለው አገልጋይ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሠርቶ ያለቀውን ምሳሌና የሥራ ዝርዝር ይቀበላል። የአገልጋዩ ድርሻ በሰማይ ተሠርቶ እንዳለቀው ሥራ አድርጎ መሥራት ነው። በእግዚአብሔር ፊጽሞ ይታመናል፣ ስለ አገልግሎቱ እግዚአብሔር ይናገረዋል፣ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ተከታትሎ ያደርጋል።

እግዚአብሔር አገልጋዮቹን በጥበብ የሚሞላቸው የእግዚአብሔርን ሥራ ከእርሱ ጋርና እንደ እርሱ ሀሳብ መሥራት እንዲችሉ ነው። «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ እይ ከይሁዳ ነገድ የሚሆን የሖር የልጅ ልጅ፣ የኡሪ ልጅ ባስልኤልን በስሙ ጠርቼዋለሁ በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም፣ በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት፣ የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ» (ዘጸ 31:1-4፣ 35:31)። በሌላም ሥፍራ «የናስንም ሥራ ሁሉ ይሠራ ዘንድ በጥበብና በማስተዋል በብልሃትም ተሞልቶ ነበር» (1ነገ 7:14) የተባለለት ሰውም ነበር። እንዲሁም «ኢያሱ የጥበብን መንፈስ ተሞላ፣ የእስራኤልም ልጆች ታዘዙለት እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ» (ዘዳ 34:9)።

ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚያውቅ መንፈሳዊ መሪ ስለ ሥራው እግዚአብሔርን የሚጠይቅና እርሱን የሚያደምጥ ሰው ነው። የቤተ ክርስቲያን ሥራ የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ በመሆኑ እግዚአብሔርን የሚያደምጥ በእግዚአብሔር ጥበብ ሕዝቡን ጥሩ ይመራል። በመሠረቱ የቤተ ክርስቲያን አመራር ለሰዎች የተተወ ሥራ አይደለም። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በሥራው ይተባበራሉ እንጂ።

ሠራተኛው ግን ራሱ እግዚአብሔር ነው። «አግዚአብሔር እስከ ዛሬ ይሠራል» (ዮሐ 5:17)።

ለመልካም አገልጋይነት አንዱ ትልቅ መስኪያ እንደ ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ነው። እግዚአብሔር በሀሳቡ ብርቱ ነው ፈቃዱንም ያደርግ ዘንድ ይተጋል። «በመጀመሪያ መጨረሻውን ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ፣ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ» (ኢሳ 46:10)።

ንጉሡ ሰሎሞን ወደ መንግሥት በመጣ ጊዜ እግዚአብሔርን የለመነው «በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ መልካሙንና ክፋውንም ይለይ ዘንድ ለባሪያው አስተዋይ ልቡና ስጠው፣ አለዚያማ በዚህ በታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል?» (1ነገ 3:9) ብሎ ነበር። የሰሎሞን ልመና ትክክለኛውን ስህተት ከሆነው መለየት የሚቻለው እግዚአብሔር በሚሰጠው ጥበብና ማስተዋል እንደሆነ ያሳያል። እንዲሁም ምንም እንኳ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር ቢፈቅድለትም ንጉሡ ሰሎሞን የሚመራው ሕዝብ ግን ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆነ ያውቃል። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት የሚችለው እግዚአብሔር በሚሰጠው ጥበብ ነው።

የእግዚአብሔር መልስ ለሰሎሞን «ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ» (2ነገ 3:12) የሚል ነበር። ይህ በጌታ ኢየሱስ ላይ «የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል» (ኢሳ 11:2) ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ የጻፈው ነው። «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና» (ቆላ 2:3)።

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ከራሴ ምንም ላደርግ አልችልም ብሏል (ዮሐ 5:30)። የሚያደርገውም አባቱ ሲያደርግ ያየውን ነው (ዮሐ 5:19)። የሚናገረውም እግዚአብሔር አብ እንዲናገር የሰጠውን ነው (ዮሐ 8:28 እና 7:16-18)። ስለዚህ የትክክለኛና ጤናማ አገልግሎት መለኪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግና የራስን ፈቃድ በማገልገል መካከል ያለውን ልዩነት አውቆ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማገልገል በመምረጡ ላይ ነው።

እግዚአብሔር መንገድን የሚያሳይ መሪ፣ ብልሃትን የሚሰጥ አስተማሪ ነው። ለናስ ሥራ (የእጅ ሙያ) ብልሃትን የሚሰጥ እግዚአብሔር የእውቀት ሁሉ ባለቤት ነውና፣ ለገበሬም «ብልሃት አምላኩ ያስታወቀዋል ያስተምረውማል» (ኢሳ 28:26) እንደተባለ ክቃሉ እናነባለን።

እዚህ ላይ ለእያንዳንዱ ውሳኔና እርምጃ ከእግዚአብሔር በቀጥታ ልዩ መገለጥ እንዲመጣ መጠባበቅ ማለት አይሆንም። ለሚያስተውል ሰው እግዚአብሔር የሚናገርበት መንገድ ብዙ ነው። ዋናው ማስሪያ ሀሳብ ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በመሪነት ላይ ያለ ሰው የሚያደርገውን ውሳኔና የሚወሰደው እርምጃ ሁሉ የእግዚአብሔር ሀሳብ መሆኑን በመረዳትና እንደ ቃሉ የሆነ በእግዚአብሔር አስቅነት ሥር የተወሰደ እርምጃ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አረኛ ወይም መሪ ወይም ሌላ አገልጋይ የራሱ የሆነ ራእይ ወይም ዕቅድ የለውም። ራእዩ ከእግዚአብሔር የመጣ ከሆነ የእግዚአብሔር

ራእይ ነው። ነህምያ «እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም አደርገው ዘንድ በልቤ ያኖረውን» (ነህ 2:12) እንዳለ ስለ ሥራው እግዚአብሔር በሰው ልብ ውስጥ የሚያስቀምጠው ይህ የእግዚአብሔር ራእይ ነው። ያለበለዚያ የሰው ሀሳብ ይሆናል፣ በሰው ዘንድ ደግሞ ብዙ ምኞት አለ (ምሳ 19:2)።

በመሠረቱ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎትን በሚመለከት መሪው ወይም እረኛው «የእኔ ራእይ» የሚለው ሊኖረው አይገባም። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት፣ ለቤቱ ሥራ የሚሆንን ራእይ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም እርሱ ሊሰጠው ራእይ እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንዳለበት ሰዝርዝር ተግባሩ (አፈጻጸሙ) ማስተዋልን ይሰጣል (1ዜና 28:19) ። «ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?» ብሎ የሚጠይቅ እግዚአብሔር የሚልከና ባለ መልእክቱ እርሱ ነው፣ አገልጋዩ ደግሞ የሚላክ ለው ወይም መልእክት አድራሽ ነው፣ የመልእክቱ ባለቤት አይደለም።

ይህ እንዲህ ከሆነ እንግዲያውስ የመሪ ድርሻው እግዚአብሔር እንደገለጠለት ወይም በልቡ እንዳኖረው ለመሥራት መነሣት፣ ለሥራውም የሚያስፈልገውን ጥበብ የጥበብ መዝገብ ሁሉ የእርሱ ከሆነው ከእግዚአብሔር መለመን፣ ሥራውን ለማከናወን ኃይልና ብርታትን ከእርሱ በመቀበል በትጋት መሥራት ነው።

## 14.2.3 የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር

### ሀ. እግዚአብሔርን የሚከተል መሪ

አመራርን በሚመለከት ብዙ ጊዜ የሚጻፈው ስለ መሪዎች የአመራር ዘይቤ ነው። ይህም ከባሕሪያቸው ጋር የተገናኘውንና እንዴት አድርገው ሕዝብን (ጉባኤን) እንደሚመሩ የሚያመለክት ነው። የዚህ ንዑስ ክፍል ትኩረት ደግሞ በመንፈሳዊ መሪነት መርሆዎች ላይ ነው። የመንፈሳዊ መሪነት ቁጥር አንድ መርሆ እግዚአብሔር የሕዝቡ መሪ እንደሆነ ማወቅና ይህንም በተግባር መለማመድ ነው።

የእግዚአብሔር ቤት አመራር በምድር ከሚገኙ ማናቸውም ዓይነት ማኅበራት ወይም ድርጅቶች አመራር የተለየ ነው። ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ስለሆነች ራስ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላት ግንኙነት ሕያው ነው። ቤተ ክርስቲያን የምትመራው ምዕመኑ በመረጣቸው መሪዎች ወይም ከሕዝቡ በውክልና ተሾመው የበላይ በሆኑ አለቆች ሳይሆን በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በእግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር ለከብሩ የጠራውን ሕዝብ የአመራር ዘይቤ በምድር ከሚታየው አስተዳደር ጋር ማመሳሰል የእስራኤላውያን ናፍቆት ነበር። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሥርዓት ንቀው የአሕዛብን አስተዳደር ተመኙ። «እኛ ደግሞ እንደ አሕዛብ ሁሉ እንሆናለንና» (1ሳሙ 8:20) ብለዋል። ይህንም በማለታቸው እግዚአብሔር በመረጠው መሪ፣ መስፍን ወይም ነቢይ ከመመራት ይልቅ በንጉሥ መመራትን መረጡ። ያም ሆኖ ጌታ እንዲህ ይላቸዋል፦

አሁንም የመረጣችሁትንና የፈለጋችሁትን ንጉሥ እዩ፣ እነሆም፣ እግዚአብሔር ንጉሥ አደረገላችሁ። እግዚአብሔርን ብትፈሩ ብታመልኩትም፣ ቃሉንም ብትሰሙ በእግዚአብሔርም ትእዛዝ ላይ ባታምፁ፣ አናንተና በአናንተ ላይ የነገሠው ንጉሥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ብትከተሉ፣ መልካም ይሆንላችኋል (1ሳሙ 12:13-14)።

ስለሆነም እግዚአብሔር ከልባቸው ድንዳኔ የተነሣ እራሳቸው እስራኤላዊያን ንጉሥ መርጠው እንዲሾሙ ቢፈቅድላቸውም እግዚአብሔርን በመፍራት ከኖሩ ያ እነርሱ የሚመርጡት ንጉሥ እግዚአብሔርም የመረጠላቸው ይሆናል።

የእግዚአብሔርን ምሪት በጥንቃቄ የማይከተል መሪ በዓይን በሚታይና በሚሰማው ማለትም በአጠቃላይ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ብቻ የሚመራ መሪ ነው። እንዲህ ዓይነቱ መሪ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲኖር ማስተዋል የጐደለውና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሸክም የሚጨምር ይሆናል። በኢያሱ ምዕራፍ 9 የምናነበው ኢያሱ ከገባዖን ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን የገባው በዓይኑ አይቶ በተገነዘበውና ሌሎችም አብረውት ያሉት በሙሉ ድምፅ በሚያረጋግጡት ጉዳይ ላይ ነበር። ግን «እግዚአብሔርንም አልጠየቁም» (ኢያ 9:14)። ስለሆነም መንፈሳዊ መሪ እግዚአብሔርን የሚሰማና የሚከተል ሊሆን ይገባዋል።

## ለ. ተጠያቂነት

እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ ይቀርባል። «እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን» (ሮሜ 14:12) እንደሚል መሪዎች ስለሚያገለግሏቸው ሰዎች ነፍስ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት አለባቸው (ዕብ 13:17)።

አገልጋዮች ስለ ሥራቸው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደሚቀርቡ አውቀው (2ቆሮ 5:10) ለሚያገለግሉትም ምእመን ተጠያቂ መሆናቸውን ተረድተውና ኃላፊነት ተሰምቷቸው፣ በማስተዋል ማገልገል ይኖርባቸዋል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተጠያቂነት ወደ ላይ ለእግዚአብሔር ወደ ጎን ደግሞ ለወንድሞቻቸው (ለምዕመናን) ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች *ተጠያቂነት* የማይወዱት የተጠያቂነት አሠራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ ሳይሆን ተጠያቂነት ለሥልጣን እጠቃቀም፣ ለገንዘብና ንብረት እያያዝ ወሰን ስለሚያበጅባቸው ነው።

ግልጽነት በሌለበት አሠራር ውስጥ ውሎ አድሮ ችግር መከሰቱ አይቀርም። ከግልጽነት መጉደል የሚነሣው ችግር ደግሞ የአገልጋዩን ሕይወት በእጅጉ የሚጐዳ ይሆናል። ሰው ደግሞ «ምቹ ሁኔታ» ሲያገኝ የተቆረጠው ጉቶ ሳይቀር ያቆጠቁጣል። ለዚህ የማሻለው ማንም ሰው «ደምና ሥጋ» መሆኑን ሳይዘነጋ በግልጽነት ለመሥራት መድፈር አለበት። ከተጠያቂነት አለመሸሽ ይገባዋል። በቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር ውስጥ የተጠያቂነት አሠራር እንዲኖር መደረጉ የሰውን ባሕርይ በመለወጥ ፈጽሞ ከችግር ነፃ ያደርገዋል ባይባልም፣ የችግርን ብዛት ግን ያለ ጥርጥር ይቀንሳል፣ በአገልጋዩም ላይ ሊመጣ የሚችለውን ስብራት ያስቀራል፣ ከብዙ ጥፋትና አደጋም ይከላከላል።

## ሐ. በጎብረት ማገልገል (የቡድን መሪነት)

በቤተ ክርስቲያን አመራርና አሠራር ምን ጊዜም ቢሆን ከአንድ ሰው ብቸኛ መሪነት ይልቅ በጎብረት፣ በመመካከርና በመደጋገፍ የሚደረግ የቡድን (የወል) አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ፣ ውጤታማና መጨረሻው የሚያምር መሆኑን በመገንዘብ፣ መሪዎች አገልግሎታቸው የጎብረት አገልግሎት እንደሆነ ሊገነዘቡት ይገባል። የአንድ ሰው አመራር ከምእመናኑ ተነጥሎ ብቻውን የቆመን የአንድ መሪን ብቸኛ መሪነት ያመለክታል። በእንዲህ ዓይነት አመራር ሰውየው እግዚአብሔርን የሚፈራና «ሁሉን ትተን ተከተልንህ» የሚል ክሆነ ባልከፋም ነበር። ግን ብዙ ጊዜ በብቸኛ አመራር ያለው ችግር «ሁሉን መተው» ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን የራስ፣ የግል ሀብት (ንብረት) አድርጎ ወደ መቁጠር ማዘንበል ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ የሚያነጋግሩ፣ የተለያዩ አመለካከት የሚያስነሱና ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት የሚያዳግቱ ጉዳዮች ቢነሱ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በመቅረብ፣ በፍቅር በመሆንና እርስ በርስ በመመካከር ለችግሮቹ መፍትሔ ለማግኘት የጎብረት መሪነት አስፈላጊ ይሆናል።

## መ. ውሳኔ አሰጣጥ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጎብረት የሚሰጥ ውሳኔ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመስማማት መሆን አለበት። ውሳኔውም የእርሱ ነው። እኛ ከእርሱ ሀሳብ ጋር ተስማምተን እርሱ ያለውን ከእርሱ ጋር አብረን የምንል መሆን አለብን። በኢየሩሳሌም ሐዋርያት፣ ሽማግሌዎችና ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ሆነው «እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና» እንዳሉት (ሐዋ 15:28) ነው። ሆኖም ወደ ውሳኔ ከመድረሳቸው በፊት ብዙ ክርክር (ሐዋ 15:6) እንደ ነበረ እናነባለን። ክርክሩ ይብዛ፣ ጊዜም ይውሰድ እንጂ ሐዋርያት፣ ሽማግሌዎችና ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የሀሳብ አንድነት ላይ ደርሰዋል (15:22)። **መንፈስ ቅዱስ እንዲመራ በተፈቀደለት ጉባኤ የሀሳብ ስምምነት፣ የልብ እንድነት ይኖራል፣ ወደሚፈለገው ውሳኔም ይደረሳል።**

ብዙኀኑ በድምጽ ብልጫ የደገፈውን ሀሳብ ውሳኔ አድርጎ መቀበል በብዙ ቦታ የተለመደ አሠራር ነው። «የለለጠነው ዓለም» የሚጠቀምበት የውሳኔ አሰጣጥ መንገድ ነው። ይህ አሠራር የሚያመለክተው ብዙኀኑ የሚፈልገው ውሳኔ የተሻለ ሀሳብ ነው፣ ክአናሳው ቁጥር ይልቅ አብላጫ ድምጽ ያለው ወደ ትክክለኛነት የቀረበ ነው የሚል ነው። እንዲሁም ጊዜን ለመቆጠብ ይጠቅማል። በአሁኑ ዘመን ይህ ዓይነቱ አሠራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብዛት እንደሚሠራበት ይታወቃል። አሠራርን ያቀላጠፈ. ቢሆንም በታሪክና በዘመናችንም፣ «የፊት ኃፍረት» የሆኑ ውሳኔዎችም ተላልፈው ይታወቃል።

አብላጫ ድምጽ ያለው ሀሳብ ሁልጊዜ ትክክለኛ ነው ማለት አይቻልም። እንዲያውም በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መሠረታዊ (ወሳኝ) የሆኑ ጉዳዮች በቁጥር ጥቂት በሆኑ ሰዎች የያዙት ሀሳብ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ክነዓንን ሰልለው የመጡት ሰዎች ሁሉም እስራኤላውያን ነበሩ። ሁሉም የወገን አለቆች ነበሩ። የአርባ ቀን የስለላ ሪፖርታቸው ተመሳሳይ

ነበር። ሆኖም ውሳኔው አሥር ለሁለት (10 ለ 2) የሆነ አብላጫ ድምፅ ነበረው። ከዚያም አልፈው የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ አግኝተዋል። እግዚአብሔር ግን ከአሥሩ ጋር አልነበረም። ከብዙኃኑ ይልቅ ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ «ልዩ መንፈስ» ነበራቸው ወይንም እግዚአብሔርን ያውቁት ነበር።

በሐዋ 27:37 እንደምናነበው በመርከብ ውስጥ ከነበሩት ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ነፍስ (ለምች) ለጉዞ አመቺ በሚመስለው ሁኔታ ያልተታለለው ጳውሎስ ብቻ ነበር። ለምች ሁሉ «እንዳሰቡት የሆነላቸው መስሎአቸው ተነሡ» (27:13)። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ አድማጭ አላገኘም። ሁለት መቶ ሰባ አምስት ለአንድ (275:1) በሆነ እጅግ ከፍተኛ ድምጽ ነበር የተሸነፈው። ግን ብዙ ሳይቆይ ክደረሰባቸው ነገር የተነሣ ተስፋ ሁሉ ሲቆረጥ ጳውሎስ የሚላቸው «እናንተ ለምች ሆይ ለምታችሁኝ በሆነ ኖሮ ከቀርጤስ እንዳትነሡ ይህንም ጥፋትና ጉዳት እንዳታገኝ ይገባችሁ ነበር» (27:21)።[87] እንግዲህ በቤተ ክርስቲያን አመራር ጥያቄው አብዛኛው ሕዝብ የደገፈው ሀሳብ የትኛውን ነው ሳይሆን እግዚአብሔር ከነማን ወገን ነው ያለው? ወይም የትኛው ሀሳብ ነው ከእግዚአብሔር የሆነው? የሚል መሆን አለበት።

«ከባድ» የሆነ ነገርን በድምፅ ብልጫ ቶሎ መቁረጥ ይቻላል። ጉዳዩ የብዙ ደጋፊ ድምፅ የበዛለት ነገር ሆኖ ሳለ ግን እግዚአብሔር የሌለበት ውሳኔ ሊሆን ይችላል (ዘጸ 23:2)። የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚጠብቅና የወንድማማች መዋደድን የሚያጠናክረው ውሳኔው በአንድ ልብ ወይንም በመግባባት ሲደረግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ርዕስ ላይ የተነሣን ወይይት በድምጽ ብልጫ ከመቁረጥ ይልቅ ጉዳዩን በይደር አቆይቶና የወንድማማችን ፍቅር፣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ጠብቆ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ጥሩ መፍትሔ ነው። እንግዲህ ነገሩ ምንም ያህል በለው ዓይን ከባድና አስቸጋሪ ቢሆንም በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት ለሚቀርቡ «እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል» (ፊሊ 3:15) እንደተባለው እግዚአብሔርን በትዕግሥት ለሚጠብቁ እርሱ ይገልጥላቸዋል።

እግዚአብሔር በቤቱና በሕዝቡ በእያንዳንዱ ጉዳይ ያገባዋል። ቤቱም የእግዚአብሔር ነው፣ ሕዝቡም የእግዚአብሔር ነው። በሙሴ ሕግ አንድ ሰው ለሚፈጽመው የበደል ዓይነት ምን መደረግ እንዳለበት በዝርዝር የተገለጸ ቢሆንም አንድ ቀን ግን በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም ላገኙት ሰው ምን ማድረግ እንዳለባቸው በሕጉ አላገኙምና ስለዚህ «ያደርጉበትም ዘንድ የሚገባው አልተገለጸምና በግዞት አስቀመጡት» ይላል (ዘኁ 15:34)። እንዲሁም «የእግዚአብሔርን ስም የለደበውንና» የአቃለለውን ሰው «ከእግዚአብሔርም አፍ ስለ አርሱ ፍርድ እስኪወጣላቸው ድረስ በግዞት አኖሩት» ይላል (ዘሌ 24:12)። በሌላም ጊዜ ከሙሴ ፍርድን የሚፈልጉ ሰዎች በቀረቡ ጊዜ ስለ ጠየቁት ጉዳይ በሕጉ መጽሐፍ አልነበረምና ለእነዚህ ሰዎች የሙሴ መልስ «እግዚአብሔር ስለ እናንተ የሚያዝዘውን እስክሰማ ድረስ ቆዩ አላቸው» (ዘኁ 9:8)።

ይህ ዘመን ራሱ ሙሴ በሕይወት ከሕዝቡ ጋር የነበረበት ጊዜ ቢሆንም እንኳ ሙሴም ሆነ ሕዝቡ የራሳቸውን እርምጃ አልወሰዱም፣ ወይም አጥፊዎችን «በተዛማጅ አንቀጽ» አልዳኙአቸውም። እግዚአብሔር እስኪመልስላቸው ይጠብቁ

[87] እንዲሁም በ1ነገ 22:4-40 ያለውን ታሪክ ይመልከቱ።

ነበርና። እግዚአብሔርን ስለ ጠበቁበት ነገር ደግሞ «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ...» ተብሎ ተጽፎአል (9:9)። ይህን ዓይነት አሠራር **ነገርን በግዙት የማቆየት ወይም በጸሎት መጠባበቅ** ልንለው እንችላለን። እግዚአብሔር ለዚህ ዓይነት በደል ፍርዱ ምን ሊሆን እንደሚገባ ተናገራቸው (16:35)። እግዚአብሔርን ለሚጠይቅ መልስ ይሰጠዋል። እንግዲህ **መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ «በተዛማጅ እንቀጽ» ላለመዳኘት ጥንቃቄ ማድረግ ነው። እግዚአብሔር ሕያው መሪ ነውና ዛሬም እርሱን የሚሰሙ መሪዎችን ቢያገኝ እርሱ ይናገራቸዋል፣ ይመራቸዋል።**

ይህ እግዚአብሔርን የመጠየቅና እርሱን የመስማት፣ እስኪናገርም ድረስ ውሳኔን የማቆየት የሙሴ አመራር አንድ ትልቅ ባሕርይ ነው። እንደ ሙሴ ሰትልቅ መሪነት የተጠራ መሪ እግዚአብሔር የሚለውን ያዳምጣል፣ እስኪናገርም ደግሞ ይቆያል፣ ይጠብቃል። ዳዊት ሰሎሞንን «እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና የአባትህን አምላክ እወቅ፣ በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው ብትፈልገው ታገኘዋለህ ብትተወው ግን ለዘላለም ይጥልሃል» (1ዜና 28:9) እንዳለው እግዚአብሔር ለሚፈልጉት ይገኝላቸዋል።

**«እረኞች ሰንፈዋልና፣ እግዚአብሔርን አልጠየቁምና፣ አልተከናወነላቸውም መንጎቻቸውም ተበትነዋል»** (ኤር 10:21)። እግዚአብሔርን የማይጠይቅ አረኛ መንጋው ይበተንበታል፣ ሕዝቡንም ይሸነግላል (ኤር 9:6)። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚመራው በእግዚአብሔር ድምጽ ነው፣ መንጋውም የእግዚአብሔርን ድምጽ ይለያል (ዮሐ 10)።

## ሠ. መመካከር (ምክር መስማት)

አገልጋይ የራሱን አስተሳሰብና መንገድ ብቻ ትክክለኛ አድርጐ እንደሚቆጥር ሰነፍ ሰው ሳይሆን ማንም ሰው መሪዎችን ጨምሮ ***ከመታረም በላይ አለመሆናቸውን በመገንዘብ*** የወንድሞችን ምክር የሚሰሙ ጥበበኞች መሆን ያስፈልጋቸዋል (ምሳ 12:15፣ 13:10)። የእግዚአብሔር ሰው በተለይም በመሪነት ቦታ ያለ ሰው የቅዱሳንን ምክር ለመስማት የተዘጋጀ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ነቢይ ንጉሡን «ነቢዩም ይህን አድርገሃልና፣ ምክሬንም አልሰማህምና እግዚአብሔር ሊያጠፋህ እንዳሰበ አወቅሁ ብሎ ተው» (2ዜና 25:16) እንዳለው ምክርን ለመስማት ፈቃደኛ የማይሆን ራሱን ለእግዚአብሔር ቅጣት ያዘጋጀ ሰው ነው።

ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔር ማስተዋልን ሰጥቶታልና ጥበበኛ ሰው ነበር። ይህ ጥበበኛ የሆነ ሰው «ጠቢብ ... ከመስማት ጥበብን ይጨምራል፣ አስተዋይም መልካም ምክርን ገንዘቡ ያደርጋል» (ምሳ 1:5) ይላል። አስተዋይ ሰው ምክርን የሚሰማ ሰው ነው። ምክርንም የሚሰማ ሰው የእርሱን የራሱን ሀሳብ ከሚደግፉ ወይም እንደ እርሱ ዓይነት አስተሳሰብ ካላቸው ብቻ ሳይሆን እውነትን ከያዙ ከሌሎች («ከተቃዋሚዎች») ለመስማት የማይታክትና ምክርን የሚፈልግ ሰው ነው፤ ምክንያቱም ማስተዋልን ለማብዛት ምክር መስማት መልካም ነውና።

ንጉሥ ሰሎሞን ራሱ ጠቢብ ሆኖ ሳለ በፊቱ የሚቆሙ ሽማግሌዎች (መካሪዎች) ነበሩት። «ለዚህ ሕዝብ እመልስለት ዘንድ የምትመክሩኝ ምንድር ነው?»

በማለትም እንደጠየቃቸው በ1ነገ 12:6 እናነባለን። ልጁም ሮብዓም እንደ አባቱ ሁሉ እነዚህን ሽማግሌዎች ምክር ሊጠይቅ ይጀምራና «እርሱ ግን ሽማግሌዎች የመከሩትን ምክር ትቶ ከእርሱ ጋር ካደጉትና በፊቱ ይቆሙ ከነበሩት ብላቴኖች ጋር ተማከረ» (12:8)።
ምክር መጠየቅ በአስተዋይነት የመጀመሪያው እርምጃ ሲሆን ምክርን መስማት ደግሞ ማስተዋል ነው። ሮብዓም ምክርን ጠየቀ ግን መልካም ምክርን ተወ (ጣለ)። ሮብዓም የሽማግሌዎችን ምክር ከመስማት ፊቱን ሲያዞርና የራሱን ዓይነቶች (ቢጤዎቹን) ሲሰማ በእነርሱም ምክር ሲመራ እናያለን። የመከሩት መልካም አልነበረምና ውጤቱም አላማረም።

የበለሱና በእድሜ የገፉ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር በሕይወታቸው ዘመን ብዙ ያስተማራቸው ስለሚሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ነገሮችን በልብ ስፋት የሚመለከቱና መልካም ምክር ያላቸው ይሆናሉ። እነዚህን ሰዎች ማድመጥ ይገባል።

የእግዚአብሔር ቃል «ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው» (ምሳ 24:6)፣ እንዲሁም «... በመልካምም ምክር ሰልፍ አድርግ» (20:18) ይላል። ቤተ ክርስቲያን ከኃይላት ከአለቆች ከሥልጣናት ከመንፈሳውያን ሠራዊት ሁሉ ጋር ሰልፍ አለባት። በዚህ ሰልፍ ድል ለማግኘት ከሁሉ በማስቀደም ድንቅ መካር ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ምክርን መጠየቅና መስማት ይገባታል። እንዲሁም ወንድሞች የመንፈስ አንድነትን መጠበቅና እርስ በርስ መመካከር ይገባቸዋል። በቤተ ክርስቲያን አመራር ቦታ ላይ ያሉ አገልጋዮች የአመራር ጉባኤው አባላት ከሆኑት ጋር ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከቆዩ ወገኖች፣ በአገልግሎት ካሉትና ከሌሎችም ሁሉ ምክር መስማት ይጠቅማቸዋል። እንግዲህ እርስ በርስ በመመካከር መወሰን አስተዋይ መሆን ነው። ይህም ሲሆን በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ሁልጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማማከር፣ ወደ እርሱ በመምጣት ምሪትን መጠየቅ በመልካም መካሪዎች ምክር የሚተካ አይደለም።

## ረ. ቅንነት

ዳዊት አሪዮንን «ወደ ቤትህ ሂድ፣ እግርህንም ታጠብ» ሲለው (2ሳሙ 11:8)፣ ሄሮድስ የሰገልን ሰዎች «እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት» ሲላቸው (ማቴ 2:8)፣ ይሁዳ «ሽቶው ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠው ስለ ምንድን ነው?» ብሎ ሲጠይቅ (ዮሐ 12:5) ሁሉም በቅንነት አልነበሩም። ሁሉም እንደ ሰው አስበዋል፣ እንደ ሰውም በዘዴ መናገራቸው ነበር። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ግን በላይ በሰማይ አለ። እንግዲህ የመሪዎች አገልግሎት ልብን በሚያየው በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት መሆን አለበት።

## ሰ. ሪፖርት

ለቤተ ክርስቲያን *ሪፖርት* ማቅረብና እግዚአብሔር የሠራውን መናገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው (ሐዋ 14:27፣ 15:4፣ 21:19)።

## 14.2.4 ለለውጥ የተዘጋጀ አሠራር

እግዚአብሔር የማይለወጥ ለዋጭ ነው። ነገሥታት ይነሣሉ ይወድቃሉ፣ አለቆች ይሾማሉ ይሻራሉ። እግዚአብሔር ግን ለዘላለም በዙፋኑ ጸንቶና ተፈርቶ ይኖራል። ይህ የማይለወጥ እግዚአብሔር፣ ይህ የዘላለም አምላክ እግዚአብሔር ሥራውን በቀናት፣ በወራት፣ በዓመታት ውስጥ ይሠራል። የታሪክ ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር አርሱ ክታሪክ በላይ ሆኖ ታሪክን ይሠራል።

ለውጥ[88] እንቅስቃሴን፣ ሂደትን፣ እድገትን ያመለክታል። አደረጃጀትን በሚመለከት ለውጥ ዓላማን በተሻለ ሁኔታ ለማሟላት የሚያስችል የአሠራር ሥልትን መቀየስና አደረጃጀትን ማስተካከል ነው።

ብዙ ጊዜ ለውጥን በቀላሉ የሚቀበል የለም። የቀደመውን አሠራር የሚያውቁና የተለማመዱ ደግሞ አዲስ አሠራርን አይፈልጉም፣ «አሮጌው ይጣፍጣል ይላሉና» (ሉቃ 5:39)። ይሁን እንጂ አንዳንድ አሠራሮች ያረጃሉ፣ ጠቃሚነታቸውም ይቀንሳል፣ ወደ ተፈለገው ውጤት የማያደርሱ ይሆናሉ።

ጌታ እግዚአበሔር በብሉይ ኪዳን በሙሴ አማካኝነት ሕግንና የቤተ መቅደስን ሥርዓት ሰጠ። ይህ ሥርዓት በጊዜው ከሰማይ የተሰጠ ለማያዊ ሥርዓት ነው። ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ አዲስ ኪዳን ሲመጣ የቀደመው «ውራጅ» (ዕብ 8:13) ሆነ። ምንም እንኳ የቀደመው ሥርዓት በዘመኑ የከበረ ቢሆንም ዋናው ሲመጣ የቀደመው ያረጃል። «ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል» (ዕብ 10:9)። የቤተ ክርስቲያን የአመራርና የአሠራር ዘይቤም ከዚህ የሚወሰደው ምሳሌ ወይም ትምህርት ይኖረዋል።


ይህም ሆኖ ሳለ የእግዚአብሔር ቃል ግን አያረጅም። የእግዚአብሔር ባሕርይ አይለወጥም። በብሉይ ኪዳን የነበረ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳንም ያው እግዚአብሔር በሙሉ ኃይሉ፣ በእርሱነቱ፣ በሙላት ያለ ነው። እርሱ ለዘላለም ያው ነው። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረጉ የአሠራር ለውጦች «አሠራር ልዩ ልዩ» (1ቆሮ 12:6) በመሆኑ ለዘመኑና ለሁኔታው የተሻለ አሠራር ከመምረጥ አንጻር እንጂ በመሠረቱ በቤተ ክርስቲያን የማንነት (የምንነት)፣ የዓላማ ለውጥ አይደረግም። ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ቢሆን መልኳን አትቀይርም። እርሷ ሕያው የክርስቶስ አካል የሆነች፣ በእርሱ መሪነት ሥር የምትኖር፣ በቃሉ የተገለጸውን ፈቃዱን ለማድረግ የተጠራች ነች። አነዚህ ነገሮች አይለወጡም።

√ በአሁኑ ዘመን *የቤተ ክርስቲያን አመራር* ሁለት ነገሮችን ያገናዘበ መሆን አለበት።
1. ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ መሆን፣
2. ለዘመኑ ወይም ከቤተ ክርስቲያን እድገት ጋር የሚስማማ የአሠራር ዓይነት።

**አንዳንድ አሠራሮች ለዘመኑ «የሚስማሙ» እና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሆነው ሳሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ አሠራሮቹ ለቤተ ክርስቲያን**

[88] በዚህ መጽሐፍ ለውጥ የሚለው ቃል የተተረጎመው ወደ ተሻለ እድገት ለመድረስ የሚደረግ ጤናማ አንቅስቃሴ ተብሎ ነው።

ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም። በሌላ በኩል ደግሞ አሠራሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሆነው ሳለ ለዘመኑ የማይስማሙ ቢመስሉም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ምርጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መንገድ መከተል ነው። ሁልጊዜም «ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው። ከምድር የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል» (ዮሐ 3:31)። ይህን ሀሳብ ቀለል ባለ መንገድ እንደሚከተለው በሥዕል መገለጽ ይቻላል።




ሀ = መጽሐፍ ቅዱሳዊ
ለ = የዘመኑ የአሠራር መንገድ
ሐ = የዘመኑ አሠራር ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አሠራር ጋር ሲስማማ

በሥዕሉ እንደምንመለከተው ትክክለኛው የቤተ ክርስቲያን አመራርና አሠራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የ «ሀ» ክብ የሚያሳየው ነው። በ «ለ» ክብ ውስጥ ያለው የተለያዩ «ዘመናዊ» የአሠራር ስልቶችና መንገዶች ናቸው። የ «ለ» ክብ በ «ሀ» ክብ ውስጥ ገብቶ «ሐ»ን ሲሰጥ አሠራሩ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ወይም የማይቃረን የአሠራር ስልቶችን የሚጠቀም በመሆኑ ጥሩ አሠራር ይሆናል።

ትክክለኛው መመሪያ «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠንን እምነት» ከሚገልጸው (ይሁዳ 3) ይገኛል። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው። የቤተ ክርስቲያን ዓላማ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋፋት ነው፣ አሠራሩም ለማያዊ ነው። እግዚአብሔርን በማክበር በፍቅር ላይ የተመሠረተ አሠራር ነው።

ስለዚህ የወይን ጠጁን ክወይን አቁማዳው (ሉቃ 5:37-38) መለየት ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን አሠራር የወይን አቁማዳው ያረጀ ከሆነና ለአዲሱ የወይን ጠጅ የማይስማማ ሆኖ ከተገኘ አቁማዳው ይቀየራል፣ የወይን ጠጁ ግን ያው ነው። የማያረጀው የእግዚአብሔር ቃል ይህን የተናገረው በአዲስ ኪዳን ስለመጣው «አዲስና ሕያው መንገድ» ነው (ዕብ 10:20)።

አሮጌው አቁማዳ ለብዙ ዘመን ያገለገለ ነው (ማር 2:22)። አዲስ ወይን ጠጅ «ሲብላላ» ብዙ ቦታ ይወስዳል፣ ይስፋፋል። ከዚህ የተነሣ አቁማዳውን ይገፋዋል፣ ይሰጥጠዋል። ለብዙ ጊዜ ተገፍቶ (ተሰጥጦ) የኖረ አቁማዳ ሌላ አዲስ ወይን ጠጅ ሲጨመርበት የአዲሱን የመግፋት ኃይል ለመቋቋም ስለሚያዳግተው ይቀደዳል። በአደረጃጀትና በአሠራር መዋቅርም እንዲሁ ነው።

ትልቁ ቁም ነገር ወይን ጠጁ ሳይፈስስ ተጠብቆ መቆየቱ ስለሆነ ይህን የሚያደርግ ተስማሚ አቁማዳ መፈለግ ይገባል። ለምሳሌ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ሁለት መቶ አባሎች ሳሉ የወጣ የአሠራር መመሪያና መዋቅር አባሎቹ ሁለት ሺህ ሲደርሱ አቁማዳው ይጠባል። ሰፋ ያለ ሁሉን የሚደርስ አሠራር ያስፈልጋል። «በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም። ቢደረግ ግን፣ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል፣ የወይኑም ጠጅ ይፈሳል፣ አቁማዳውም ይጠፋል። አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ያኖራል» (ማር 2፡22)።

የወይን አቁማዳው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት እኛ የምናዘጋጀው አደረጃጀት፣ የአሠራር ሥልት፣ የምናዘጋጃቸው ፕሮግራሞች፣ የምንቀርጻቸው የውስጥ የአስተዳደር መመሪያዎች ናቸው። እነዚህ የአሠራር መንገዶች ከአገር አገር፣ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሊለያዩ ይችላሉ። ትልቁ ጥያቄ ግን እኛ ባለንበት ዘመንና ባለንበት አገር የእግዚአብሔርን ቃል ሳይቃረን ጥሩ የአሠራር መንገድ የትኛው ነው? ብሎ መጠየቅ ይሆናል። በአንድ ዘመን የነበረ አሠራር በሌላ ትውልድ ብዙም ውጤት ላያስገኝ ይችላልና።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እካሉና ሙላቱ ናት። የምትመራው በእግዚአብሔር ቃል ነው። በየትኛውም ዘመንና ሁኔታ በየትኛውም አገር ውስጥ ብትሆን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት፣ ይህ ሊለወጥ አይችልም፣ አይገባም።

በለውጥ ጊዜ መለወጥ የሚገባውንና መለወጥ የሌለበትን ለይቶ ማወቅ ትልቅ ማስተዋል ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ዘመን ደቀ መዛሙርት ያላቸውን ሁሉ በአንድነት ያደርጉ ነበር። ይህን አሠራር በአሁኑ ዘመን በቀጥታ በሥራ ላይ ለማዋል ያስቸግራል። ግን ደቀ መዛሙርት ይህን በማድረጋቸው ለዚህ ዘመን የሚቀርልን መሠረታዊ ነገር አለ። ይህም **በአሁኑ ዘመን ያሉ የጌታ ደቀ መዛሙርት (ክርስቲያኖች)** በአንድ ልብ መሆን እንደሚገባቸውና በቅዱሳንም መካከል ችግረኞችን መርዳት እንደሚገባ ነው።

### 14.2.5 ተተኪዎችን ማዘጋጀት- «ኢያሱን እዘዘው፣ አደፋፍረው፣ አጽናውም»

እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪና ባለቤት ስለሆነ እርሱ የጀመረውን ሥራ መቀጠል ያውቅበታል። እግዚአብሔር አንድን መሪ ቢወስድ ሌላ ተተኪ አዘጋጅቶ ነው። በሥልጣን ላይ ያለ አስተዋይ መሪ አስተዋይነቱ ከሚለካበት መንገድ አንዱ ከእርሱ በኋላ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ሰው በመለየቱ፣ ያን ሰው በማሳደጉና አሁን በቃህ ወይንም የምትሞትበት ቀን እነሆ ቀረበ ሲባል (ዘዳ 31፡14) በፈቃደኝነትና በደስታ እርሱን የሚተካውን ሰው እግዚአብሔር እንዲቀባው በእግዚአብሔር ፊት በማቅረቡ ነው። «መሞቻዬ እንደቀረበ የማውቀው ስሞት ብቻ ነው» ሳይል፣ ወይም እንደ ሳያል የሚተካውን ሰው በቅንዓት ለመግደል ሳያሳድድ ሌላውን የሚተካ ነው።

ሳያል እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ በማወቁና መንግሥትንም ለእርሱ እንደሚሰጠው በመረዳቱ ዳዊትን በመግደል መንግሥቱን (ቅባቱን) ለማራዘም የሞከረ ማስተዋሉ የተወለደበት ሰው ነው። ሳያል በእግዚአብሔር የተመረጠና የተቀባ ነገር ግን ለራሱ ምኞት የተሸነፈ የደካማ መሪ ምሳሌ ነው።

በቤቱ ውስጥ የሚያገለግሉትን አገልጋዮች የሚመርጥ፣ የሚቀባ፣ የሚሾም እግዚአብሔር ነው። ይህን ተግባር በሰዎች በኩል ሊያደርገው ይችላል። ለኢያሱ እንዳደረገው። እግዚአብሔር ሙሴን፦ «በፊትህ የሚቆም የነዌ ልጅ ኢያሱ እርሱ ወደዚያ ይገባል፣ እርሱ ለእስራኤል ምድሪቱን ያወርሳልና አደፋፍረው» (ዘዳ 1:38) አለው። ኢያሱ በሙሴ ፊት ይቆም የነበረ፣ በሙሴ «እግር ሥር» መሪነትን የተለማመደ፣ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ያደረገውን ተአምራት ያየ ሰው ነው (ዘዳ 3:21)። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፦ «እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ፣ እንደ ሙሴ ያለ ምልክትና ድንቅን ያደርግ ዘንድ የተላከ ነቢይ አልተነሣም» (ዘዳ 34:10-12)። ይሁን እንጂ ሙሴም ለሁልጊዜ እንዲኖር ሞት አይፈቅድለትምና ሙሴ ከመሞቱ በፊት እርሱን የሚተካ «ሴላ መንፈስ» ያሰውን ኢያሱን እግዚአብሔር አዘጋጅቶ ነበር። በሙሴ ፊት የሚቆምና ይረዳው የነበረ ኢያሱ የሙሴን በትር ተቀበለ፣ ኤልያስን የሚከተል ኤልሳዕ የኤልያስን መጎናጸፊያ ወሰደ፣ ኤልሳዕን ይከተል የነበረ ግያዝ ግን ለክብር አልበቃም። ለራሱ ጥቅም ፈልጓልና (2ነገ 4:8-37)።

እንደ ሙሴ ያሉ ትሑት መሪዎች እግዚአብሔርን በማማከር እነርሱን የሚተኩ አገልጋዮችን የሚለዩና የሚያዘጋጁ ናቸው። እነዚህ መሪዎች እግዚአብሔር ሙሴን ስለ ኢያሱ፦ «ኢያሱን እዘዘው፣ አደፋፍረውም አጽናውም» (ዘዳ 3:28) ብሎ እንዳዘዘው መሪዎች እነርሱን የሚተኳቸውንም ማደፋፈርና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመረጣቸውን ደቀ መዛሙርት ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል ከእርሱ ጋር አቆይቶ፣ አስተምሮ፣ አሰልጥኖ፣ አለማምዶ እርሱ ያስተማራቸውን ሁሉ እንዲያስተምሩ (ማቴ 28:18-20) ኃላፊነት ሰጣቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ አገልጋዮችን በተለይም ደግሞ ጢሞቴዎስንና ቲቶን በጌታ አሳድጎና «አሠልጥኖ» ኃላፊነት የሰጣቸው ሰዎች ናቸው።

ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጽድቅና ጥበብ ለመሪነት የመረጣቸው ሰዎች አገልግሎታቸውን እንዲያቋርጡ ቢያደርግ የሥራው ባለቤት ተተኪዎችን አዘጋጅቶ ነው። ሙሴን ወደ ከነዓን አትገባም ሲለው ኢያሱን አዘጋጅቷል (ዘዳ 1:37-38፣ 31:2-8)። ዳዊትን ቤት አትሠራልኝም ሲለው ሰሎሞንን አዘጋጅቶ ነው (1ዜና 22:5-13፣ 28:2-8)። ነቢዩ ኤልያስን ሊወስደው ሲፈልግ ኤልሳዕን «በእጥፍ» እንዲያገለግል እያዘጋጀው ነበር (2ነገ 2:9)።

እንግዲህ የአካሉ ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ቤቱ አመራር ያስባል። የሾመውን በቃህ ሲለው ሌላ ያዘጋጀው ስላለው ነው። በሰዎች ዘንድ ደግሞ ሥራው ተከታይነትና ቀጣይነት እንዲኖረው አድርጎ የአሠራር ሥርዓት ማበጀት፣ ተተኪዎችን ማዘጋጀት (ማሰልጠን)[89] መልካም አደረጃጀትና አመራር ነው።

[89] succession planning

## 14.3 አገልጋይ መሪነት

### 14.3.1 የክበሬታ ስፍራና አገልጋይነት

በዚህ ዘመን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እየታየ ያለው ትልቁ ትግል የክበሬታ ወንበሩ[90] ለማን ይሰጥ በሚለው ጉዳይ ላይ ነው። ይህም ያለ ወንበሩ በገንዘቡ ላይ ማዘዝ ስለማይቻል፣ ያለ ወንበሩ በልብ ያለውን እቅድ ለማከናወን ስለሚያዳግት ብዙ ጊዜ ወድድሩ አገልግሎትን ለመፈጸም ሳይሆን በገንዘቡ ላይ ለማዘዝ ወይንም ከረጢቱን ለመያዝ፣ ታላቅነትን ለማሳወቅ፣ የልብ ምኞትን (የግል ራእይን) ለማስፈጸም ሲሆን ይስተዋላል።

ታላቅነትን መፈለግ በጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል የታየ ችግር ነበር (ማቴ 20:26-27)። የክበሬታን ወንበር የሚሰጠው ለዚህ ቦታ የተጠራውን ሰው የሚያውቀው ጋባዡ ነው (ሉቃ 14:7-11)። ወንበሩን የያዘ ሰው እንደ ጌታ ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን ለማገልገል ካቃተው አገልጋይነትን ገና አልተማረም።

«በቀኝና በግራ እንድንቀመጥ» የሚለው ጥያቄ (ማቴ 20:21) ዛሬ በብዙ ቤተ ክርስቲያናት ዋና የመከራከሪያ ርዕስ ነው። ወንበሩ ላይ ስለ መቀመጥ። ጌታ ደግሞ የሚለው መሪነት ማለት ማበሻውን መታጠቅ፣ ዝቅ ማለት፣ ማገልገል ነው። ስለዚህ በወንበርና በአገልግሎት መካከል ያለውን ልዩነት አለመገንዘብ የዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ዋና ችግር ነው። በቤተ ክርስቲያን ያለውም ፉክክር በአብዛኛው «ወንበሩ ለእኔ ነው» የሚል የይገባኛል ጥያቄ ነው።

የክበሬታ ወንበር በውስጡ «እኔ እበልጥ አንተ ታንስ» የሚል የበላይነት ስሜትን የያዘ ነው። እውነት ነው ሰው ራሱን ከሌላ ሰው ጋር ሲያወዳድር በአንዳንድ ምድራዊ መለኪያዎች እኩል ይሆናል፣ ይመጣጠናል፣ ይበልጣል ወይም ያንሳል። ማንኛውም ሰው ራሱን በእግዚአብሔር መለኪያ የሚለካ ቢሆን ግን «ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋልና» (ሮሜ 3:23) የተባለውን ያስተውላል። ስለዚህ በምንም ዓይነት ወንበር ላይ ቢቀመጥ «የማንጠቅም ባርያዎች ነን» (ሉቃ 17:10) የሚለውን ያስተውላል።

በቤተ ክርስቲያን ማዕረግ የሚሰጠው ለአገልግሎት ነው። መጋቢ ቢባል የመመገብ ተግባር (አገልግሎት) እንጂ የሥልጣን ደረጃ ማለት አይደለም። የመጋቢነት አገልግሎት ሥራ ነው። ሽማግሌ የሽማግሌነት ወይም የአመራር አገልግሎት እንጂ የበላይነት መግለጫ አይደለም። የአገልግሎቱ ዓይነት በሥራው ላይ ከፊት ለመገኘት፣ ቀዳሚ ሆኖ ለመገኘት፣ ተጠሪ ለመሆን ነው። ቀዳሚነቱና ተጠሪነቱ በአገልግሎትነቱ ነው እንጂ «በገርነት» አይደለም።

---

[90] በዚህ መጽሐፍ «የክበሬታ ወንበር» የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው በአገልጋይነት ላይ ያላተኮረ አመራርን ነው።

ክብርን መፈለግ ከመንገድ የሚያስቀር ጠልፎ የሚጥል ገመድ ነው። መከበርን የለመደ መዋረድን ለመቀበል፣ መስቀል ተሸክሞ ለመሄድ እጅግ ይቸግረዋል። ሰው አብዛኛውን ጊዜ ራሱን አሁን ካለበት ቦታ ይልቅ ከፍ ባለ የከበሬታ ስፍራ ላይ ለማየት ይናፍቃል። ይህም ራስን ማጠላለፍና ራስን ለውድቀት ማዘጋጀት ነው። በሌሎች ሰዎች ዘንድ መከበርን የሚናፍቅ ሰው የሚከበረው ከአንድ የከበሬታ ስፍራ ወደ ሌላኛው የከበሬታ ስፍራ ያደገ እንደሆነ አድርጎ ያስባል። ይህ ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ ምኞት ካደገ ኃጢአትን ይወልዳል።

እግዚአብሔር የሚፈልገው መሪ እንደ ሙሴ ለመጠላት እራሱን ያዘጋጀ፣ ክብርን የናቀና መነቀፍን የሚመርጠውን ነው (ዕብ 11:24-26)። አሁን ከፍ ባለ የከበሬታ ስፍራ ያለ ሰው ቀድሞ በነበረበት ስፍራ ተመልሶ ለመቀመጥ ለማገልገልና በሌሎች ወንድሞች ሥር ሆኖ ለመታዘዝ የተዘጋጀ ካልሆነ ትዕቢት እያደባችበት ነው። ጌታ እንደ መልካም ፈቃዱ የእርሱን ቦታ ለሌላ ቢሰጠው ጌታ ለሰጠው ሰው ይዞት ያለውን ስፍራ ለማስረከብና ለመልቀቅ የተዘጋጀ ልብ የሌለው ሰው ራሱን በራሱ ያከበረ ሰው ነው። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር የተናቀ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ሁሉም ምእመናን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወንድማማችና እኩል የሆኑ ወንድሞች ናቸው። መጋቢነትና ሽማግሌነት ሌሎችን ወንድሞች እንዲጠቅሙበት የተሰጣቸው የጸጋ ስጦታ ነው። የከበሬታ ስፍራም ሆነ ሰው «አለኝ» የሚለው ማናቸውም መልካም ነገር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲሁ የተሰጠው ችሮታ ነው። ከእግዚአብሔር በችሮታ የተሰጠ ነገር ስለሆነ ከሌላው ለመብለጫ ወይንም ለመወዳደሪያ አልተሰጠውም። መጽሐፍ እንደሚል በአንዱ ላይ አንዳችሁም እንዳትታበዩ፡... አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው» (1ቆሮ 4:6-7)።[91] ስለሆነም ለአገልግሎት መጠራት የበለጠ ትሑት ሊያደርገን ይገባል።

ትሕትና ስለ ጌታ ብሎ ዝቅ ያለ ስፍራን ወይም በሌሎች የተዋረደ የሚመስል ደረጃን ለመቀበል ፈቃደኛና ዝግጁ መሆን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ንጉሥ ሆኖ ሳለ በነገሥታት አካሄድ በሠረገላና በሠረገለኞች ታጅቦ መሄድ ሲቻለው «እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል» (ማቴ 21:4-5) እንደተባለው የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ ራሱን ዝቅ አድርጎ ነው የተመላለሰው። እውነተኛ ታላቅነት የሚገኘው ራስን ዝቅ አድርጎ ማበሻ ታጥቆ፣ በማገልገል (ማር 10:42-47) ነው።

በእግዚአብሔር መንግሥት ወንበር ወይም ደረጃ የሚሰጠው *በትሕትና* ነው። ትሑት የሆነ ዝቅ ብሎ ታናናሾችን ለማገልገል የማይሸዘደው ወይንም አገልግሎትን የአዘቦት ተግባር የሚያደርግ ነው። ትሑት የሆነ ራሱን ከሌላው እንደሚሻል አድርጎ የማይቆጥር ነው። ይልቁንም የእግዚአብሔር ቃል «አያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር» (ፊሊ 2:3) እንደሚል ሰው ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል አድርጎ ለመቁጠር ትሕትና ያስፈልገዋል። ትሑት የሆነ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚወድና የሚያከብር ነው።

[91] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ እንዲህ ይላል። «አንድን ሰው ከሌላው አብልጣችሁ አትመኩበት። ለመሆኑ አንተን ከሌላው እንድትበልጥ ያደረገህ ማን ነው? ያልተቀበልኸው የራስህ የሆነ ነገር ምን አለ? ከተቀበልህ ታዲያ እንዳልተቀበልህ ለምን ትመካለህ?»

በእግዚአብሔር መንግሥት በእግዚአብሔር ሚዛን ከመጥምቁ ዮሐንስ ይልቅ ታናሽ የተባለው ይበልጣልና (ሉቃ 7:28)። በአንድ ቤተ ክርስቲያን ካለ ከአረኛው (ከሽማግሌው) ይልቅ በእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ ማዕረግ የሚኖረው አንድ በአረኛው እንኳ የማይታወቅ ምእመን ሊሆን ይችላልና።

የአገልግሎት ማዕረግ ማለትም አረኛ፣ አስተማሪ፣ ወንጌላዊ፣ ሽማግሌ፣ ዲያቆን ወዘተ የበላይነት ማዕረግንና ወንበርን አያመለክትም፣ የተሰጠውን የመክሊት ዓይነት እንጂ። በተሰጠው በመክሊቱ የነገደ ታማኝ ይባላል። በትሕትና የሌደ፣ የሚያስተምረውንም የሚያደርገው (ማቴ 5:19፣ ሉቃ 9:48) ታላቅ ይባላል። ይህም ጌታ ለባርያዎቹ የሚሰጠው አሠራርና ማዕረግ ነው። በተሰጠው የጸጋ ስጦታ ድንቅና ተአምራት ያደረገ አገልግሎቱን ፈጽሟል፣ ታማኝ ነው። በድንቅ ሁኔታ ያስተማረም መልእክቱን አድርሷል ታማኝ ነው። የሚያገለግላቸውን የወደደና ከፍቅር የተነሣ ያገለገለ ዋጋው ታላቅ ነው። ይህ የከበረ ነው፣ ታላቅ ነው።

ስለዚህ ጌታ ያስተማረውና በተግባር የገለጸው አመራር በአገልግሎት ላይ ያተኮረ የባሪያ አመራር ወይም አገልጋይነት[92] ስልት ነው። መሪው ባሪያ ወይም አገልጋይ ሊሆን በአኩያሞች መካከል ፊት የሚቆም፣ እንደ አኩያዎቹ አኩል ባሪያ የሆነ ነው እንጂ ገዢ አይደለም። ቦታው የሰጠውን ኃላፊነት በትሕትና ይፈጽማል። እርሱ ግን እንደ ሌሎች ሁሉ ራሱም የጌታ ባሪያ የሆነ በአንድ ቤተሰብና በወንድሞች መካከል ወንድም የሆነ ነው።

### 14.3.2 «ዋናው» መሪ ማን ነው? - (ጳጳስ/ ቄስ/ አረኛ/ ሽማግሌ)

በዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን የአሠራር ዓይነት እየተቃኘ የመጣው ከጌታ ቃል ውጭ በሆነ የአሠራር ዘይቤ ሆኖአል። ቢቻል አንድ ጎልቶ የሚወጣ መሪና ሌላው ሁሉ በእርሱ የሚመረጥ በእርሱ የሚሾም የሚሻር[93] ተመሪ እንዲሆን ለማድረግ። መሪነት ማለት ገዥነት፣ አዛዥነት፣ ሥልጣንን ማስባሰብ፣ ከተጠያቂነት መራቅ ማለት እየሆነ ነው። ይሁን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የአመራር ትምህርት አይታለፍም።

---

[92] For more reading on servant leadership please refer to Gottfried Osei-Mensah, (1990) *Wanted: Servant Leaders*, Africa Christian Press.

[93] በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አንድ «ዋና» ሰው የእርሱን የአመራር አባላት (team / cabinet) የሚመርጥበትና የሚያሰናስትበት አሠራር አለ።

መሪነት[94] ምን ማለት እንደሆነ ብዙዎች ትርጉም ሰጥተዋል[95]። ይህ ጸሐፊ ለመንፈሳዊ መሪነት የሚሰጠው አጭር ትርጉምና የትርጉሙም ይዘት የሚከተለው ነው።

***መንፈሳዊ መሪ ክርስቶስን እየመሰለ የሚኖርና ሌሎችን ለሥራው የሚያነሣሣ ነው።***

በዚህ ትርጉም መሠረት መሪነት ሁለት ቁልፍ ነጥቦችን (ሐረጎች) ይዟል።
ክርስቶስን መምሰል
ሌሎችን ማነሣሣት[96] የሚሉት ናቸው።

እነዚህ ነጥቦች ሲዘረዘሩ የሚከተለውን የትርጉም ይዘት ሊሰጡ ይችላሉ። መንፈሳዊ መሪ፦

(1) የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር የሆነና የእርሱን ፍለጋ የሚከተል፣
(2) የሚመራውን ሕዝብ የሚወድና የሚያከብር፣
(3) ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ራሱን ያስገዛ፣
(4) እርሱ ላለበት ዘመን (ወቅት)፣ ቦታ (አካባቢ) እና ሥራ (ኃላፊነት) የመንፈስ ቅዱስን ምሪት የሚጠይቅ፣ ስለሆነም
(5) የሚሄድበትን አቅጣጫ ያወቀ፣ የተረዳውን ለሕዝቡ በትሕትና የሚያስረዳ፣ የሚመካከርና ለሥራ የሚያነሣሣ
(6) ፊት በመሆን መንገድ የሚያሳይ፣ አብሮ የሚያደርግና ውጤቱ በጋራ እንደተደረገ የማይዘነጋ፣
(7) በቃልና በተግባር ምሳሌ የሚሆን፣ ሥርዓትንም የሚያስጠብቅ
(8) ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር የሚያደርግ

አገልጋይ ነው።

እንዲህ ዓይነት መሪ እንደ ጳውሎስ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ቆሮ 11:1) ይላል። የዚህ መሪ ትልቁ የመሪነቱ ጥንካሬ የተመሠረተው ክርስቶስን በመምሰሉ ላይ ነው።

የመሪነት (የአገልጋይነት) ትርጉም እንዲህ ከሆነ የዚህ ንዑስ ምዕራፍ ዓላማ - መሪነትን በተመለከተ ያሉትን የአመራር መንገዶች በአጭሩ በማመልከት ስህተት በሚታይባቸው አሠራሮች እርማት ለማድረግ እንዲረዳና የተሻለና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የአመራር ስልት ለማሳየት ነው።

---

[94] Hb:- to lead - H5148 nachah (naw-khaw')- to guide; H5057 nagiyd (naw-gheed'); or nagid (naw-gheed'); a commander (as occupying the front), civil, military or religious; one out in the front. Gk:- G3594 hodegeo (hod-ayg-eh'-o); to show the way.

[95] «Leadership is influence, the ability of one person to influence other, one man can lead others to the extent that he can influence them.» J. Oswald Sanders. "One leads in order to show the way. One leads in order to take others down a particular path." ... "A leader is a person with influence." Leadership letter, Issue 1, May 2004.

[96] influence, motivate, draw or rally people to a common cause

## 14.3.3 የቤተ ክርስቲያን አመራር በታሪክ ውስጥ

(1) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየው ወመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረችው የቤተ ክርስቲያን አመራር በሽማግሌዎችና በጎብረት ነበር። ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ በሽማግሌያዊ አመራር ላይ የሀሳብ ልዩነት የታየበት ጊዜ ነበር። (2) ይህም በሽማግሌዎች አመራርና በአንድ ጳጳስ የበላይነት ሥር መመራት በሚለው መካከል ነበር። በሦስተኛውና አራተኛው ክፍለ ዘመን በአንድ ጳጳስ የበላይነት ሥር መመራት የሚለው አስተሳሰብ እየተጠናከረ እንደሄደ ከታሪክ እናነባለን። (3) ከዚህ በኋላ እንዲያውም አማኞች የንጉሥ ካህናት መሆናቸውን የሚዘነጋ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት ዓይነት ሥርዓት እየተጠናከረ መጥቷል። ማርቲን ሉተር በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግልጽ ከተቃወመው አንዱ ይህ ነበር። ከዚህ በኋላ ባሉት ዘመናት የተለያዩ የአመራር መንገዶች ታይተዋል።

ዛሬ በኢትዮጵያ በሚገኙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የምናያቸው አንዳንድ የአመራር ዓይነቶች በታሪክ ከታዩት ከእነዚህና ከሌሎችም አመራሮች በጥቂት ወይም በብዙ የተወሰደ የአመራር ዘይቤ ይታይባቸዋል።

በዚህ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በሦስት ዋና ክፍሎች ይመድቧቸዋል። እነርሱም ኤጲስቆጶሳዊ፣ ፕሪስፒቴሪያዊ እና ኮንግርጌሽናዊ ናቸው። እነዚህን አከፋፈሎች በምድር ከሚታዩ የመንግሥት አወቃቀሮች ጋር ሲያዛምዷቸውም ኤጲስቆጶሳዊን ከሞናራካዊ፣ ፕሪስፒቴሪያዊን ከአርሲቶክራሲያዊ እና ኮንግርጌሽናዊን ከዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ጋር ያመሳስሏቸዋል። እነዚህን አጠር ባለ ሁኔታ ቀጥሎ እንመለከታለን።

### ሀ. ኤጲስቆጶሳዊ

ኤጲስቆጶሳዊ (ወይም ሞናርካዊ አገዛዝ) የተሰኘው የቤተ ክርስቲያን አመራር ዓይነት ይበልጥ የቀራበ ሆኖ የሚገኘው በጳጳስ አስተዳደር ሥርዓት ለሚተዳደሩ ቤተ ክርስቲያናት ነው። ይህም ጳጳሱ ወይም የአንድ ሰው የበላይነት የሚታይበት የአመራር ሥርዓት ነው። አንድ ሰው አብረውት ከተሰለፉት በላይ አለቃና መሪ ሆኖ በገሸሩነት ከፍ ብሎ የሚታይበትን ሥርዓት ገላጭ ነው።

ይህ የአንድ ሰው አመራር «የሚቀጥርና የሚያባርር»[97] ተብሎም ይገለጣል። ያ አንድ ሰው የሚሾም የሚሽር፣ የሚቀጥር የሚያሰናብት፣ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ለማመልከት ነው። የአንድ ሰው መሪነት ብዙ ችግሮች እንዳሉት ብዙዎች ይገልጻሉ።[98]

---

[97] Hire and fire pastoral system

[98] Dr Elijah Maswanganyi and Dr Kevin J. Conner in their book state that:- «The one man type of leadership "... has been referred to as the "one man showroom", or "the one-band", where every one feels he is the whole orchestra [choir]. This one-man leadership ministry is a loner, an isolationist, and independent. He has no one to speak to his life. He has no checks and balances. He is a law to himself. He has much authority, great

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደታየው ይህ አንድ ሰው ጳጳስ፣ ኤጲስቆጶስ፣ ፓስተር (መጋቢ)፣ ዋና ሽማግሌ፣ ወዘተ ሊባል ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ «ነጻ ቤተ ክርስቲያኖች»[99] ወይም «ራሳቸውን የቻሉ ቤተ ክርስቲያኖች» በሚባሉት እንዲህ ዓይነት አመራር ይታያል።

ይህ አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ በታማኝነት የሚያገለግል፣ ትሑት ሊሆን ይችላል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች፣ ትታነጻለች፣ ሰላምም ይሆናል። ይህ ሰው አመጸኛ፣ ራሱን ወዳድ በሆነበት ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከት ይፈጠራል።

የዚህ ዓይነት አመራር ዋና ችግሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊነቱ በእጅጉ አነጋጋሪ ከመሆኑም በላይ ለአሠራሩ ተገቢ ሥርዓት፣ መቆጣጠሪያና መመለሻ መንገድ ስለማይበጅለት ሰውየው ከመስመር የወጣ እንደሆነ እስከ ቤተ ክርስቲያን መክፋፈልና መፍረስ ሊያደርስ መቻሉ ነው። ይህ ሰው የስህተት ትምህርትን ካስገባም ብዙዎችን ያሳስታል። ይህም በብዙ ቦታ የታየ ነው።

## ለ. ፕሪስፒቴሪያዊ

ፕሪስፒቴሪያዊ አመራር ጥቂት ሰዎች ወይም አኩል ደረጃ ያላቸው ሽማግሌዎች በአንድ ላይ ወይም በጎብረት ሆነው የሚመሩበት ሥርዓት ነው። በሽማግሌዎች ቦርድ የምትተዳደር ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓይነት አመራር ያላት ቤተ ክርስቲያን ነች።

እነዚህ ሽማግሌዎች መልካም ከሆኑ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መልካም ነው። በጎብረት በመሆናቸው አንዱ ሌላውን ለመምከር፣ በጎብረት ሀሳብን ተከፋፍሎ፣ ተመካክሮ ለመወሰንና ለመምራት የተሻለ የአሠራር ስልት ነው። ሆኖም ይህ የሽማግሌዎች ጎብረት ራሱን ከምዕመናን ካራቀና ለብቻው ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ከፈለገ የጎብረት (የቡድን) ገዥነት ሊታይበት ይችላል። በሽማግሌዎች መካከል እግዚአብሔርን አለመፍራት ከመጣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብና ጉብረት የራሳቸው (የግላቸው) አድርጎ እስከመቁጠር ሊያደርስ ይችላል። ሆኖም ይህ ዓይነት አሠራር በጎብረት የሆነ አመራር በመሆኑ የመቆጣጠሪያው መንገድ ቢበጅለት የተሻለ አሠራር ነው።

---

responsibility, but no accountability to anyone. Such a man is a danger to himself as well as a danger to others. The one-man leadership ministry may be described under various synonymous words, ... the autocrat, the chieftain, the dictator, ..., the monarch, the super-star." p.19. «history [modern church history] ... is scattered with "Super-Stars" who have fallen. ... The reason? They were alone. They were untouchable. They were unaccountable. ... How many one-man leaders and ministers feel they are "Super-Stars", and all others have to move around them in the orbit of their will!" Biblical Principles of Leadership: Two are better than one, 2000 second edition, Hebron Press, Tzaneen, SA, p. 23.

[99] Independent churches

## ሐ. ኮንግርጌሽናሳዊ

ኮንግርጌሽናዊ አመራር ዲሞክራሲያዊ አመራር ነው። ይህም በአብዛኛው ሕዝብ ፍላጎት ወይም ድምጽ መመራት ማለት ይሆናል። በዚህ ዓይነት የአስተዳደር ሥርዓት የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን የሚሾሙትም ሆነ መጋቢውን የሚቀጥሩት (የሚሽሙት) እና የሚያሰናብቱት በድምጽ ብልጫ ነው። በእንዲህ ዓይነት ሥርዓት ውሳኔ ሰጪው ሕዝቡ በመሆኑ ሁልጊዜም አብላጫ ድምጽ ያለበት ሀሳብ ትክክለኛ ነው ተብሎ ይቆጠራል።

ከዚህም በተጨማሪ አራተኛ የአመራር ዓይነት የሽማግሌዎችና እረኞች ቦርድ አመራር ነው። ከእነዚህ ሌላ ከአንደኛው ዓይነት የተወሰነ ነገር በመውሰድና ከሌላው ዓይነት የቀረውን በመጨመር የተዘጋጁ የአመራር ዓይነቶችም አሉ። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ኤጲስቆጶስ ወይም ሽማግሌ በሚለው ምትክ ቄስ የሚለውን መጠሪያ ይጠቀማሉ። የቤተ ክርስቲያንን አመራር (አስተዳደር) በሦስት ደረጃ በጳጳስ፣ በቄስ፣ በዲያቆን የሚከፍሉም አሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አመራር ዓይነት የተለያየ ነው። የሚከተሉት ጎልተው ይታያሉ።

- የሽማግሌዎች ቦርድ
- የአረኛ(እረኞች)ና ሽማግሌዎች ቦርድ
- እረኛው «ዋና» መሪ የሆነበት

በአመራር ውስጥ የእረኛውን ቦታ በሚመለከት አንዳንዶች እረኛውን የእረኞችና ሽማግሌዎች ቦርድ ስብሳቢ ሲያደርጉ አንዳንዶች የቦርድ አባል ብቻ አንዳንዶችም ድምጽ የለሽ አባል ያደርጉታል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የእረኞች ምርጫ የሚደረገው ለውድድር ከሚቀርቡት መካከል በድምጽ ብልጫ ሲሆን ሌሎች ቤተ ክርስቲያናት ደግሞ የእጩው እረኛ የአገልግሎት ፍሬና ጸጋው (ጥሪው) በመሪነት ላይ ባሉት ተመዝኖ ይመረጣል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እረኞችን ለመቀበል ማለትም የእረኝነት አገልግሎት እንዳለ በማመን እረኞችን የመሾም እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው። ይህ ጸሐፊ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት እየታየ ያለው የእረኞችን አገልግሎት የመቀበል እንቅስቃሴ ትክክለኛ እርምጃ እንደሆነ ያስባል።

የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት መንፈሳዊና አስተዳደራዊ በማለት ለሁለት የሚከፍሉ አሉ። በዚህ አከፋፈል የመንፈሳዊው ዘርፍ ተጠሪዎች አብዛኛውን ጊዜ እረኞች ሲሆኑ የአስተዳደራዊው ዘርፍ ተጠሪዎች ደግሞ ሽማግሌዎች ናቸው። ይህ አከፋፈል ለአሠራር ጥሩ ቢመስልም ችግር አለበት። ዋናው ችግር የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች እርስ በርስ እንደተለያዩና የማይገናኙ ያለመስላቸዋል። እንዲሁም ለአስተዳደራዊው ተግባር የሚመደቡት ሽማግሌዎች ከመንፈሳዊ አገልግሎት የራቁ ያደርጋቸዋል።

እነዚህ የአመራር ዓይነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለመሆናቸውም እነዚህን የአመራር ዘይቤዎች የሚከተሉት እያንዳንዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሷቸው ጥቅሶችና ማስረጃዎች ያቀርባሉ። እንዲህ ከሆነ «ትክክለኛው» የሚሆነው የትኛው የአመራር

ዓይነት ይሆን? ትክክለኛው የአመራር ስልት የትኛው አስተዳደራዊ አደረጃጀት ነው ብሎ ከመጠየቅ አስቀድሞ የአመራር ዓላማው (ግቡን) መመርመርና የማንን ምሳሌ በመከተል የተነደፈ የአመራር ዘይቤ ነው? የሚለውን ጥያቄ ማስቀደም የተሻለ ይሆናል። ወደዚህ ሰመድረስ እንዲረዳን የቤተ ክርስቲያንን አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ እንመልከት።

## 14.3.4 የቤተ ክርስቲያን አመራር አጭር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ጎልቶ የሚወጣው እውነት እግዚአብሔር የሕዝቡ (የቤተ ክርስቲያን) ልዑል መሪ መሆኑ ነው።

እግዚአብሔር በአዳምና ሔዋን ላይ ፍርድን ሲሰጥ፣ በኖኅ ዘመን ሊያደርጉ የሚገባቸውን ሲናገርና በአመጸኞችም ላይ ሲፈርድ እናየዋለን። በመሳፍንት ዘመን «ጌዲዎንም፡- ልጄም አይገዛችሁም እግዚአብሔር ይገዛችኋል» (መሳ 8:22-23) ሲል የእግዚአብሔር ገዢነት የታወቀ መሆኑን ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር መሳፍንትን፣ ነቢያትን፣ ነገሥታትን ሲመርጥ፣ ሲቀባ፣ ሲሾም እንመለከታለን። የሥራ ዝርዝር ይሰጣቸዋል፣ እንዴት እንደሚሄዱ ተልኮአቸውን ያሳያቸዋል። በማይታዘዙት ላይ ቅጣት ሰማምጣት እርሱ ዳኛና ፈራጅ መሆኑንም ይነግራቸዋል።

ሙሴ ለመሪነት በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው (ዘጸ 3) ነው። የሌዊ ወገን በእግዚአብሔር የተለየ ወገን ነው። አሮን በእግዚአብሔር የተጠራ፣ የተመረጠ፣ ለሊቀ ካህንነት የተሾመ ሰው (ዘጸ 28:1) ነው። ነቢያት ኤልያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ ሌሎችም እግዚአብሔር ያስነሳቸውና የቀባቸው ነበሩ።

በሐዋ 13:20 ላይ «ከዚህም በኋላ እስከ ነቢዩ እስከ ሳሙኤል ድረስ አራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል መሳፍንትን ሰጣቸው» የሚለውን እናገኛለን። «ሰጣቸው» የሚለው ቃል እግዚአብሔር መሳፍንትን እንደመረጠና ለሕዝቡም እንደሰጠ ያስገነዝበናል። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የተመራው በእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር መሪዎችን ይጠራል፣ መሪዎችን ይቀባል፣ ኃይልም ይሰጣቸዋል። እንዲሁም እግዚአብሔር የመረጠውን መሪ በስዎች በኩል ሲቀባ እንመለከታለን። ለምሳሌ ሳያልና (1ሳሙ 9:10) ዳዊት (1ሳሙ 16) በሳሙኤል በኩል ሲቀቡ እናያለን።

አዲስ ኪዳንንም ስንመለከት የሐዋርያት መመረጥ በጌታ ነበር። እንዲሁም «መንፈስ ቅዱስ፡- ... ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ» (ሐዋ 13:2) በማለት ለዎችን እንደሾመ እናነባለን።

ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር የበለጠ ለመረዳት ከአመራር ጋር የተያያዙ ቃላትን ወይም ስያሜዎችን መተንተን አስፈላጊ ይሆናል።

## ጳጳስ/ ኤጲስቆጶስ

ጳጳስ የሚለው ቃል በግሪኩ ኤጲስቆጶስ[100] ማለት ሲሆን አጠር ያለ ትርጉሙ የበላይ ተመልካች ወይም ተጠሪ/መሪ የሚል ፍቺ ይኖረዋል። ጳጳሳት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን የመጠበቅ ኃላፊነትና አደራ ያለባቸው (ሐዋ 20:28) አገልጋዮች ናቸው። በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን (ኤፌሶን) ከአንድ በላይ ቁጥር የነበራቸው ጳጳሳት/ ኤጲስቆጶሳት ነበሩ (ሐዋ 20:17፣ ፊሊ 1:1)። ኤጲስቆጶስ ሽማግሌ[101] ተብሎም ይጠራል።

ኤጲስቆጶስ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን የሚጠብቅ (1ጢሞ 3:5) ነው። ኤጲስቆጶሳት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው (ፊሊ1:1፣ 1ጢሞ 3:1-7)። ይህም ሽማግሌ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው (ቲቶ 1:5-9፣ 1ጴጥ 5:1-4)። ኤጲስቆጶስ የሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ሽማግሌ የሚለውን ቃል ይበልጥ የሚጠቀሙት አይሁድ ናቸው። ኤጲስቆጶስ/ ሽማግሌ ከአገልግሎታቸው አንዱ ማስተማር (1ጢሞ 3:2) ነው።

## ካህናት

ክህነት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው (ዘጸ 18:7)። በተለይ በብሉይ ኪዳን ካህናት ሕግን የማስተማር፣ መሥዋዕት የማቅረብ፣ ሕዝቡን የመባረክና በቤተ መቅደስ ውስጥ አገልግሎት የመፈጸም ኃላፊነት ነበራቸው (ዘኁ 6:22-27፣ ዘሌ 1:4-17፣ 10:11፣ ሚል 2:7)። በአዲስ ኪዳን ምዕመናን ሁሉ ካህናት ተብለዋል (1ጴጥ 2:9)።

## እረኞች

እረኞች[102] ምርኮን ማርኮ ስጦታን በሰጠው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው (ኤፌ 4:11)።[103] ከቃሉ ትርጉም

---

[100] bishop የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል የመጣው episcopus/ episkopein ከሚል የግሪክ ቃል ሲሆን 'epi'- upon + skopos - to look (see) = overseer. Bishop is a high ranking member of the christian clergy having authority, over other clergy and usually supervising a diocese or church district:: በተለይ በአሁኑ ዘመን እንደሚሠራበት ጳጳስ፡- ከአንድ በላይ የሆኑ አጥቢያዎችን የሚመራ /የሚከታተል/ የሚቆጣጠር መሪ ነው። አነዚህ አጠራሮችና የአገልግሎት አመዳደቦች ካለፉት ጥቂት መቶ ዓመታት ጀምሮ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች (denominations/ traditions) መለያ እየሆኑም መጥተዋል።

[101] ሽማግሌ የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜው መብለልን ወይም መብሰጥን ብዙ የሕይወት ልምድ ያለው ለው መሆንን የሚያሳይ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደግሞ በአንድ አጥብያ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር ከአንድ በላይ የሆኑና ለመሪነት ተመርጠው የሚሾሙ አገልጋዮችን ያመለክታል።

[102] GK: poimen (poy-mane'); a shepherd (literally or figuratively):

እንደምንረዳው እረኞች ኃላፊነታቸው መንጋውን መጠበቅና ማስማራት ነው (ዮሐ 21:15-17፣ ኤፌ 4:11)።

በአንዳንድ የአፍሪካና ላቲን አሜሪካ አገሮች እንደሚታየው እረኞችን የሙሉ ጊዜና የትርፍ ጊዜ ብለው በሁለት ይከፍሏቸዋል። የሙሉ ጊዜ የሆኑት ጊዜያቸውን በሚሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሰጡ ሲሆኑ የትርፍ ጊዜ የተባሉት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በእረኝነት ተቀብላቸው ለመኖሪያቸው ግን በሌላ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው።[104] በሀገራችን እስካሁን የሚታወቀው እረኞች ሁሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች እንደሆኑ ነው።

ባለንበት ዘመን ያለውን የእረኝነት ሁኔታ አንዳንዶች በሦስት

1. ለእረኝነት አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸውና ቤተ ክርስቲያንም ፍሬያቸውን መዝና የተቀበለቻቸው፣
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስለተመረቁ እረኛ የሆኑ፣
3. ራሳቸውን እረኛ ያደረጉ

በማለት ይመድቧቸዋል።[105]

በመሠረቱ እረኝነት በትምህርት ደረጃ ወይንም የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር የሚገኝ አገልግሎት አይደለም። እረኝነት ጥሪ ነው፣ ሸክም ነው፣ ጸጋ ነው። ትምህርት ይህን አገልግሎት ለመፈጸም ጥሩ መሣሪያ ይሆናል። ትምህርት የሚያገለግሉትን እውነት በሚገባ በማወቅ ለማገልገል የሚረዳ መሣሪያ ነው። መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብቶ ያልተማረ እረኛ መሆን አይችልም አይባልም። ይህ የጠራው የእግዚአብሔር ፈንታ ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለአገልግሎት በጠራው ሰው ውስጥ ያስቀመጠውን ጥበብና ጸጋ እርሱ ያውቀዋል። የተጠራው ሰው ግን መማሩ ስጥቅም ይሆናል። አንድም በመማሩ ምክንያት የቃሉ መረዳት ስለሚያድግለት እንዲሁም መንፈሳዊ ትምህርት መማር ትክክለኛ ነገር መሆኑን በተግባር በራሱ ሕይወት ስምእመኑ ለማሳየት መማሩ ተገቢ ነው።

---

[103] እውነት (ወይም የአንድ ቃል ትክክለኛነት) ብዙ ጊዜ ወይም በጥቂቱ በመጸፋ አይለካም እንጂ በአዲስ ኪዳን እረኛ የሚለው የተጠቀሰው ከጌታችን ሌላ እዚህ አንድ ወይም ሁለት (1ጴጥ 5:4) ቦታ ብቻ ነው።

[104] ይህ ሁኔታ ይበልጥ እየታየ ያለው Revival churches / Independent churches በሚባሉት ዘንድ ነው።

[105] በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ጥሪው ላይኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስለተማሩ ብቻ እረኛ ተብለው የሚሾሙትን ለማመልከት ነው። ስለሆነም ተራ ቁጥር 2 ለእረኝነት አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮአቸው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የተማሩትን አይመለከትም። በተራ ቁጥር 3 የተመለከቱትና ራሳቸውን እረኛ ብለው የሚሰይሙት ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን በመክፈል ከማኅበሩ የሚለዩና የራሳቸውን ተከታዮች የሚያሰለፉ ናቸው።

## ሽማግሌዎች

በብሉይ ኪዳን የካህናት ሽማግሌዎችንና የሕዝቡን ሽማግሌዎች እንገኛለን። «የሕዝቡ ሽማግሌዎች» (ዘጸ 19:7፣ ዘኁ 11:25፣ ዕዝ 10:14) «የእስራኤል ሽማግሌዎች» (ዘጸ 3:16)፣ እንዲሁም ሰባ ሽማግሌዎች (ዘጸ 24:1) ተብለዋል። ሰባዎቹ ሽማግሌዎች ከሙሴ ጋር ሆነው ሕዝቡን ያስተዳድሩ የነበሩ ናቸው።

በዚህ ዘመን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት **ሽማግሌና ዲያቆን** በሚል ሁለት ክፍል ደለው አመራር አላቸው። ክእነዚህ የአመራር ክፍል ውስጥ አንዳንዶች የሽማግሌዎችን ቢሮ የሚያስተምሩ ሽማግሌዎችና የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች በማለት በሁለት ይከፍሉታል። የሚያስተምሩ ሽማግሌዎችን የሙሉ ጊዜ ሽማግሌዎች ወይም እረኞች ለሏቸው በትርፍ ጊዜ በሽምግልና የሚያገለግሉትን ደግሞ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ይሏቸዋል። የሚያስተምሩ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር (ክፍ ያለ ክፍያ/ ገንዘብ) ይገባቸዋል።

ክ1ጴጥ 5:1-5 እንደምናስተውለው ሐዋርያው ጴጥሮስ በጻፈው መልእክቱ የሽማግሌዎች ተግባር መንጋውን መጠበቅ፣ መጐብኘት፣ ማጎበሩን በኃይል ሳይሆን ምሳሌ በመሆን መምራት እንደሁም ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት መጠበቅ (ሐዋ 20:28-31) ነው። እነዚህ ሽማግሌዎች የእረኞች አለቃ ክሆነው ክጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥር (1ጴጥ 2:25፣ 5:4) የእረኝነትን ተግባር የሚያክናውኑ አገልጋዮች ናቸው።

ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን ወክለው እርዳታ ሲቀበሉ (ሐዋ 11:29-30)፣ በቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ እምነት/ ጉዳዮች ላይ ከሐዋርያት ጋር ሆነው ሲመካከሩ ሥርዓት ሲያወጡ (ሐዋ 15:1-29፣ 16:4-5፣ 21:18) ይታያሉ። ሽማግሌዎች ያስተዳድራሉ፣ ያስተምራሉ (1ጢሞ 5:17)፣ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶችን ይፈጽማሉ (1ጢሞ 4:14፣ ያዕ 5:14-15)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ቲቶን ሽማግሌዎችን እንዲሾም ሲመክረው (ቲቶ 1:5) ሽማግሌ ኤጲስቆጶስ መሆኑንና (1:7) የሽማግሌም ተግባር መጋቢነት (1:7) መሆኑን ይጽፍለታል።

## ሽማግሌዎችና እረኞች

ሽማግሌዎች የማስተዳደር ኃላፊነት እንዳለባቸው ክ1ጢሞ 3:4-5፣ 5:17 እንገነዘባለን። ክሽማግሌዎች- «ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት» (1ጢሞ 5:17) እንደሚል ሽማግሌዎች የመስበክና የማስተማር አገልግሎት ይፈጽማሉ። መስበክና ማስተማር ደግሞ የእረኝነት ተግባር ነው። እንግዲህ ሽማግሌዎችና እረኞች በስም የተለያዩ ሆነው ሳለ ተመሳሳይ ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ።

በ1ጢሞ 3 የተገለጸው የሽማግሌዎች መምረጫ መመዘኛ ለእረኞች እንዲሁም በአጠቃላይ ለአገልጋዮች ሁሉ ሊሆን የሚችል ነው።

ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡ እረኞችና ሽማግሌዎች በመንፈስ ቅዱስ የሚሾሙ ሆነው የተገለጹበት ጊዜ አለ። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባን ሽማግሌነት በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ ሹመት መሆኑን ነው (ሐዋ 20:17፣ 28)። እረኞችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠ ጌታ ሽማግሌዎችንም የሾመ መንፈስ ቅዱስ - ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው። ሽማግሌዎች በሰዎች የሚመረጡ ቢሆኑም እንኳን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ መመዘኛዎችን ተጠቅማ ከመረጠች፣ አድልዎ ከሌለበትና እግዚአብሔርን በመፍራትና በጸሎት ከተደረገ ሽማግሌዎችም ለቤተ ክርስቲያን «የተሰጡ» ናቸው። እረኞችም ቢሆን የሚሾሙት ጥሪያቸው በሰዎች ተመዝኖ ወይም (በሰዎች ተመርጠው) ነው።

ይህ እንዲህ ሆኖ እያለ ከአመራር ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ብዙ ችግሮች ይታያሉ። ችግሮቹ ጎልተው የሚታዩት በሽማግሌዎችና በእረኞች መካከል ወይም በአመራር ዘይቤው ላይ ነው። እነዚህ ችግሮች ምን እንደሚመስሉና መፍትሔዎቻቸው ምን መሆን እንደሚገባው ቀጥሎ እንመለከታለን።

## 14.3.5 በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አመራር የሚታዩ ጉልህ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች

### ችግሮች

#### *ሀ. ወንበሩ ይገባኛል ባይነት*

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአንዳንድ ቦታዎች በሽማግሌዎችና በእረኞች መከካል ከረር ያሉ መሳሳቦች ወይም አለመግባባቶች የሚታዩባቸው ቤተ ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ አሁንም እንኳን እንዳሉ ይታወቃል። ይህም በአብዛኛው «አኔ ልሾም ወይም ዋና ልሆን ይገባኛል» ከሚሉ ጥያቄዎች የመጣ ነው።

የእረኝነትን ቦታ የሚፈልጉ አንዳንድ ወገኖች በእርግጥ መለኮታዊ ጥሪ ኖሯቸው ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስለ ተመረቁ ብቻ የሚመጣ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። በመሠረቱ እረኝነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመመረቅ የሚያገኝ ሥራ አይደለም። እረኝነት መለኮታዊ ጥሪ ነው። እረኛ ከትንሣኤው ጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ አገልጋይ ነው። ከአንድ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምሮ መውጣት በአገልግሎት ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም አንድ ሰው ስነ መለኮት ትምህርት በመማሩ ብቻ «እረኛ መሆን አለብኝ» ብሎ ማሰብ አግባብ አይሆንም።

በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች በሽማግሌዎች ዘንድ ተመሳሳይ ችግሮች እየታዩ ነው። በተለይ ለረጅም ዓመታት በሽምግልና የቆዩ አንዳንድ ሰዎች ከሽምግልና ቀጥሎ ያለው የሥራ ዝውውር ወይም የአገልግሎት የደረጃ እድገት እረኝነት እንደሆነ በማሰብ፣ ወይም «ረጅም ጊዜ አገልግለናል፣ ከፍተኛ ዋጋ የከፈልን እኛ ስለሆንን ለእረኝነት ከኛ ሌላ ሰው አይመጣምና እረኝነቱ ይገባናል» እያሉ የሚጠይቁ ጥቂቶች አይደሉም። ክዚህም የተነሣ ችግሮች የተነሱባቸው ቦታዎች ወይም ቤተ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። ሆኖም ቀደም ብሰን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመመረቃቸው ብቻ «እረኝነቱ ይገባኛል» ስለሚሉት የተባለው ለእነዚህም የጸና ይሆናል። ለእነዚህም ደግመን ማለት ያለብን - እረኝነት መለኮታዊ ጥሪ ነው። እረኝነት ክትንሣኤው ጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን መሰጠት ነው እንጂ «የደረጃ እድገት» አይደለም።

## ለ. መመዘኛዎችን አለመጠበቅ

ሽማግሌዎች በዕድሜ የበሰሉ፣ በአገልግሎት የተፈተኑ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛዎች መሠረት በጥንቃቄ የተመረጡ ሲሆኑ ይገባል። ሽማግሌዎች የበሰሉ ሌሎችን ሊመክሩ የተገባቸው ሆነው ሳለ አንዳንዶች በተለይ ወጣት አገልጋዮችን በልብ ስፋት ለማስተናገድና በምሳሌነት ለማሳደግ የሚከብዳቸው እንዳሉ እየታየ ነው። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤት ብዙ ያልቆዩ አዳዲስ አባላት ለሽምግልና ሲመረጡ የቤተ ክርስቲያንን መልክና አሠራራ ወደ ሌላ ሁኔታ ለመለወጥ የሞክሩባቸው ሁኔታዎች አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ገና ትምህርታቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጨርሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ የመጀመሪያው ጥያቄያቸው ስለሚሰጣቸው ቦታ፣ «ማዕረግ» እና የሚከፈላቸው ደምወዝ መጠን እየሆነ በመምጣቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግር የሚያስነሱ ጥቂቶች አይደሉም። መመዘኛው ተዛብቷል።

## ሐ. ሽምግልና በየተራ/ በመፈራረቅ ከመሆኑ ጋር የተያያዙ

በመሪነት ላይ ቆይተው ከበርካታ ዓመታት በኋላ ልባቸው በአገልግሎቱ ላይ እንዳልሆነ እየታወቀ «ደክመው» ሳለ ቦታን አንለቅም ለሚሉ ሽማግሌዎች እነርሱን ለማሳረፍና የሌሎችን ጸጋ ለመጠቀም አንዱ መንገድ የአገልግሎት ዘመንን መወሰን መሆኑ ጥሩ ነው። ሆኖም በተግባር ሲታይ በአንዳንድ ቦታ «መሪነት በየተራ ሁሉም ይድረሰው» ዓይነት አተረጓጎም እየያዘ መጥቶ ተራ የመያዝና በተራ የማዳረስ አፈጻጸም ይታይበታል። ስለሆነም አካሄዱ አንድ ሰው ያለ ችሎታው ወይም ያለ ጸጋው ወደ ሽምግልና እንዲገባ የሚያደርግ ቀዳዳ አለው። በሌላ መልኩ ደግሞ የመሪነት ጸጋ አየታየባቸው፣ አመራሩን ለምደውት «ገና ጉልበታም ነኝ እያሉ» ጥሩ ሊመሩ የሚችሉ ሕዝቡም የሚቀበላቸው መሪዎች የጊዜ ገደቡ በቦታው ላይ እንዳይቆዩ ያደርጋቸዋል። ይህን የሚያገናዝብ ስልት ካልተቀየሰ ይህ የተራ ጉዳይ አይሎ የቤተ ክርስቲያንን አመራር ይዘትና መልክ ሊቀይረው ይችላል።

### መ. የጊዜ መጣበብ

በተለይ በቅርብ ዓመታት እየታየ ያለው አንዱ ችግር ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ያላቸው የጊዜ መጣበብ ነው። በቢሮ ወይም በሌላ ሥራ የተያዙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ሥራ የሚሰጡት ጊዜ መጠን በጣም አጭር እየሆነ መምጣቱ የእግዚአብሔር ቤት ሥራ «በትርፍ ጊዜ ሠራተኞች» በአጥጋቢ ሁኔታ ሊሠራ ይችላል ወይ? የሚል ትልቅ ጥያቄ እያስነሣ ነው። አንድ ሽማግሌ ቦታው (ኃላፊነቱ) የሚጠይቀውን ያህል «ትርፍ ጊዜ» እንደማይኖረው ከታወቀ ሽማግሌ ተብሎ በመሾሙ ምኑን አገለገለ ይባላል!! በተጨማሪም የአመራሩ ስልት አብዛኛውን ጊዜ በስብሰባ ማሳለፍ እየሆነ መምጣቱ የመሪነትን ዋና ትኩረት ያስረሳል።

### ሠ. የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን ከቤተ ክርስቲያን አመራር ማራቅ

በአንዳንድ ቦታዎች እረኞች በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ የሰብሳቢነት ቦታ ካልተሰጣቸው በስተቀር እራሳቸውን «የሽማግሌዎች ተላላኪ ወይም ጉዳይ አስፈጻሚ» አድርገው የሚቆጥሩ አሉ። በዚህ አባበል (አስተሳሰብ) ውስጥ ትዕቢት እንዳይኖርበት ልብን መመርመር ይገባል። በሌላ በኩል ደግሞ በኤፌሶን 4:11 የተገለጡትና አሁን በቤተ ክርስቲያን የሚታዩት[106] የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ቁልፍ ጉዳዮች ውይይት ላይ እንዲገኙና ከመሪዎች ጋር አብረው እንዲመክሩ አለማድረግ ሕይወታቸውን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥተው እያለ «ባይተዋርነት» እንዲሰማቸው ማድረግ ነው። በሁሉም የመሪዎች ስብሰባ ላይ መገኘት ባይገባቸውም በዋና የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ግን መታጣት አይኖርባቸውም።

### ረ. ባለ ራእዩ «እረኛው ብቻ ነው» ማለት

ብዙ ጊዜ እረኛው ብቸኛ መሪ ወይም የመሪዎች ቦርድ ሰብሳቢ መሆን አለበት የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት አንዱ ማስረጃ ለቤተ ክርስቲያን ራእይ የሚመጣው በእረኛው በኩል ስለሆነ ነው ይላሉ። በዚህ አስተሳሰብ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጠውና የሚመጣው በዚህ ሰው ብቻ ነው ወይም እርሱ የእግዚአብሔርን ድምጽ ይሰማል፣ ፈቃዱን ያውቃል እስክ ማለት ይኬዳል። ራእዩን ለማስፈጸም ደግሞ ሥልጣኑ ይገባዋልና ዋናው እርሱ መሆን አለበት የሚል ነው።

ምንም እንኳ ለቤተ ክርስቲያን የሚመጣ ራእይ በመሪው (እንበል በእረኛው) በኩል ሊመጣ እንደሚችል ቢቆጠርም ይህ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን አሠራር መወሰንና መገደብ እንዳይሆን መፍራት ይገባናል። ራእይ (ወይም ምሳሌ) ተቀብሎ «አንተ አትሠራልኝም» መባልም አለ። ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክትም በተለያየ ሰው በኩል ሊመጣ ይችላል። የእግዚአብሔርን ቃል

[106] The five-fold ministries

በመፈለግ ወደ እርሷ ይመጡ እንደ ነበረ እንደ ነቢይቱ ሕልዳና ወይም በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን እንደመጣው «ለዩልኝ» የሚለው መልእክት እግዚአብሔር በወደደው በኩል ይናገራል።

እንግዲህ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ራእይ በመሪነት በተቀመጠ አንድ ሰው በኩል ሊመጣ ይችላል፣ በነቢይ በኩልም ሊነገር ይችላል። መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን በጎብረት በሚመሩበት ሁኔታ ደግሞ ይህን አንድ የተባለውን ሰው ጨምሮ የእግዚአብሔር ጸጋ በተለያዩ ሰዎች ይገለጣል። በራእይ አፈፃፀም ትልቁ ቁም ነገር የቲቀበሉትን ራእይ በሥልጣን ማለትም በግድ ሰማስፈጸም መጣር ሳይሆን የተሰጠው ራእይ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን አብረው በሥራው ሰተሰሰፉት ሁሉ በማሳየቱና አብሮ በጎብረት በመሥራቱ ላይ ነው። ለዚህም ጥበብንና ምገስን ከእግዚአብሔር መለመን ያስፈልጋል። የማንን ራእይ ማን በግድ ያስፈጽማል?

## ሰ. «ገዥነት»

አንድ ሰው ብቸኛ መሪ ከሆነና መቆጣጠሪያ ዘዴ ከሌለው ያለውን ሥልጣንና የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ለራሱ ጥቅም ወይም ለፈለገው አገልግሎት ለማዋል ይችላል። በማንም የማይጠየቅ ገዥ (አምባገነን) ይሆናል። ለዚህም ብዙ ምሳሌ በታሪክ ውስጥ እናያለን የሚል ነው። የአንድ ሰው ብቸኛ አመራር ገዥነትን የሚያመጣውን ያህል የቡድን ገዥነትን ይኖራል። አንድ ሰው (እረኛ) በነጠላ ገዥ እንደሚሆነው ሽማግሌዎች በቡድን ሲሆኑ ይችላሉ።

በሽማግሌዎችና በእረኞች መከካል በአመራር ዘይቤ ላይ ያሉት አለመግባባቶች በአብዛኛው የስነ-መለኮት መረዳት ልዩነቶች ሳይሆኑ የአመራር ወይም የማኔጅመንት ጉዳዮች ያለዚያም «የግል ጉዳዮች» እንደሆኑ ይህ ጸሐፊ ያስባል። በሽማግሌዎችና በእረኞች መካከል ያለ አለመግባባት በአመዛኙ ስነ-መለኮታዊ መስሎ የሚቀርብብት ጊዜ ቢኖርም የችግሩ ሥረ መሠረት ሲታይ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ችግር ሆኖ አናገኘውም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አመራሩ የአገልጋዮችን ጸጋ የማያበረታታና ከሥር ሰዎችን የማያሳድግ ሲሆን፣ አድሎ ሲታይ ወይም «ለወገኔ ይጠቅማል» ማለት ሲኖር ችግሩ አይሎ ይታያል። ታዲያ ችግሩ እንዴት ይፈታ? በአመራርስ ላይ ትኩረት የሚያስፈልገው ነገር ምንድን ነው?

## 14.3.6 ሰብሳቢው ወይም ዋናው መሪ ማን ይሁን?

ቤተ ክርስቲያን ከአመራር ቦታና ከክበሬታ ወንበር ጋር በተያያዘ ሁልጊዜ በራሷ የውስጥ ችግር እንዳትናጥ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ሚዛናዊ የሆነ አሠራር በፍቅርና በመመካከር ማበጀት ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ባለ ችግር ውስጥ የምትገባው ስለ አካሉ አስተዳደር ጌታ ኢየሱስ ግልጽ የሆነ ሥርዓት ስላልሰጠ ወይንም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለማይናገር አለመሆኑን ማስተዋልም ያስፈልጋል። ችግሩ «ሰዋዊ/ ሰው ሠራሽ» ማለትም ሰው ሠራሽ ነው። ችግሩ የክርስቲያኖች «እኔነት/ ሥጋዊነት»፣ በዓለም ካለው አመራር ጋር ሰማመሳሰል ያለው «ፍላጎት» ነው። አብዛኛውን ጊዜ ቦታው የሚፈለገው ዝቅ ብሎ ለማገልገል ሳይሆን ለሥልጣን ስለሚፈለግና በፍቅር፣ በጸሎትና በመመካከር ከእግዚአብሔር ምሪትን በመጠየቅ ስለማይደረግ ነው። ስለዚህ «ከተጻፈው አትለፍ» አግባብ ያለው የጥንቃቄ መልእክት ነው።

በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን አመራር እየታየ ያለው አንድ ችግር የአንድ ሰው የበላይነትን (ያ ሰው ዋና እረኛ ወይም ዋና ሽማግሌ ሊባል ይችላል) መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር አድርገው ከሚያቀርቡ ወገኖች በኩል ነው። ለዚህም የያዕቆብን፣ የጢሞቴዎስንና የቲቶን አገልግሎቶች እንደማስረጃነት ይቀርባሉ። ስለ ያዕቆብ፣ ጢሞቴዎስና ቲቶ አገልግሎት ባጭሩ እንመልከት፦

በሐዋ 15 ላይ በጉባኤ ሲናገር የምናገኘው ያዕቆብ የጌታ ወንድም የሆነው «ዐምድ» የተባለ ሐዋርያ (ሐዋ 12:17፣ ገላ 1:19፣ 2:6፣9) ነው እንጂ ሽማግሌ ወይም እረኛ ብቻ አልነበረም። ሌላው ያዕቆብ ቀደም ብሎ በሰይፍ ተገድሎአል (ሐዋ 12:1-2)።

የሐዋርያው ጳውሎስ ረዳት የነበረው ጢሞቴዎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው አገልግሎቱ የሐዋርያውን መልእክት ማድረስና በእርሱ ምትክ ሆኖ ተልዕኮን ለተወሰነለት ጊዜ መፈጸም ነው (1ጢሞ 1:3)። ጢሞቴዎስ በአንድ ቦታ የተሰጠውን ተልዕኮውን ሲፈጽም ሌላ ተልዕኮ ይሰጠው ነበር። እንዲሁም ጢሞቴዎስ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር በአንድነት ሐዋርያ ተብሎ ተጠርቷል (1ተሰ 1:1፣ 2:6)። ስለሆነም ብቸኛ መሪ ወይም እረኛ/ ዋና እረኛ ሰመሆኑ ማረጋገጫ የለም።

እንደ ጢሞቴዎስ ሁሉ ቲቶን የምናገኘው የሐዋርያው ጳውሎስ ተባባሪ በመሆን (2ቆሮ 8:23፣ ገላ 2:1) ለተወሰነ አገልግሎት ወደ አንድ ሥፍራ በሐዋርያው በመላክ ሲያገለግል ነው። ለምሳሌ በቀርጤስ (ቲቶ 1:5)። እንዲሁም በተለያየ ቦታ (2ቆሮ 1:5-7፣ 8:6፣ 12:18)። በአንድ ሥፍራ ተቀማጭ አልነበረም። የተሰጠውን የተወሰነ ተግባር ሲፈጽም ጳውሎስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ጠርቶታል (3:12)።

የጢሞቴዎስና ቲቶ አገልግሎት የሽምግልና ወይንም የእረኝነት ሥፍራቸው በግልጽ አልተጻፈም። የማደራጀትና የማስተማር ኃላፊነት እንደተሰጣቸው ግን እናውቃለን። ይሁን እንጂ ማደራጀትም ሆነ ማስተማር የሽማግሌዎችና የእረኞች ተግባር ሲሆን በሐዋርያው የተመረጠና የተላከ ደግሞ ይህን አገልግሎት ስለመፈጸሙ ግልጽ ነው።

አንዳንድ ጊዜም ሙሴን እንደ ዋና አረኛና ሰባዎቹን ሽማግሌዎች እንደ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አድርጎ በመቁጠር ከዚህ የአንድን ሰው የበላይ መሪነት መደገፍና የአሠራር ስልት መቀየስ ብዙም አይረዳም። በሁለት ምክንያት:- አንደኛ ይህ አሠራር ዋናውን የማደሪያውን ድንኳን አገልግሎት የዘነጋና ለእነ አሮንና ለካህናት ቦታ የሚያሳጣ የአመራር ዘይቤ ስለሚሆን፣ ሁለተኛ የሙሴ አገልግሎት ድርሻ አረኛነት ብቻ ስላይደለ ነው። የጳውሎስ አገልግሎት ከአረኝነት በላይ መሆኑ ግልጽ እንደሆነ ሁሉ የሙሴም የመሪነት አገልግሎት ከአረኝነት አገልግሎት የላቀ ነው።

ሙሴን እንደ አረኛ በመቁጠር ራእይ ተቀባይና የአንድ ብቸኛ መሪ ምሳሌ ነው ከተባለ የዘሩባቤልንና የነህምያን አመራር አብሮ ማጤን ያስፈልጋል። የሕዝብ አለቃ (መሪ) ለነበረ ለዘሩባቤል ምሪትና ምክር ከሊቀ ካህኑ በማስቀደም ይሰጠው ነበር። ለታላቁ ካህን ኢያሱ የተናገረና ምሪትን የሰጠ እግዚአብሔር ከይሁዳ ወገን ለሆነው ለዘሩባቤል አስቀድሞ ተናግሮአል እንዲሆም ለሕዝቡ ተናግሮአል (ሐጌ 1:1-)። ይህም ከእግዚአብሔር የሆነ ምሪትን (ራእይን) መቀበልን (1:1)፣ የመንፈስን ማነሣሣትን (1:14-15)፣ ማበረታታትን (2:1-፣ ዘካ 4:8-10) ሁሉ ያጠቃልላል። እዚህ ላይ ትልቁ ትምህርት የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በደካማው ዘሩባቤል ወይም በታላቁ ካህን በኢያሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ (ዘካ 4:6) መሆኑን ነው።

**ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን አመራር መሠረታዊ መርህ[107] ነጠላ ሳይሆን የጋራ፣ ብቸኛ ሳይሆን የወል ነው። በቤተ ክርስቲያን የአንድን ሰው የበላይነት አሠራር ከማን ተማርነው ያሰኛል?**

**ከመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ማስረጃ የምናየው ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ኃላፊነት የሽማግሌዎች መሆኑን ነው (ሐዋ 11:30፣ 14:23፣ 15:2-4፣ 20:17፣ 28፣ ፊሊ 1:1፣ ቲቶ 1:5-7፣ 1ተስ 5:12)። ሽማግሌዎችና እረኞች ተመሳሳይ ተግባር ስለሚያከናውኑ እረኞች ባሉባቸው ቤተ ክርስቲያኖች ደግሞ የመምራት ኃላፊነቱ የሽማግሌዎችና እረኞች ጉባኤ (ስብስብ ወይም ቦርድ) ነው። ሁለቱም ዋናዎች ናቸው (ዕብ 13:7፣ 17)።**

ከዋኖች መካከል ዋና የሚሆነው ተጠሪ ይሆናል፣ ቤተ ክርስቲያንን ይወክላል። ብቻ ዋናው ከዋኖቹ ያልተፈነጠረ ወይንም ለብቻው የወጣ አንዳይሆንና ለራሱ ለትዕቢት ማቆጥቆጥ ምክንያት ሆኖበት ጠልፎ እንዳይጥለው አጥብቆ መጠንቀቅ አለበት። እንዲሁም አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ተጠያቂነትና ግልጽ የአሠራር መርህ የሚታይበት በተለይም በገንዘብ አስተዳደር ለእግዚአብሔርና ለሰው አእምሮ የሚመች መንገድ የሚሠራበት መሆን አለበት።

**ትልቁ ጥያቄ ማን ዋና ይሁን? አይደለም። ትልቁ ጥያቄ ዋና የሆነው ዋናነቱን የሚያሳየውና ተግባሩን የሚያከናውነው እንዴት ነው? የሚለው ነው። ይህ ሰው በዋናነት ከመሥመር የወጣ እንደሆነስ? እርሱም ሰው ነውና ቢሳሳት፣ የስሕተት**

[107] ይህ ጸሐፊ ያደረገው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውጤት የሚያሳየው በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን አማራር በጎበረት መሆኑን ነው። The MAIN THRUST of the New Testament (and of the whole Bible) on church leadership is NOT singular/ one man leadership BUT corporate leadership.

አሠራር ቢያስገባ፣ እንዴት ነው በፍጥነት ሊስተካከልና ሊመሰስ የሚችለው? ማን ሐይ ይሰዋል? ተው ተመሰስ የመባያውስ ቀዳዳ (መንገድ) በየት በኩል ነው? የሚሉት ጥያቄዎች በሰከነ ሁኔታ ሊጤኑ ይገባል።

በተረፈ ግን የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር፣ በጎቹ የታላቁ እረኛ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ ራእይ የሚሰጠው ሰቤተ ክርስቲያን፣ ራእዩና ምሳሌው የራሱ የእግዚአብሔር መሆኑ እስከታወቀ፣ እረኞችና ሽማግሌዎች እርስ በርሳቸው ወንድማማች ሁሉም የአንድ ጌታ ባሪያዎችና አገልጋዮች መሆናቸውን ካልዘነጉ የሚቀረው በትጋት ማገልገል ብቻ ነው።

በገንዘብ ላይ ሰማዘዝ ቀጥተኛ እጅ ሊኖረው የሚወድና ተጠያቂነት የሌሰበትን አገዛዝ ሰሚናፍቅ ስው ቤተ ክርስቲያንን ራሱ እንደወደደና «የራሱን መልክ» ሰማስያዝ ሰሚፈልግ መሪ በፍቅርና በመመካከር፣ ግልጽ በሆነና ሥርዓትና ተጠያቂነት ባሰው አሠራር መሥራት ትልቅ ፈተና ሊሆንበት ይችላል። ፈተናስ ክርስቶስ በሞተለት ሕዝብ፣ የእርሱ አካል በሆነው ቤተ ክርስቲያንና ባከበረው ቅዱስ ሕዝብ ላይ «ገዥና ባለቤት» ሆኖ መቀመጡ ነው።

የዋናነቱ ቦታ «ለእኔ ይገባል ወይም ለእኔ ተፈቅዶልኛል» ብሎ አጠቃላይ በሆነ መንገድ ለመናገር ለዚህ «መብት ወይንም ፈቃድ» ያለው ከፍል መኖሩን ከመጽሐፍ ቅዱስ በእርግጠኝነት ለመናገር ያዳግታል። ቦታው የተሰጠው ለአገልግሎት እንጂ- ለወንበር አይደለምና።

በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአንድ በላይ እረኞች ሊኖሩ ሁሉም እረኞች «ዋና» ስለማይሆኑ የሽማግሌዎችና እረኞች ገባኤ (ስብስብ/ ቦርድ) ተጠሪ ወይም ዋና የሚሆነው ከመካከላቸው አንዱ ብቻ ነው። እረኞችን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠ እግዚአብሔር ከመካከላቸውም «ዋና» ሊሆን የሚገባውን እርሱ ያውቃል፣ ይሾማል፣ ቤተ ክርስቲያንም ይህን ትሰያለች።

**እንግዲህ የሚዛኑ እጅታ ያለው የከበሬታውን ስፍራ ሽማግሌው ወይም እረኛው የሚፈልግበት ምክንያት ላይ ነው። አንድ ሰው የከበሬታውን ስፍራ የሚፈልገው ከእግዚአብሔር ስለተሰጠው ወይንስ እርሱ ስለናፈቀው? የሰብሳቢነት ጸጋ (ችሎታ) ስላለው ወይንስ የወንበሩ ናፍቆት? እንግዲህ ሚዛኑ የት ላይ ነው?**

አብዛኛውን ጊዜ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን የሚያከናውኑት የራሳቸው ከሆነ መደበኛ ሥራ በተጨማሪነት በመሆኑ በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት እንደ እረኞች ሰፊ ጊዜ ለመመደብ ያዳግታቸዋል።

እረኞች ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «የተሰጡ» ስለሆኑና እነርሱም ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት የሚያገለግሉ በመሆናቸው በቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር የበለጠ ኃላፊነትና ተግባር ቢሰጣቸው አግባብነት ይኖረዋል። ሆኖም እረኛው አስተዳደራዊ በሆኑ ጉዳዮች ጊዜው ከተያዘበት ደግሞ መንጋውን የመጠበቁንና የመመገቡን ሥራ ማን ይሥራው? ለመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእረኝነት አገልግሎት ዋና ትኩረት ምንድን ነው? እረኛ ከበጎቹ ጋር መዛመዱን ሕሊና እንኳን ይነግረናል።

Dilemma ① ②

«ዋና» መሆንን በሚመለከት «ከተጻፈው አትለፍ» እንደተባለው፡-

- አገልግሎት የጸጋ ጉዳይ ነው፣ መንጋውን መጠበቅም ሆነ አገዛዝ ጸጋዎች ናቸው።

- ጥያቄው ሽማግሌ ወይስ እረኛ ማን ከማን ይበልጣል? ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትኛው ሥራ በማን ቢሠራ ይሻላል? ከዚህም በመነሣት በመሪነት ማን ይምራ? ማን «ዋና» ይባል? የሚል መሆን አለበት።

- የክበሬታ ወንበር ወይም ዋና መሆን - የአገልጋይነት ሥፍራ ነው እንጂ የገሾርነትና ከተጠያቂነት በላይ መሆን አይደለም።

- የእረኛና የሽማግሌ አገልግሎት ተመሳሳይ መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም በሥራ ክፍፍል[108] ላይ እረኞች ከበጎቹ ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው አገልግሎት ቢመደቡ በጣም አግባብ ነው።

ሽማግሌዎችም ሆኑ እረኞች በየተራም ይሁን በቋሚነት «ዋና» ቢሆኑ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ በአመራር ዘይቤው (ወይም ስልቱ) ላይ ነው። ትኩረቱ እንኪንስ ዋና ተብሎ የሚመረጠው መሪ ቀርቶ በአጠቃላይ ዋናዎቹ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩት እንዴት ነው? የሚለው መሆን አለበት።

**ቅንነት በሌለበት የሰብሳቢ ወንበር** ስልት ባለው የስብሰባ አመራር «ጥበብ» የራስን ሀሳብ ለማስወሰን ይረዳል። የቤተ ክርስቲያን አሠራር ቅንነት ሲጐድለው የጉባኤ መሰብሰብ ለቃለ ጉባኤ ያህል እንደሆን እንጂ ስብሰባው የሚካሄደው አስቀድሞ በሰብሳቢውና በደጋፊዎቹ የተወሰነን ሀሳብ ለማስጸደቅ ይሆናል።

ቅንነት በሌለበት የሰብሳቢውን «ጥቅም» የሚነኩ ወይንም የተለያዩ አመለካከት ያሉባቸው ቁልፍ ጉዳዮች ለምክክርና ለውሳኔ የሚቀርቡት ቀንና ሁኔታ ተጠብቆ፣ በተለይም እውነተኛነትንና ግልጽነትን የሚወዱና ጠንከር ያለ ሀሳብ የሚያቀርቡ የጉባኤ አባሎች በሌለበት ቀን ይሆናል። እንደ ምድራዊ አሠራር አንድ ሀሳብ ውሳኔ ሆኖ እንዲያልፍ ለተወሰኑት የጉባኤ አባላት አስቀድሞ ማስረዳትና ማባበል[109] ሊኖር ይችላል። ይህም የክበሬታው ወንበር የሚናፈቅበት አንዱ ምክንያት ይሆናል። ይህ የክርስቶስን ሳይሆን የራስን መፈለግ ነው። ይህ ክርስቶስ ያስተማረው ስልት አይደለም። ታዲያ ይህን «ጥበብ» ከማን ተማርነው?

ግልጽ የአሠራር ሥርዓት በሌለበት ለወገኔ ይጠቅማል የሚል አድሎአዊ አሠራርን ይጋብዛል፣ የእግዚአብሔር ቤት ገንዘብ ይባክናል፣ ሥራው ይተጓጐላል፣ የእግዚአብሔር ስም ይሰደባል።

---

[108] የሥራ ክፍፍል፡- በአንድ ጉበረት (team) ውስጥ እያንዳንዱ አባል ባለው ዝንባሌ ወይም ችሎታ (ማለትም ጸጋ) የሚይዘው / የሚሰጠው የሥራ ድርሻ ነው።

[109] lobby ማድረግ

## 14.3.7 የቤተ ክርስቲያን አመራር መርሆዎች (መፍትሔዎች)

በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየታዩ ላሉ ችግሮች የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል።

### ሀ. አንድ ቢሮ/ ተመሳሳይ ተግባር

በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን በሽማግሌዎችና በእረኞች መካከል ያሉ ችግሮች በአብዛኛው በጥቂት ሰዎች የግል ባሕርይ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ይታያል። እነዚህ ችግሮች በሁሉም ቤተ ክርስቲያኖችና አካባቢዎች የሚታዩ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በፍቅር፣ በመከባበር፣ በአንድ ሀሳብ ሆነው የሚሠሩ አሉና።

ሽማግሌ የሚለው ቃል በዕብራይሰጡ (ሲይብ)[110] ማለት ሲሆን ይህም በዕድሜ ከፍ ማለትን፣ የሕይወት ብስለትንና ልምምድን የሚያመለክት ነው። ሽማግሌ ከቀደመው ጊዜ ጀምሮ በእስራኤላውያን ታሪክ፣ በሙሴ፣ በኢያሱ በሌሎችም መሪዎች ጊዜ የነበረ ወደ አዲስ ኪዳንም የተሸጋገረ መጠሪያ ነው። በአዲስ ኪዳን በየቤተ ክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ሲመረጡ እንመለከታለን። ቤተ ክርስቲያን እያደገች ከኢየሩሳሌም ወደ ይሁዳ ከዚያም ወደ ዓለም ሁሉ ስትሄድ ኤጲስቆጶስ የሚለው የግሪክኛ ስያሜ ለሽማግሌዎች ውሏል።

ሽማግሌነት ብስለትን፣ በዕድሜ ማደግን ሲያመለክት፣ ኤጲስቆጶስ ደግሞ የበላይ ሆኖ መመልከትን፣ መጠበቅን ያመለክታል። እንዲሁም እረኛ የመጠበቅን፣ የመመገብንና ማሰማራትን ተግባር ወይም ሥራ ያመለክታል። መጽሐፍ ሽማግሌዎችን መንጋ ጠብቁ ይላቸዋል (ሐዋ 20:17-28 1ጴጥ 5:1)። ይህም የሽማግሌዎች ተግባር እረኝነት መሆኑን ሲያመለክት ነው።

ስለዚህ ሽማግሌ፣ ኤጲስቆጶስና እረኛ የሚሉት ቃላት ከተግባር አንጻር ተወራራሽ እንደሆኑ ያሳያል። ሽማግሌዎች የሕይወት ብስለትን፣ ኤጲስቆጶስ የበላይ ሆኖ መጠበቅንና መምራትን እንዲሁም እረኝነት መመገብን፣ ማሰማራትን ያመለክታል። ስለዚህ በተግባር አንድ ናቸው። ሽማግሌዎች፣ ኤጲስቆጶሳት ወይም እረኞች ሁሉም ለአንድ ተግባር በቃሉ መመዘኛ (1ጢሞ 3:1-፣ ቲቶ 1:5) የሚመዘኑና የሚሾሙ ናቸው። ሽማግሌዎችና እረኞች ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው የአንድ ቢሮ ሠራተኞች/አገልጋዮች ናቸው።

---

[110] siyb (seeb); , to become aged, i.e. (by implication) to grow gray: KJV-- (be) grayheaded.

## ለ. ተከታይነትና የባሪያ አገልጋይነት

ሁልጊዜም የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር መሆኑን አስመዘንጋት የጥሩ መንፈሳዊ መሪ ባሕርይ ነው።

የቤተ ክርስቲያን አመራር በመሠረቱ (በይዘቱ) እግዚአብሔር ገዢ የሆነበት (ቲዎክራቲክ) ነው። ይህ ጸሐፊ እንደሚያገናዝበው ቲዎክራቲክ የሚለው የአገዛዝ ዓይነት በብሉይ ኪዳን ብቻ የነበረ የአመራር ዓይነት አይደለም። እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳንም መሪዎችን ይጠራል፣ ይመርጣል፣ ይቀባል፣ የጸጋ ስጦታዎችን ይሰጣል። ብቃታቸው እርሱ ነው። መመረጥ፣ መጠራት፣ መቀባት፣ መሾም በእግዚአብሔር ከሆነ ሁሉን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው። እንግዲያውስ እግዚአብሔር የመረጠውና የሾመው ሰው ከእርሱ እየሰማ በእርሱ ፈቃድ መሠረት ማገልገል ይጠመቅበታል። ከትልቅ አለቃ ሥር የሆነ አገልጋይ ነውና።

መሪዎች የተጠሩት የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥር[111] ሆነው እንዲያገለግሉ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ገዢ፣ ራስ፣ የበላይ፣ አለቃ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን የሚሾሙት መሪዎች ቃሉ እንደሚል ጌቶች ሊሆኑ አልተፈቀደላቸውም (1ጴጥ 5:3)። ይልቁንም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ማለት እያንዳንዱ ክርስቲያን የእርሱ ራስ ክርስቶስ መሆኑን እንዲያውቅ መርዳትና ማሳየት ከአገልጋዮች ይጠበቃል (ቆላ 2፣19)።

በቤተ ክርስቲያን ያሉ አለቆች ወይም መሪዎች የተሰጣቸውን ሥልጣን በሥራ ላይ የሚያውሉት ራሳቸውን የቤተ ክርስቲያን ራስ ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ ፊጽሞ በማስገዛትና ምንም ያህል መሪዎች ቢባሉ እነርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች መሆናቸውን አጥብቀው በመረዳት ነው። ይህም ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በየአጣቢያው በሚያገለግሉ አገልጋዮች በኩል ይገዛል። ገዢው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አፈጻጸሙ በሰዎች በኩል ሊሆን ይችላል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከበር ውጭ እስካልተደረገ ድረስ (ራእ 3:20) ሁልጊዜ በሕያውነት በቤቱ ላይ አለ። ቃሉ ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» (ማቴ 18፣20) ይላል። እንዲሁም በራእ 1፣10-20 ሐዋርያው ዮሐንስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ማለትም በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሲመላለስ አይቶታል። ዛሬም ቢሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን በሕያውነት ይመላለሳል። ቤቱ የእርሱ ስለሆነ መሪዎች ባለ አደራዎች እንጂ ባለቤቶች አይደሉም። የዚህ ጌታ ተከታዮችና ባሪያዎች ናቸው። ይህን ማስተዋል በግል ሕይወትና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚነሣ ከብዙ ችግር ያድናል።

መሪ የሚመረጠው ለአገልጋይነት ነው። ሆኖም ይህ ሰው ከመቆየት የተነሣ የአመራር ባሕርይው ቢቀይር፣ ወይም ያልተሰጠውን ኃላፊነት ቢወሰድ ወይም

[111] Under shepherds

ቢነጥቅ ይህ ለጥፋት ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ መሪዎችን ወደ መታበይ የሚያደርሳቸው የማይገባቸውን ክብር/ «ስግደት» የሚሰጣቸው ራሱ ሕዝቡ ወይም ምዕመኑ ነው። አንዱ በአንድ ቦታ «ሰዎች በአንድ ወቅት ለአገልጋይነት የመረጡትን ይክቡ ይክቡና ወደ አምባገነንነት እንዲለወጥ ካደረጉት በኋላ እንደገና ከሥልጣን ያወርዱታል» እንዳለው።[112]

## ሐ. ወንድማማችነት

መሪዎች ሁሉም በጌታ ወንድማማች የሆኑ በአገልግሎት አኩያሞችና የአንዱ ጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች ናቸው።

በጎበረት ወይም በወል የሚመሩ መሪዎች የአንዱ ጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎችና እርስ በርስ ወንድማማች በመሆናቸው ሲመሩ ሳለ አንደኛው ወንድም ሌላውን መካሪ፣ ከመስመር እንዳይወጣ ተቆጣጣሪና እርስ በርስ ተደጋጋፊ ናቸው። አሠራሩ አንዲህ ሲሆን በብዙዎች ያለውን ልዩ ልዩ ጸጋ በመክፋፈል ለቤተ ክርስቲያን መልካም የሆነ ነገር ይወጣል። ይህም ልዩ ልዩ ጸጋን የሚሰጥ የእግዚአብሔር መንፈስ አሠራር ነው። ሁሉ በመመካከርና በመደጋገፍ ለመተናነጽ ሲሆን ወደ እግዚአብሔር መላት ለማደግ ይረዳል። ስለሆነም ዋናው መሪ ከእኩያዎች መካከል ቀዳሚ ነው።[113]

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአጠቃላይ አንዱ ለሌላው በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛ ሲሆን የሚገባ ሲሆን (ኤፌ 5:21) በተለይ ደግሞ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸውን አገልጋዮች ምዕመናን እንዲያከብሯቸው፣ እንዲታዘዙላቸው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው (1ተሰ 5:12-13፣ ዕብ 13:17)።

## መ. በምሳሌነት መምራት

---

[112] Quoted from Plato in "The Republic", by Kevin, Ibid.

1. If there is no leadership, people select someone and nurse him to greatness.
2. In this time they call him their benefactor.
3. In time he changes from such to be a tyrant - self-serving now because of the deification by the people.
4. Tyranny now produces revolution.
5. People then pull him down from the pinnacle of power. The same society who nursed this leader to greatness will also pull him down.

[113] First among equals. To elaborate the idea some site the way the geese fly as an example. «A flock of geese in flight always have a lead bird, the others following in formation accordingly. The lead bird takes the direction for the flock.» የሚበሩት መስመር ጠብቀውና በአንድነት ነው። ፊት የምትመራዋ አንድ ወፍ ትኖራለች። እርሷ ፊት ትበርራለች፣ አቅጣጫ ታሳያለች ሌሎቹ ከእርሷ በኋላ ይመጣሉ እርሷን ይከተላሉ፣ ይሄዳሉ። ከተወሰነ ርቀት ወይም ቆይታ በኋላ መሪዋ ወፍ በሌላ ልትቀየር ትችላለች።

መሪዎች እርስ በርስ መከባበርን ለምዕመንና ሊያሳዩ ሲገባቸው በአንዳንድ ቦታዎች በተለይ ከሥልጣን ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እርስ በርሳቸው ባለመግባባት የሚጣሉበት ሁኔታ ይታያል። ሽማግሌዎች እርስ በእርሳቸው ወይም ከአረኛው ጋር የማይስማሙ ከሆነ ምዕመኑ ከእነርሱ ምን መልካም ነገር ይማራል? መሪዎች አንድነትና ፍቅር ከሌላቸው የቤተ ክርስቲያኗ ሰላምና አንድነት እንዴት ይጠበቃል? ጥቂት መሪዎች አብረው መሥራት ሳይችሉ ሌሎች አገልግሎቶች እንዴት በፍቅር መሥራት ይችላሉ? እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ጉባኤው ቢለያይ አያስደንቅም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጎበረት አገልግሎት እንዲኖር መደማመጥ፣ መከባበርና በምሳሌነት መምራት ይገባል። ስለዚህ መሪዎች፣ ሽማግሌዎችና አረኞች በአንድነት አንዱ ሌላውን በማክበርና በመከባበር፣ በፍቅር፣ ለመንጋው ምሳሌዎች በመሆን በቅንነት የሚሠሩ፣ የራሳቸውን ጥቅም ባለመፈለግ የሚያገለግሉ መሆን አለባቸው።

## ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአመራረጥ መመዘኛን መጠበቅ

ሽማግሌዎችን መምረጥ ትልቅ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ተግባር ነው። መመዘኛ ተሰጥቷልና። ሽማግሌዎች የበሰሉ፣ አዲስ ክርስቲያን ያልሆኑ፣ ከጌታ ጋር የቆዩ፣ ማስተማር የሚችሉ፣ ለመንጋው የሚጠነቀቁ፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚያስቡና ሌሎችንም የቤተሰብ አስተዳደር መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

አሁን በአንዳንድ ቦታዎች እንደሚታየው በሽማግሌዎች ምርጫ ዋናው ትኩረት በየተራ የመምረጥ (ወይም አንዱን አሳርፎ ላልደረሰው መስጠት) ከሆነ መለኪያው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመቆየት ወይም የዘመን ርዝመት መጠን ብቻ ወደ መሆን ይወርዳል። አንዳንድ ጊዜ ተረኞቹ መመዘኛውን የማያሟሉ፣ ለቦታው የማይመጥኑ ወይም ሸክም የሌላቸው ሲሆኑም ይታያሉ።

ስለሆነም ለአገልግሎት ዘመን (ለምሳሌ 3 ዓመት) «የተመደበው ጊዜ ካለቀ በኋላ ተራውን ለሌላ ይለቃል» ከሚለው አሠራር ጋር በአገልግሎት ላይ የነበረው ሽማግሌ ከመውረዱ በፊት አገልግሎቱ ቢመዘን የተሻለ ይሆናል። በቢሮ (አገልግሎት) ላይ ያለው ሰው «መቀጠል አለብኝ» ብሎ «የይገባኛል» ጥያቄ ማንሳት አይችልም። ሆኖም ግን በአገልግሎቱ ፍሬ ታይቶበታል? ለፍቅር፣ ለአንድነትና ለእድገት ምክንያት ሆኖአል? ሌላ አገልግሎት ዘመን ቢቀጥልስ በእርሱ፣ በቤተሰቡና በሥራው ላይ ችግር ይኖራል? እርሱስ ለመቀጠል ፈቃደኛ ነው? የሚሉ መመዘኛዎችን በማዘጋጀት መመዘንና እንደሚደረስበት ውጤት ማስተናገድ የተሻለ ይሆናል።

በሌላም በኩል ለሽምግልና ለመመረጥ መለኪያው ሀብት ወይም የንግግር ችሎታ ወይም በሌላ መሥሪያ ቤት ያለው የኃላፊነት ደረጃ ወዘተ መሆን አይገባውም። መለኪያው በእግዚአብሔር ቃል (1ጢሞ 3:1-7) የምናየው ነው። አንድ ሰው ምንም ያህል የተማረ ቢሆን ወይም በሌላ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊነት ቢኖረው ወይም ሀብታም ቢሆን ለምሳሌ አዲስ ክርስቲያን ከሆነ በእግዚአብሔር ቤት ለመሪነት ገና ነውና አይመረጥም ማለት ነው። እንዲሁም ለማስተማር የሚበቃ መሆኑና መልካም ምስክርነት ያላው መሆኑ ታይቶና ተፈትሾ ነው ለሽምግልና መመረጥ ያለበት።

## ረ. የራእዩ ባለቤት ሰጪው ነው

ስለ መክሊትና ጸጋ ስጦታ አጠቃቀም ስንነጋገር በሽማግሌዎችና እረኞች ጉባኤ ሙሉ ጊዜውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከመስጠቱ አንጻር የመምራቱ ኃላፊነት ለእረኛው ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ ሳለ በጉባኤው ውስጥ በእረኛው ከሚታየው ይበልጥ የመምራት ጸጋ (ችሎታና ልምድ) ሊኖር እንደሚችልም ማጤን ይገባል። በብዙ ሁኔታም ታይቷል። እግዚአብሔር ጸጋን ይሰጣል። ጸጋ ደግሞ በመለማመድ ይዳብራል።[114] ስለሆነም «ካለ እረኛው ሌላ ሰው ሰብሳቢ መሆን የለበትም» ብሎ ማክረር በጎብረቱ ውስጥ የሚገለጠውን ጸጋ አለማስተናገድ ይሆናል። እንዲህ ያለው አሠራር ደግሞ በሕግ የተገደበ የጸጋ አጠቃቀም ወደ መሆን ይወስዳል።

በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች እንዳሉ የታወቀ ሲሆን በርናባስንና ሰያልን የመለየት ትልቅ አገልግሎት የፈጸሙት በጎብረት ባሉበት ጊዜ ነው በዚህ ጊዜ ሰብሳቢው ማን እንደሆነ የሚያመለክት ነገር አናገኝም። በጉባኤ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ምሪትንና ራእይን በወደደው ዕቃ በመሪው፣ በነቢዩ ወይም በሌላም ሰው በኩል ሊሠራ ይችላል። ይህ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነው።

እንግዲህ ረእዩ የሰጪው የእግዚአብሔር ነው እንጂ የተቀባዩ የእረኛው፣ ሽማግሌው፣ ነቢዩ፣ ወዘተ አይደለም። እነርሱ አስተላላፊ መሣሪያዎች ናቸው።

## ሰ. በጎብረት መምራት

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችባቸው ቦታዎች ሁሉ ሽማግሌዎች በጎብረት ይመሩ እንደ ነበረ ከአዲስ ኪዳን እናነባለን። በኢየሩሳሌም (ሐዋ 16:4)፣ በኤፌሶን (ሐዋ 20:17-28)፣ በፊሊጵስዩስ (ፊሊ 1:1)፣ በአንጾኪያ (ሐዋ 14:22-23)። ሐዋርያው ጳውሎስ በየቦታው ሽማግሌዎችን ይሾማል። በየቦታው የምናየው አንድ ሽማግሌ አይደለም ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን ነው።

በመሪዎች ጉባኤ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም ዋና ሽማግሌ ወይም ቀዳሚ ፓስተር፣ ወዘተ የሚሆነው ሰው በጎብረት ማገልገልን የሚወድ፣ በመሪዎች መካከል ቀዳሚ፣ በወንድሞች መካከል ፊት የሚቆም ወንድም ማለት ነው። ይህ ሰው በወንድሞቹ ላይ የሚሰለጥን፣ ወንድሞቹን የሚገዛ እንዲሁም የአሠራር ሥነ ሥርዓትን ጥሶ ለብቻው ተነጥሎ የሚወጣ «ዲዮጥራጢስ» አይደለም።

በመሪዎች ጎብረት ወይም ቦርድ ውስጥ ያሉት ሽማግሌዎችና እረኞች የአመራርን ጸጋ የሚያከናውኑበት ልዩ ልዩ ጸጋ ሊሰጣቸው ይችላል። መሪዎች

[114] ወደ ሽምግልናና እረኝነት ለሚመጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን አመራርን በሚመለከት ሥልጠናዎችን ልታዘጋጅላቸው ይገባል።

በአማኝነታቸው እኩል ናቸው። በቢሮ ደረጃ (በአገልግሎት) እኩል ናቸው። በባሪያነታቸው እኩል ናቸው። ግን አገልግሎታቸው እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን ነው። *መሪዎች* እኩል ወንድማማች፣ እኩል የጌታ ባሪያዎች ሆነው ሳለ እያንዳንዱ ግን በተሰጠው ጸጋ መጠን ያገለግላል። በተሰጠው መክሊት ብዛት ይነግዳል። ስለሆነም እያንዳንዱ የተሰጠው መክሊት ወይም ጸጋ «መጠን» እኩል ነው ማለት አይደለም። የጎበረቱ እያንዳንዱ አባል በተሰጠው ጸጋ መጠን ሊያገለግል በቤተ ክርስቲያን ጤናማና የተሟላ አመራር ይኖራል።

## ቀ. የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን በአመራር ማስገባት

ከእረኞች ሌላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ሁሉ አግባብ ባለው መንገድ በአመራር ውስጥ የሚሳተፉበት ስልት ቢቀየስ መልካም ይሆናል። ጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ስጦታዎች (ሰዎች) (ኤፌ 4:11) በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ከመሪዎች ጋር አብረው መምከርና አብረውም መጸለይ ይገባቸዋል። ይህም ከጥሪያቸው ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው። እነዚህ ሰዎች የተጠሩት ለቤተ ክርስቲያን ጉዳይና የተሰጡትም ለቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ነው።

የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች እንደ ምዕመናን በዓመት አንድ ጊዜ (ወይም ሁለት ጊዜ) *ሪፖርት* ስሙ የሚባሉ ብቻ መሆን አይኖርባቸውም። እንዲሁም ከመሪዎች መመሪያ (ትዕዛዝ) ለመቀበል ብቻ የሚጠሩ ሳይሆኑ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሰዩና ሕይወታቸው ከቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዘ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ተግባር ከፍ ያለ ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል።

የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን በአመራር ማስገባት ማለት ቤተ ክርስቲያን ቀልጣፋ የአመራር ስልት በመዘርጋት የቤተ ክርስቲያንን ዋና ተልኮዎች እቅድና የተግባር አፈጻጸምን በሚመለከቱና መሰል ቁልፍ ስብሰባዎች ላይ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ከአመራሩ ጋር የሚሰበሰቡትና የሚመክሩበት አሠራር ነው። እነዚህ ስብሰባዎች የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን ማግለል የሰባቸውም። ያአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ይህን በሚያሳይ መንገድ ሊቀረጽ ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር በአንዳንድ አካባቢዎች ገና አይታይም።

ሆኖም በአተገባበሩ ላይ ያስፈልጋል። ይህ ሲባል በሽማግሌዎችና እረኞች ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ሁልጊዜ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በሙሉ ወይም በተወካዮቻቸው በኩል ይገኙ ማለት አይደለም። ይህ ቢሆን አንድም የተጠሩበትን ዋና ዓላማ ሊያዘናጋባቸው ያለዚያም መብትን ለማስጠበቅ የሚደረግ ውክልና ያስመስለዋል።

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የአመራር ኃላፊነት ያለው በሽማግሌዎችና እረኞች ላይ ነው። እነርሱ በአመራራቸው ሊተማመኑ ይገባል። ሰዎችን በተሰጣቸው ጸጋ ማስማራት ካለና እርስ በርስ መቀባበልና መተማመን ካለ ወንጌላውያንና ሌሎች የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን በየጊዜው በሚደገረጉ የመሪዎች ስብሰባዎች ላይ መገኘት አስፈላጊ አይሆንም። ቤተ ክርስቲያን የራስን መብት ማስጠበቂያ መድረክ (ሸንጎ) አይደለችምና።

## በ. በትንሽ ብዙ በመሥራት

በርካታ ታላላቅ ድርጅቶች የሚመሩት በስብስባ ብዛት ሳይሆን በአሠራር ሥርዓትና ቅልጥፍና ላይ በማትኮር በትንሽ ብዙ በመሥራት ነው። በቤተ ክርስቲያንም ቀልጣፋ የአሠራር ዘዴንና የስብሰባን ሥርዓት መንደፍ በጣም አስፈላጊ ነው። ያለዚያ መሪነት ማለት «ስብሰባ ብቻ» ማለት ይሆንና በጎቹ ሳይለማሩና ሳይመገቡ ይቀራሉ።

ከዚሁ ጋር በቤተ ክርስቲያን ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር የሰጠ መጋቢ (ወይም መጋቢዎች) ቢኖሩ በጣም ጠቃሚ ይሆናል። ለሁሉም አካባቢዎችና ቤተ ክርስቲያኖች በአንድ ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ መልስ ለመስጠት ቀላል ባይሆንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚመድብ ሰው (እረኛ) ካልተገኘ ወይም ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት ከልተበጀ (ወይም ሁለቱም መንገዶች በአንድነት ከልተቀየሱ) በስተቀር የሥራ መበደልና መጓተት እንደሚኖር ግልጽ ይሆናል። በሌላም በኩል እረኛው ዋና ተግባሩ የበጎች ጉዳይ ሆኖ ሳለ ቀኑን ሙሉ በቢሮ ሥራ ከተጠመደ እርሱም በተራው የጊዜ ጥበት እንደሚያጋጥመው መዘንጋት የለበትም።

## ተ. ጤናማ የአሠራር ሥርዓት ማበጀት

ቤተ ክርስቲያን ሕያው አካል ስትሆን በምድር ላይ ተግባሯን ለመፈጸም የሚያግዛት ድርጅታዊ አቋም[115] ይኖራታል። ይህ ድርጅታዊ አቋም በመተዳደሪያ ደንብ የሚገለጽ ይሆናል። በተጨማሪም ጤናማ የአሠራር ሥርዓትን የሚያመለክቱና አስፈላጊነታቸው ታምኖባቸው በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ሊገለጹ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉት መዘንጋት አይኖርባቸውም።

- አቅድ (የሥራ ዝርዝርና በጀት በወጪ ዓይነት)
- የመሪዎች የኅብረት አመራር (መለኪያ ተበጅቶለት)
- ተጠያቂነት (የማያሳፍር አሠራር)
- የአሠራር ግልጽነት፣ (አግባብ ያለው ሰው/ቡድን ሊያየው በሚችለው ሁኔታ የሚቀመጥ ሰነድና መዛግብት)
- የአሠራር አዲት[116] (የቤተ ክርስቲያንን ዋና ተግባሮች ከበጀት አጠቃቀም ጋር በማነጻጸር)
- የገንዘብ አዲት[117] (አጠቃላይ አዲትና በተለይ በዋናው መሪ በኩል/ ወይም በእርሱ ተእዛዝ በተደረጉት ወጪዎች ላይ ከመመሪያና ከበጀት አንጻር)
- ሪፖርት (ዓመታዊና እንደ አስፈላጊነቱ በተወሰኑ ወራት)

[115] Organizational structure
[116] Operational or programme audit
[117] Finanacial Audit

በእነዚህና በመሰል ቁልፍ የአሠራር ስልቶች በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንን ድርጅታዊ ይዘትና ጤናማነት መከታተልና መጠበቅ ያስፈልጋል።

የሂሳብ አዲት እንዳለ ሁሉ የአሠራር ኦዲትም አለ። ይህም በመሪዎች (ወይም በሕዝቡ) በሚመረጡ የታመኑ አባሎች ወይም ቀደም ብለው በመሪነት ካገለገሉት መካከል በሚመረጡ ሰዎች ሊከናወን ይችላል። ይህ ማንንም አይጎዳም፣ ቤተ ክርስቲያንን ግን ይጠቅማል። የዚህ አዲት ዓላማ ጥፋተኛውን ለመፈለግ ወይም ስህተትን ለማውጣት ሳይሆን ስህተት ከታየ እንዳይቀጥል ለመታረምና የተሻለ አሠራርን ለመንደፍ ነው። መሪዎች በዋናነት ተጠያቂነታቸው ለእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ለሕዝቡም (ለቤተ ክርስቲያን) መሆኑንም በመገንዘብ ጤናማነትን ለመጠበቅ የገንዘብ አዲት ሊደረግ ይገባል።

በአጠቃለይ የቤተ ክርስቲያን አመራር ዓላማው እግዚአብሔርን የማክበርና በኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት በትሕትና ራስን ዝቅ አድርጎ ለማገልገል መሆን አለበት። የአስተዳደራዊ አደረጃጀቱ በጎችን ለመጠበቅ የሚያግዝ የአመራሩ ትኩረት የበጎች ጉዳይ መሆን አለበት። ስለሆነም በመንጋው ውስጥ ያሉትን በጎች ሁሉንም በጎብረትና እያንዳንዳቸውን በነጠላ ለመመግብ፣ ለመጠበቅና ለማስማራት የሚያስችለው አመራር የትኛው ነው? በማሳ ላይ እንደሚገኝ የፍሬ ዛፍ እያንዳንዱ ተክል እንክብካቤው ሳይጓደልበት ውኃ የሚያገኘው በየትኛው የአሠራር መስመር (ቦይ) ነው? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ሊያገኙ የተሻለ አመራርና አሠራር ይኖራል። የቤተ ክርስቲያንን አመራር በዓለም ከሚታየው ገዥነት ልዩ የሚያደርገውም ይህ የአገልግሎትና የአመራር መርህ ነውና (ማር 10:42-45)።

## 14.3.8 የዋናዎቹ መሪዎች የአገልግሎት ዋና ትኩረት - የበጎች ጉዳይ

የእረኞች አለቃ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (1ጴጥ 5:4) ነው። መጽሐፍ «በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን» (ዕብ 13:20)፣ ትልቅ እረኛ (ዕብ 13:20) «የነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ» (1ጴጥ 2:25) እንደሚል።

ጌታ ኢየሱስ «ግልገሎቼን አሰማራ»፣ «ጠቦቶቼን ጠብቅ»፣ «በጎቼን አስማራ» ብሎ ጴጥሮስን ሲያዘው (ዮሐ 21:15-17) ተግባርና ኃላፊነት ሲሰጠውና አደራ ሲቀበል እናያለን። **አስተዋይ አገልጋይ አጥብቆ «ቄ»ን («ኤ»)ን ልብ ይበል። ግልገሎች፣ ጠቦቶች፣ በጎች የታላቁ እረኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው።** ስለሆነም እርሱ ግልገሎቼ፣ ጠቦቶቼ፣ በጎቼ ይላቸዋል። ጴጥሮስና ሌሎች አገልጋዮች ከታላቁ እረኛ በአደራ የተቀበሏቸውን በጎች በማሰማራትና በመጠበቅ እንደ ታላቁ እረኛ ፈቃድ የሚያገለግሉና ለእረኛው በታማኝነት የሚያስረክቡ ናቸው። መንጋው የእግዚአብሔር ነው (1ጴጥ 5:2)።

በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር እስራኤልን «በጎቼ» ብሎ ይጠራቸዋል (ሕዝ 34:6፣8፣10)። እረኞች ሲስንፉ ወይንም ራሳቸውን ማስማራት ሲጀምሩ በጎች

ይበተናሉ። መልካሙ እረኛ እግዚአብሔር ግን ለመንጋው ይጠነቀቃል። ቃሉ እንደሚል «የጠፋውን እፈልጋለሁ፣ የባዘነውንም እመልሳለሁ፣ የተሰበረውን እጠግናለሁ፣ የደከመውንም እጸናለሁ፣ የወፈረውንና የበረታውንም አጠፋለሁ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ» (34:16)። እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ሲናገር «እረኛ በተበተኑ በጎች መካከል ባለጊዜ መንጋውን እንደሚፈልግ፣ እንዲሁ በጎቼን እፈልጋለሁ» (ሕዝ 34:11) ይላል። እንዲሁም እግዚአብሔር «መንጋውን እንደ እረኛ ያለማራል፣ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፣ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል» (ኢሳ 40:11)።

ስለሆነም የእረኝነት አገልግሎት የእግዚአብሔርን እረኝነት በምሳሌነት የሚከተል ነው። በጎች በበረት (በጉሮኖ) ውስጥ ሆነውና ተሰባስበው በጤንነትና በብርታት እንዲኖሩ በመካከላቸውም የሚነሣውን በደል በመዳኘት በሰላም እንዲሰማሩ ማድረግ የእረኞች ኃላፊነት ነው። እረኛ መንጋውን በልብ ቅንነት የሚጠብቅ (መዝ 78:72፣ ኤር 31:10)፣ ከነጣቂ አውሬ የሚያድን (አሞ 3:12)፣ ከመንጋው የማይለይ (ዮሐ 10:11-16፣ ዘካ 11:17) ነው። እረኛ መንጋውን የሚያሰወጣና የሚያስገባ (ዘኁ 27:17)፣ እንዳይበተኑ የሚሰበስብ (ኢሳ 13:14፣ ኤር 30:1-3፣ ሕዝ 34:4) ነው። **የእረኛውና የሌሎችም ዋና መሪዎች ትኩረት የበጎች ጉዳይ ነው።**

የእግዚአብሔር ፈቃድ መንጋው እረኛ እንደሌላቸው በጎች እንዳይጨነቁና እንዳይጣሉ (ማቴ 9:36)፣ ያነከሰውም እንዲፈወስ (ዕብ 12:13) ነው። እግዚአብሔር በቤቱ ሰሚሾማቸው ለሎች የሚሰጣቸው ትልቁ ተግባርና የአገልግሎት አደራ ወይም ኃላፊነት የእግዚአብሔር የሆነውን ሕዝብ ማለትም በጎቹን ማሰማራት፣ መመገብ፣ መጠበቅ ነው። ስለሆነም አገልጋዮች ራሳቸውን ከራሳቸው ከማስተያየትና ከመመዘን ተቆጥበው (2ቆሮ 10:12-18) በትዕግሥትና በትሕትና ሊያገለግሉ ይገባል።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ባልጠበቁ፣ ባልመገቡና እንደ ሀሳቡ ባላገለገሉ አገልጋዮች ላይ ይቆጣል (ዘካ 10:3)። ፈቃዱን እንደሚገባ የማያገለግሉትን አገልጋዮች በመሻር በምትካቸው ሌሎችን ከጉረቤታቸው እንደ ሀሳቡ የሆኑትን የታመኑትን ያስነሳል (1ሳሙ 2:35፣ 3:20፣ 13:14፣ 15:28፣ ሐዋ 13:22)። በአንባሩ ደግሞ እንደ ሌዊ ቃል ኪዳናቸውን የጠበቁና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አገልጋዮች ፍሬያቸው ብዙ ይሆናል (ሚል 2:4-6)።

**ስለሆነም** መሪዎች እንደ ዲዮጥራጢስ እምቢተኞች፣ የክፉ ምሳሌዎች፣ በክፉ ቃል የሚሰፈልፉ፣ ከሌሎች መንፈሳዊያን ለሎች ጋር ጎብረት ለማድረግ የማይፈልጉ፣ አንድነትን የሚያዳክሙ፣ መልካም የሚያደርጉትንም በእነርሱ ሥር ስላልሆኑ ለበብ እየፈሰጉ ከቤተ ክርስቲያን የሚያገልሉ (3ዮሐ 9፣11) እንዳይሆኑ ራሳቸውን መመርመር ይገባቸዋል።

**የመሪዎች ኃላፊነት የሚመሯቸውን ለሎች ሁሉ ወደ ክርስቶስ እንዲመለከቱ ማድረግ** ሆኖ ላለ ምእመናን ለመሪዎቻቸው ፈቃድ የሚኖሩ አድርጎ በመቁጠር ታማኝነታቸውን እንዲገልጹላቸው የማባበል ወይም የማስገደድ አዝማሚያ እንዳይኖር መጠንቀቅ አለባቸው።

## በማጠቃለያ

- የቤተ ክርስቲያን አመራር በጎብረት ነው - በነጠላ አይደለም
- የአረኛና የሽማግሌ አገልግሎት ተመሳሳይ ስለሆነ አንድ ተግባር ነው።
- እረኛ (እረኞች) በሌሎባቸው ማኅበሮች (ቤተ ክርስቲያኖች) መሪዎች ሽማግሌዎች ናቸው። እረኛ (እረኞች) ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጡ የቤተ ክርስቲያን አመራር በጋራ የሽማግሌዎችና የእረኛው (እረኞች) ጎብረት (ጉባኤ) ይሆናል።
- የእረኞች የአገልግሎት ዋና ትኩረት በጎችን በመጠበቅ፣ በማሰማራትና በመመገብ ላይ መሆን ይገባዋል።
- እረኛው (እረኞች) እና ሽማግሌዎች በጋራ ሲመሩ ለሰብሳቢነት ከመካከላቸው ለቦታው የበለጠ ጸጋ ያለውን (የሚታይበትን) ሰው መምረጥ አግባብ ነው። ከሌሎች የላቀ ወይም ግልጥ የሚታይ የሰብሳቢነት ጸጋ (ችሎታ) እስካለው ድረስ እረኛው ሰብሳቢ ቢሆን ለሥራው የበለጠ ይበጃል።
- በአንድ የሽማግሌዎችና እረኞች ስብስብ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ «ዋናዎች» ማለት የመምራት ጸጋ የሚታይባቸው ሲኖሩ (ቢኖሩ) «ዋናነቱን» ማፈራረቅ መልካምና ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ይሆናል።
- ሰብሳቢው ከሽማግሌዎች በሆነ ጊዜ ያ ሽማግሌ (የሙሉ ጊዜ ሽማግሌ/ሠራተኛ እስካልሆነ ድረስ) ሰብሳቢነቱን ከመተዳደሪያ ሥራው ጋር አጣምሮ በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሥራት አዳጋች እንዳይሆንበት ወይም አገልግሎቱ የማይበደል መሆኑን በእጅጉ ማጤን ያስፈልጋል።
- በአስተዳዳርና በአመራር ሥርዓት መሠረት ሰብሳቢ የሆነው ሰው ሽማግሌም ይሁን እረኛ የራሱ ጉዳይ (ፋይል) በሚታይበት ስብሰባ የጉባኤው ሰብሳቢ ሊሆን አይገባም- መቸስ ሰው አይደል!! የእርሱ ጉዳይ (ማለትም የቀለብ ጭማሪ፣ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ፣ ወዘተ) ውይይቶች ሲሆን እርሱ በሌለበት ቢደረጉ፣ ያለዚያ ግን የዚያን ጊዜ ሰብሳቢነቱን ሌላ ሰው ሊይዘው ይገባል።
- በመተዳደሪያ ደንብ ደረጃ የቤተ ክርስቲያን አመራር በሽማግሌዎችና እረኞች ጎብረት ሆኖ እያለም እንኳን ሰብሳቢ ሆኖ የሚመረጠው እረኛ ወይም ሽማግሌ የአንድን ሰው ብቸኛ ወይም የነጠላ አመራር ዘይቤን እንዳይዝ መጠንቀቅ መልካም ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዚህ ዋና ለተባለው ሰው «የግሉ» እንደሆነች እስከሚመስል ድረስ «ዋናው» ለብቻው የራሱ እንዳያደርጋት። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗ ለአፍታም ያህል መዘንጋት የለበትም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ኢየሱስ እንጂ የአንድ ሽማግሌ ወይም እረኛ ባለመሆኗ ከዋና መሪነት ጋር ተያይዞ በስፋት

እየታየ ያለውን «የአኔ» ወይም «የአከሌ» ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ማስወገድ ይገባል።

- «ዋናነት» በትግል ወይንም መለያየትን በማምጣት አይሁን። መከበር የሚፈልግ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያግኝ፣ በሰውም ዘንድ መከበሩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሚገለጽ የጸጋ ሙላትና በትሕትና አገልግሎቱ ይሁን።

- የሚመረጠው የአስተዳደር አደረጃጀት በየአጥቢያው ሊወሰን ቢችልም ቁልፉ ነጥብ በአመራር «ዋና» የሚሆነው ሰው (ዋና እረኛ፣ ሰብሳቢ፣ ፕሬዝዳንት፣ ወዘተ ተብሎ የሚሰየመው) ለአሠራሩ፣ ለገንዘብና ንብረት አስተዳደሩ ለቤተ ክርስቲያን ተጠያቂ የሆነበትን የማያሻማ መመሪያ ማዘጋጀት ነው።

- እንደ አዕማድ በሚታዩ ጥቂት ሰዎች የሕይወት ውድቀትና ማባከን ምክንያት የእግዚአብሔር ስም እንዳይሰደብና ክርስትናም እንዳይነቀፍ በተለይ በመሪነት ላይ የሚሆኑትን ሰዎች ከሚዘጋጀው የአሠራር መመሪያ አንጻር በሕይወትና አገልግሎት ተጠያቂነት ላይ ጠበቅ አድርጎ መያዝ ለራሳቸው ጥቅምና ለቤተ ክርስቲያን ጤናማነት በእጅጉ ያግዛል።

- በገንዘብ አስተዳደር ለእግዚአብሔርና ለሰው አእምሮ የሚመች መንገድን መንደፍና ከሚዘረጋው ግልጽ ሥርዓት ውጭ ማንም ሰው እጁን ከገንዘብ አስተዳደደር እንዲያርቅ ማድረግ ተገቢ ነው። (በዚህ ዘመን ይህን ነጥብ አንዳንድ «ዋና» መሪዎች አይፈልጉትም/ አጥብቀው ይቃወሙታል። እነርሱ አይውደዱት እንጂ ምክሩ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፦ «ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን» እንደተባለ።

- እንዲሁም «በጌታ ፊት ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ» (2ቆሮ 8:20-21) ተብሎ እንደተጻፈ የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት፣ አሠራርና መዝገብ አያያዝ ግልጽ የሆነና በሚያየውም ዘንድ ከትክክለኛነቱ በስተቀር የማያሳፍር መሆን አለበት።